አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች


*የቤተሰብና የማህበረሰብ ተሳትፎን ማጠናከር*

# የልዩ ትምህርት የቤተሰብ ግብአትና መረጃ መመሪያ















*ብሔራዊ ትምህርት ቤት የህዝብ ግንኙነት ማህበር*
*ቼሰፒክ ምእራፍ 2012*
*የኮሚንኬሽን ውድድር*
**የላቀ ተሸላሚ**

# ትርጉም

If you are interested in learning more about special education and prefer to speak in Amharic, Arabic, Bengali, Mongolian, Russian, Spanish or another language, please contact the Special Education Parent Resource Center (PRC) at 703-228-7239.

Arlington Public Schools has interpreters available by telephone, and we will be happy to assist you.

Si quiere saber más acerca de Educación Especial y prefiere hablar con alguien ya sea en español, amhárico, árabe, mongol, o bengalí, por favor, contacte el Centro de Recursos para Padres, al 703.228.7239. Las Escuelas Públicas de Arlington cuentan con intérpretes disponibles por teléfono, y con gusto le ayudaremos.

ስልዩ ትምህርት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈጉ (በአማርኛ፣ አረብኛ፣ ቤንጋሊ፣ ሞንጎሉያና በስፔንኛ) እባክዎ የልዩ ትምህርት የወላጆች መረጃ ማእከልን (PRC) በ 703.228.7239 ያግኙ። አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤት የስልክ አስተርጓሚዎች ያሉት ሲሆን ስንረዳዎ በደስታ ነው።

إن كنت ترغب فى معرفة المزيد عن التعليم الخاص باللغات (ألمهارية ، العربية ، البنغالية ، المنغولية والإسبانية) الرجاء إلتصال على مركز موارد آلباء للتعليم الخاص على هذا الرقم: 703.228.7239 هنالك خدمة للترجمة الفورية بالتلفون لمدارس آرلنجتون العامة ، وسنكون سعداء لمساعدتكم.

আপিন িনশল নলkেl mেশক (আম ানরক,িআরী,িl ং া,মাংশ ান য়াি িel ং sয্াি ীল ভা ায়) আশরা জাি েশ আg ী শ ,িag কশর 703.228.7239 িmশর sspl eডুশকিল পযাশরn নরশ l ( s nাশর sযা াশযা কিি। আন (lংP পাি ন ক s -e sটন শ াি শ s াভা ী পাoয়া যায় িel ং আমরা িআপাশক িেআশর াে শ াে য়া িকর।

Та Тусгай Боловсролын талаархи дэлгэрэнгүй *(Амхар, Араб, Беангли, Монгол, Испани хэлүүд дээр)* мэдээлэл авах сонирхолтой бол 703.228.7239 тоот утсаар Тусгай Боловсролын Эцэг Эхчүүдийн Мэдээллийн Төв *(Special Education Parent Resource Center)*- тэй холбогдоно уу. Арлингтоны Улсын Сургуулиас утсаар хэлмэрч авах үйлчилгээ үзүүлдэг ба бид танд туслахад баяртай байх болно.

የልዩ ትምህርት

# የቤተሰብ ግብአትና መረጃ

## መ መ ሪ ያ




የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
የተማሪ አገልግሎት እና ልዩ ትምህርት ክፍል
የልዩ ትምህርት ቢሮ
1426 N. Quincy Street
Arlington, VA  22207

ዶ/ር ፓትሪክ ኬ.መርፊ፣ የበላይ ተቆጣጣሪ
ዶ/ር ብሬንዳ ዊልክስ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ፣ የተማሪ አገልግሎት
ሚስተር ፖል ጃሜልስካ፣ ዳይሬክተር፣ የልዩ ትምህርት ቢሮ



የተሻሻለው – ግንቦት/2017

# ማውጫ

እንኳን ደህና መጣችሁ እና ምስጋናዎች
እንደ ወላጅ/አሳዳጊ የእኔ ሚና

## ልዩ ትምህርት፡ ቁልፍ ለሆኑ ስብሰባዎችና ሽግግሮች መዘጋጀት

የልዩ ትምህርት የወላጅ መገልገያ ማእከልና የልዩ ትምህርት ኡደት
የተማሪ ጥናት ኮሚቴ ስብሰባዎች
በቨርጂኒያ የብቃት ኮሚቴ ስብሰባዎችና የአካል ጉዳተኛ ልጆች
የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባዎችና የተማሪ ምደባ
የድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባዎች
የድጋሚ ግምገማ ስብሰባዎች
የቤተሰብ/የትምህርት ቤት ትብብር
ቁልፍ እውቂያዎች
ሽግግሮች

## የእኔ ልጅ

ልጅዎን በትምህርት ቤት ካለ ከሰራተኞች ጋር ማስተዋወቅ
የእኔ ምርጥ ቀን፡ *ለክፍልህ አዲስ ነኝ፣ እራሴን እንዳስተዋውቅ ፍቀድልኝ*

## የመዝገብ-መያዣ መሳሪያዎች

መዝገብ አያያዝ
የዳራ መረጃ
የሕክምና መረጃ
የትምህርት ቤት ግምገማዎች
የሂደት ሪፖርቶች
ያለፉ IEP
የግል ሪፖርቶች

## ለወላጆችና አሳዳጊዎች መርጃዎች

የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መርጃዎች
የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች ኮሚቴዎችና ማህበራት
ቁልፍ ህትመቶችና ቁሳቁሶች
የአርሊንግተን ካውንቲ ፕሮግራሞችና ቢሮዎች
የአርሊንግተን ድጋፍ ቡድኖችና ኔትዎርኮች
የሰሜን ቨርጂኒያ ድጋፍ ሰጪ ቡድኖች
ጥብቅና/ክፍሎች/ስልጠና/ድጋፍ
የኮንፈረንስ እድሎች
ለወታደራዊ ቤተሰቦች መርጃዎች
ጊዜአዊ እንክብካቤ መስጫ
የተለያየ ምንጭና የማህበራዊ ዋስትና ገቢ



ይህ *የልዩ ትምህርት የቤተሰብ ግብአትና የመረጃ መመሪያ* የተዘጋጀው በ 2011-12 የትምህርት ዘመን ከቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ ዩኒቨርሲቲ የኦቲዝም ማእከል (VCU-ACE) በእርዳታ በወላጆችና በአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) አባላት በትብብር ሲሆን በ 2016 ተሻሽሏል፡፡

የAPS ልዩ ትምህርት ስርአትን ሲጎበኙ የእኛን ድጋፍ የምናደርግልዎና ይህ መመሪያም የሚከተሉትን ለማድረግ እንደሚረዳዎት ተስፋ እናደርጋለን፡ የልጅዎ የትምህርት ቡድን ንቁ አባል ይሁኑ፣ ስለልጅዎ መረጃ ያደራጁ፣ ከትምህርት ቤትዎ ጋር በትብብር ይስሩ፣ እርስዎንና ልጅዎን ለመደገፍ ያሉትን የተለያዩ መገልገያዎችን ያግኙ እንዲሁም ልጅዎን ወክለው የሚቻሉትን ውሳኔዎች ያሳልፉ፡፡



---

## ምስጋና

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እና በዚህ መመሪያ የመጀመሪያ ህትመት ወቅት በነበራቸው/በያዙት የሥራ ኃላፊነቶች ተለይተው የተቀመጡት **የ 2011 -2012 የአርሊንግተን VCU -ACE የቡድን** አባላት ከቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል እና ከቨርጂኒያ የባህርይ ጤና እና ልማት አገልግሎቶች ክፍል የተገኘን እርዳታን ተግባራዊ ለማድረግ ሰርተዋል፡፡ የእነሱ ቁርጠኝነት፣ ትብብርና ሙያዊ እውቀታቸው በዚህ መመሪያ ውስጥ እና ከዚህ ስራ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ለተረጋገጠላቸው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የትምህርት አገልግሎቶችን ለማሻሻል በአሁኑ ጊዜ እየተካሄዱ ባሉ የተለያዩ ውጥኖች ላይ ተንፀባርቀዋል፡፡

ኤም. አሌክሳንድራ አሪጋ፣ *ወላጅ*
ዶክተር ሎረን ቦኔት፣ *የንግግር ፓቶሎጂስት*
ዶና በድዌይ፣ *ወላጅ*
ስቲቨን ሴልመር፣ *የVCU-ACE የቴክኒክ ድጋፍ ተባባሪ*
ዶ/ር ጁሊ ክራውፎርድ፣ *የልዩ ትምህርት ቢሮ ዳይሬክተር*
ላውራ ዴፓች፣ *የኦቲዝም ባለሙያ*
ኤሪን ዶኔሁ፣ *የኦቲዝም ስፔሻሊስት*
ካትሊን ዶኖቫን፣ *የPRC አስተባባሪ*
ዲቦራ ሀመር፣ *የኦቲዝም ስፔሻሊስት*

ሱዛን ሆላንድ፣ *የምክር ዳይሬክተር*
ጆይስ ኬሊ፣ *የሽግግር አስተባባሪ*
ሞሪን ኔሴልሮዴ፣ *ረዳት ርዕሰ መምህር*
ዶ/ር ሊዛ ፒሆታ፣ *ርዕሰ መምህር*
ኢሌን ፖርተር፣ *የልዩ ትምህርት አስተባባሪ*
ጃኔት ኳንትሪል፣ *የልዩ ፕሮግራሞች ተቆጣጣሪ*
ካሮሊ ቲይል፣ *የልዩ ትምህርት አስተባባሪ*
ዶ/ር ቴሪግ ቶማስ፣ *ወላጅ*
ቤት ዚቪች፣ *የልዩ ትምህርት መምህር*

በዚህ ህትመት ውስጥ የተጻፉ እና አርትኦት የተሰራባቸው ሰነዶች በማቅረባቸው እና በዚሁ መመሪያ ዝግጅት አጠቃላይ *ሥራቸው* **አልክሳንድራ አርያጋ** *(ወላጅ)* እና **ካትሊን ዶኖቫን** *(የልዩ ትምህርት ወላጅ-ምንጭ ማእከል አስተባባሪ)* ልዩ ምስጋና ይድረስ ተባባሪነታቸው በጠንካራ የትምህርት ቤት አጋርነት አማካኝነት እውን የሚሆን የበጎ ውጤት ተምሳሌት ነው፡፡

እንዲሁም *ለኢማ ፓረል፣* የወላጅ ምንጭ ማእከል አስተዳደራዊ ረዳት ለቴክኒካዊ ድጋፏ እንዲሁም ጄንሎ APS የህትመት ተቆጣጣሪ ለመመሪያው፣ ሙያዊ እውቀትና ድጋፍን፣ ዶክተር ረጂኒያ አሪያጋ እና ሚስ እስቴላ ማርቴኔዝ በስፓንሽ እና ቋንቋ ትርጉም ላበረከተችው ድጋፍ፣ ዲኪቬር በዳሰሳው እና ወቅታዊ በማድረግ ባበረከተው አስተዋጽኦ እንዲሁም ይህንን መመሪያ በማዘጋጀት ሂደት እገዛ ላበረከቱ በርካታ *የአርሊንግተን ወላጆችና ሠራተኞች፣* ኬሬን ሻምኩስ እና የAPS PEP (የስራ ቅጥር ዝግጁነት ፕሮግራም) ላበረኩት የፕሮዳክሽን ድጋፍ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ከቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት እና ተማሪዎች አገልግሎት ጽህፈት ቤት በተገኘው እርዳታ በ 2016 መመሪያው በድጋሚ እንዲታተም አስችሏል፡፡ ይህንን ፕሮጀክት በመደገፋቸው ለVDOE ሀንክ ሚሊዋርክ፣ ግሎሪያ ዴልተን እና ቴሬሲ ሊ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

# እንደ ወላጅ/ሞግዚት የእኔ ሚና ምንድን ነው?

ወላጆች የልጆች ትምህርታዊ ቡድኖች ዋጋ የሚሰጣቸው አባላት ናቸው፡፡ እርስዎ በልጅዎ ላይ ልዩ ባለሙያ ነዎት፡፡ የልጅዎን ታሪክ፣ ጥንካሬና ፍላጎት በሚገባ ያውቃሉ፡፡ እርስዎ የልጅዎ ትምህርታዊ ቡድን ቋሚ አባል ነዎት፡፡ እርስዎ ከሚጫወቷቸው ሚናዎች ጥቂቱ፡

*እንደ መብት ተከራካሪ ወላጅ፡* ከምንም የበለጠ ልጅዎን ያውቁታል ስለሆነም የልጅዎን የትምህርታዊ ቡድን ጠቃሚ አባል ነዎት፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥ የግንኙነትዎ ዋና ነጥብ ማን መሆን እንደለበት መጠየቅና ልጅዎን ትምህርት ላይ ለመርዳት ገንቢ በሆነ መልኩ እንደቴ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ይጠይቁ፡፡ ስለልጅዎ የሚያውቁትን እንዲሁም ስለ አገልግሎት ያወቁትንና የሚቻለውን የላቀ ምክረ ሀሳብ እና ውሳኔ ለመስጠት ያሉትን አማራጮች መጠቀም፡፡ እንደወላጅ ልጅዎን በተለያዩ ሁኔታዎች ቤት ውስጥ፣ በመጫወቻ ሜዳ፣ በአጎራባች ቦታዎች እንዲሁም በሌሎች በርካታ ሥፍራዎች ልጅዎን ያያሉ፡፡ ልጅዎ በአዳዲስ ሁኔታዎች እንዴት እንደሚንቀሳቀስ እና ከአዋቂዎች ብሎም ልጆች ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲሁም የሚያደርጋቸውን የሚታወቁ መሻቶችና ፍላጎቶችን ያውቋቸዋል፡፡

*ወላጅ እንደ መምህር፡* እርስዎ የልጅዎ ቋሚ አስማሪና የልጅዎን ትምህርታዊ ታሪክ የሚያውቁ ነዎት፡፡ እርስዎ ልጅዎ ቤት ውስጥ ምን እንደሚሰራ እና ለእርስዎ እና ለልጅዎች ቤት ውስጥ የሚሰሩትን ከተሞክሮ እና ሀሳበት ከትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጋር በመጋራት መወያየት ይችላሉ፡፡ እንዲሁም በእርስዎ ቤት ውስጥም ይሁን የትም ቦታ በሚኖሩበት ጊዜ የልጅዎን የተግባር ክህሎት በመደገፍ ትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪውን ትምህርት ማጠናከር ይችላሉ፡፡ መልካም ተግባቦት በማበረታታት በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ውጭም በሚኖር ማንኛውም ቦታ የሚያስተምሩበትን/የሚያከላክሉበትን እድል በመፍጠር ሊያግዙት ይችላሉ፡፡

*ወላጅ እንደ አጋር፡* የልጅዎን ፍላጎቶች መለየትና ከልጅዎ የሚጠብቁዋቸውን ነገሮች፣ ተስፋዎና ህልምዎ ከቡድኑ ጋር መወያየት፡፡ ግብአትዎን ማጋራት ለቡድኑ ማስታወቅ እና ግልጽ ተግባቢ በመሆን አስፈላጊ ሲሆን ከቡድንዎ ምክር መጠየቅ፡፡ እርስዎ የሚመርጡትን የተሳትፎና የትብብር ደረጃዎች ላይ ያለዎትን ሀሳብ በመግለጽ ትምህርትን መሰረት ያደረገ የቡድን አባላት ጋር በመሆን አጋርነትን ገምቢ በሆነ መልኩ ለመመስረት ምርጥ ስለሆነ መንገድ መወያየት፡፡

*ወላጅ እንደ ተራኪ፡* አዳዲስ ፕሮግራሞች እና አገልግሎት አቅራቢዎች ወቅታዊ የሆነ መዝገብ ያላቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ፡፡ ዘወትር ስለልጅዎ ሪፖርቶችና ሰነዶች ቅጅ በሙሉ ጠይቀው ማስቀመጥና ልጅዎ በህይወት ዘመኑ/ኗ የሚያገኛቸውን/የምታገኛቸውን አገልግሎቶች ይቆጣጠሩ፡፡ ይህ መረጃ ልጅዎ ትምህርት ቤት ስለሚያገኘው አገልግሎት ለመወሰን የሚረዳ እና ልጅዎ ከትምህርት ቤት ወደ አዋቂነት በሚሸጋገርበት ወቅት የአዋቂዎችን አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

# ልዩ ትምህርት፡
# ለቁልፍ ስብሰባዎች
# እና
# ሽግግሮች መዘጋጀት

# የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
# የልዩ ትምህርት የወላጅ መርጃ ማእከል (PRC)
## የሳይፋክስ አካዳሚክ ማእከል በሴኮያ ፕላዛ
## 2110 Washington Boulevard, Suite 158
## Arlington, VA 22204
### www.apsva.us/prc
### 703-228-7239



የ PRC አላማ የአካል ጉዳተኛ ልጆች ቤተሰቦች የልጃቸውን ልዩ የትምህርት ፍላጎቶች ለመለየትና ለማሟላት ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር ሲሰሩ መረጃ እና ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ በ PRC ያሉ ሰራተኞች ስለልጃቸው የአካል ጉዳት፣ የልዩ ትምህርት ሂደት፣ ለመብት መሟገትና ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ወክለው ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር እንዴት መስራት እንደሚችሉ የበለጠ ለማወቅ ሁሉም ቤተሰቦች እንዲያነጋግሯቸው በራቸው ክፍት ነው፡፡ በቋንቋ አስተርጓሚዎች በኩል የ PRC ሰራተኞች ከእንግሊዝኛ ውጪ ባሉ ቋንቋዎች መናገር ከሚመርጡ ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት ማድረግ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም PRC ቤተሰቦችን ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ለማገናኘት ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረጉ የግንኙነት ነጥቦች ሆነው የሚያገለግሉ የወላጅ ማገናኛዎች አሉት፡፡

PRC የሚያቀርበው፡


- በትምህርት አመቱ በሙሉ በአካል ጉዳትና በወላጅነት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ነጻ የወላጅ ትምህርት ክፍለ ጊዜዎች
- ከአካል ጉዳተኝነት፣ ከወላጅነት እንዲሁም ከአጠቃላይና ከልዩ ትምህርት ጋር በተያያዙ መርጃዎችን የሚያበድሩ ቤተመጽሐፍት፡፡
- የመረጃ ድረገጽ በ www.apsva.us/prc ፡፡
- እርዳእና ድጋፍ ለማድረግ በግለሰብ ደረጃ የቤተሰብ ስብሰባዎችና ምክክር
- የኢ-ዜና ዝመናዎች በ APS School Talk (በ www.apsva.us ላይ ይመዝገቡ)
- ከማህበረሰብ ድጋፍ ቡድኖችና ዝርዝር አቅራቢዎች ጋር ለመገናኘት እገዛ ማድረግ
- መረጃና ሪፈራል
- የልዩ ትምህርት ሂደትን በማሰስና ከትምህርት ቤት ሰራተኞች አባላት ጋር በመተባበር እገዛ ማድረግ

PRC ከሰኞ እስከ አርብ ከ 8፡30 ኤ.ኤም እስከ 4፡00 ፒ.ኤም ክፍት ነው፡፡ ምሽትና ቅዳሜ በቀጠሮ ይገኛሉ፡፡ በማንኛውም ጊዜ ቤተ መጻሕፍቱን ለመመልከት ቤተሰቦች ቢመጡ መልካም አቀባበል ይደረግላቸዋል፡፡

ነገር ግን፣ ከ PRC አስተባባሪ ጋር ለመገናኘት የሚፈልጉ ከሆነ ከተቻለ አስቀድመው ቀጠሮ ማስያዝ መልካም ይሆናል፡፡ PRC የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መጥፎ የአየር ሁኔታ ፖሊሲን የሚከተል ሲሆን በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ምክንያት ትምህርት ቤቶች ከተዘጉ፣ PRC እንዲሁ የሚዘጋ ይሆናል፡፡ ስለ PRC የበለጠ ለማወቅ፣ የአቅጣጫዎችንና የመኪና ማቆሚያ መረጃን ለማግኘት የ PRC አስተባባሪ ያግኙ ወይም ቀጠሮ ለመያዝ እባክዎን በ http://www.apsva.us/prc በኩል ይጎብኙን፡፡

# የልዩ ትምህርት ሂደት

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ ቤተሰቦች መብቶቻቸውንና ኃላፊነታቸውን፣ የልጆቻቸውን መብቶች እንዲሁም የልጆችን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት የትምህርት ቤቶች ያለባቸውን ሀላፊነቶች እንዲረዱ ለማገዝ ***የወላጅ የልዩ ትምህርት መመሪያን*** በ 2010 አሳትሟል፡፡




መመሪያው የልዩ ትምህርት ሂደትን እንዲሁም ከአርስዎና ከአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች በእያንዳንዱ የሂደቱ ደረጃ ላይ ምን እንደሚጠበቅ ይገልጻል፡፡ ቤተሰቦች በልዩ ትምህርት ስብሰባዎች ላይ ከመገኘታቸው በፊት መመሪያውን እንዲመለከቱ ይበረታታሉ፡፡

ይህ መመሪያ እያንዳንዱን የልዩ ትምህርት ሂደት ደረጃ አጉልቶ የሚያሳይ ቢሆንም እንዲሁም ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ በ VDOE ***የወላጅ የልዩ ትምህርት መመሪያ*** ውስጥ ይገኛል፡፡


የ VDOE ***የወላጆች መመሪያ*** በኦንላይን ላይ ይገኛል፡

እንግሊዘኛ፡ http://www.doe.virginia.gov/special_ed/parents/parents_guide.pdf
ስፓኒሽ፡ http://www.doe.virginia.gov/special_ed/parents/parents_guide_spanish.pdf
e- PUB ለሞባይል ጽሑፍ
አንባቢ፡http://www.doe.virginia.gov/special_ed/parents/parents_guide.epub

ተጨማሪ የ VDOE የወላጅ ግብአቶችና የልዩ ትምህርትን በተመለከተ መረጃ በ http://www.doe.virginia.gov/families/index.shtml ይገኛል፡፡

በመጨረሻም፣ የቨርጂኒያ ልዩ ትምህርት የወላጅ ግንኙነት በ https://vafamilysped.org/ ላይ ለቤተሰቦች ብዙ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡

# የልዩ ትምህርት ኡደት



# የተማሪ ጥናት ኮሚቴ ስብሰባዎች

# የተማሪ የጥናት ኮሚቴ (SSC) ስብሰባ

**የተማሪ ስም:**______________________ **ቀን:** ______________

| | |
|---|---|
| **የተማሪ ጥናት ኮሚቴን በጨረፍታ** | **የተማሪ ጥናት ኮሚቴ ምንድን ነው (SSC)?**<br>SSC የማንኛውንም ተማሪ አሳሳቢ ጉዳዮችና ፍላጎቶች ለመገምገም የተሰባሰበ ቡድን ነው::<br>**የ SSC አባላት እነማናቸው?**<br>ወላጅ/አሳዳጊ እንዲሁም በአጠቃላይ ርእሰ መምህር/ረዳት ርእሰ መምህር ወይም ተወካይ፣ የክፍል መምህር እና/ወይም ሌሎች በትምህርት ቤቱ እና/ወይም በቤተሰብ የተጋበዙ ናቸው::<br>**በምን ጉዳይ ላይ ውይይት ይደረጋል?**<br>• ልጁን የላከው ግለሰብ የሚኖሩትን ስጋቶችን ያካፍላል::<br>• ልጅዎን የሚመለከቱ ሁሉም ጠቃሚ መረጃዎች ይገመገማሉ::<br>• ማንኛውም የሚገኝ የህክምና መረጃ ከግምት ገብቶ ይታያል::<br>**የሚወሰነው ምንድን ነው?**<br>• ቡድኑ በልጅዎ ክፍል(ሎች) ውስጥ ስልቶችን እና/ወይም ጣልቃገብነቶችን እንዲሞከሩ ሊመክር ይችላል::<br>• ቡድኑ ልጁን ለልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁነት ግምገማ ሪፈር ሊያደርገው ይችላል:: ቡድኑ ግምገማ ካቀረበ እንዲሁም እርስዎ ፈቃደኛ ከሆኑና ፈቃድ ከሰጡ፣ ልጅዎን ይኖርበታል ተብሎ በተጠረጠረው የአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ ብቁ በሆኑ ባለሙያዎች (ከቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል (VDOE) ወይም ሌላ ተገቢ የስቴት ወይም ብሔራዊ ኤጀንሲ የሚፈለጉትን ፈቃድ የያዙ ሰዎች) ምርመራ ማድረግ ይኖርበታል:: እነዚህም ተገቢነት ካላቸው የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ: ጤና፣ እይታ፣ መስማት፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ሁኔታ፣ አጠቃላይ የማሰብ አቅም፣ የትምህርት ብቃት፣ የተግባቦት ሁኔታቸ የሰውነት እንቅስቀሴ ችሎታዎች እንዲሁም የመላመድ ባህሪ:: የሚመከሩ የግምገማ ክፍሎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ: ማህበረ-ባህላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ትምህርታዊ፣ አስተማሪ ትረካና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ እንደ የንግግር/ቋንቋ እና/ወይም የአካል እንቅስቃሴ ህክምና:: |
| **ለማዘጋጀት የሚሆኑ ጠቃሚ ምክሮች**<br>*ትምህርት ቤትዎ እርስዎ ለሚያደርጉት አስተዋጽኦ ዋጋ ይሰጣል::* | • የልጅዎን ጥንካሬዎችና ድክመቶች ለማንጸባረቅ ጊዜ ይውሰዱ::<br>• እንደአስፈላጊነቱ የልጅዎን ምላሽ ይቀበሉ::<br>• ማጋራት የሚፈልጉትን ማንኛውንም የግል ሪፖርቶችን ያሰባስቡና ያስገቡ::<br>• ለዚህ ስብሰባ ቤተሰብዎ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮችና የሚፈለጉትን ውጤቶች ግምት ውስጥ ያስገቡ:: ሃሳቦችህን ለማደራጀት ለማገዝ የመወያያ ነጥቦችን ክፍልን (ከታች) ይጠቀሙ::<br>• በስብሰባው ወቅት ሊጠይቋቸው የሚፈልጓቸውን ጥያቄዎች በጥያቄዎች ክፍል (ከታች) ላይ ያስፍሩ::<br>• ለመማር የወላጅ መገልገያ ማእከልን (PRC) ያነጋግሩ::<br>• ስለ ሂደቱ የበለጠ ለማወቅ የወላጅ መገልገያ ማእከልን (PRC) ያግኙና የሚቻል ከሆነ ለ PRC "ልዩ ትምህርት መግቢያ" ክፍለ ጊዜ ይመዝገቡ::<br>• ከእርስዎ ጋር ወደ ስብሰባው የሚመጣ ሌላ ሰው እንዳለ ለትምህርት ቤትዎ ያሳውቁ ይህም ትምህርት ቤቱ ቦታና ቁሳቁሶችን በበቂ ሁኔታ ለማዘጋጀት ያስችለዋል:: |
| **እንደ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የእኔ ሚና**<br>*እርስዎ በትምህርት ቡድኑ በእኩል የሚታዩና ጠቃሚ አባል ነዎት::* | • በስብሰባው ላይ በንቃት ይሳተፉ::<br>• የእርስዎን ግብአት፣ ሃሳብ እና ማንኛውንም የሚያሳስቦን ነገር ለማካፈል ምቾት ይሰማዎት::<br>• ጥያቄዎችን እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ማብራሪያን ይጠይቁ::<br><br>*ማሳሰቢያ: ግምገማ የሚመከር ከሆነ፣ ግምገማው ከመካሄዱ በፊት የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልጋል::* |

| የመወያያ ነጥቦች | ጥያቄዎች |
| --- | --- |
| | |

# የብቃት
# ኮሚቴ
# ስብሰባዎች

# የብቃት ኮሚቴ ስብሰባዎች

የተማሪ ስም: ______________________  ቀን: ______________

| የብቃት ኮሚቴ ስብሰባዎች በጨረፍታ | **የብቃት ኮሚቴው ምንድነው?**<br>የብቃት ኮሚቴው ልጅዎ የአካል ጉዳት እንዳለበት እንዲሁም የልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው መሆኑን ለመወሰን የተሰባሰበ ቡድን ነው።<br>**በተለምዶ የብቃት ኮሚቴ አባላት እነማን ናቸው?**<br>ወላጅ/አሳዳጊ፣ ርእሰ መምህር/ረዳት ርእሰመምህር ወይም ተወካይ፣ የክፍል መምህር፣ የልዩ ትምህርት መምህር፣ የልዩ ትምህርት አስተባባሪ (SEC)፣ የትምህርት ቤት ነርስ፣ የትምህርት ቤት የስነልቦና ባለሙያ፣ የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ፣ ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች እና/ወይም ሌሎች በትምህርት ቤቱ እና/ወይም በቤተሰቡ የተጋበዙ።<br>**በምን ጉዳይ ላይ ውይይት ይደረጋል?**<br>• እያንዳንዱ የቡድን አባል (ወላጅ/አሳዳጊን ጨምሮ) ግምገማቸውንና ግብአታቸውን ያጠቃልላሉ።<br>• ቡድኑ ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን፣ የወላጅ ግብአት፣ የመምህራን ምክሮችና የተጠናቀቁና የቀረቡ ግምገማዎችን ጨምሮ በጥንቃቄ የሚመረምር ይሆናል።<br>• ቡድኑ ግምገማዎቹና መረጃዎች ልጅዎ እንደ "አካል ጉዳተኛ ልጅ፣ በዚህም የተነሳ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው" መስፈርቱን የሚያሟላ መሆኑና አለመሆኑ ላይ ጥቆማ ያደርጋል ወይም ውይይት ያካሂዳል።<br>•<br>**የሚወሰነው ምንድን ነው?**<br>• ቡድኑ የጋራ ስምምነትን ለማምጣት የሚሰራና ልጅዎ እንደ "አካል ጉዳተኛ ልጅ፣ በዚህም የተነሳ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው" የብቁነት መስፈርቶችን ማሟላቱን የሚወስን ይሆናል።<br>• እያንዳንዱ የቡድን አባል በብቁነት ውሳኔው መስማማቱን ወይም አለመስማማቱን ይገልጻል። |
|---|---|
| **ለማዘጋጀት የሚሆኑ ጠቃሚ ምክሮች**<br>*ትምህርት ቤትዎ እርስዎ ለሚያደርጉት አስተዋጽኦ ዋጋ ይሰጣል።* | • የእርስዎን የስርአት መከላከያዎች ይገምግሙ።<br>• የልጅዎን ጥንካሬና ድክመቶች ያንጸባርቁ።<br>• የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ "የአካል ጉዳተኛ ልጆች" ትርጓሜዎችን ይገምግሙ (በዚህ ክፍል)። የብቃት ኮሚቴው ለመለየት የሚፈለገው መስፈርት እነዚህ ነው።<br>• ለዚህ ስብሰባ ቤተሰብዎ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮችና የሚፈልጉትን ውጤቶች ግምት ውስጥ ያስገቡ። ሃሳቦችህን ለማደራጀት ለማገዝ የመወያያ ነጥቦችን ክፍልን (ከታች) ይጠቀሙ።<br>• ለማስታወስ የሚፈልጓቸውን ጥያቄዎች በጀርባ በኩል በጥያቄዎች ክፍል ማስታወሻ ይያዙ።<br>• ማጋራት የሚፈልጓቸውን ማናቸውንም የግል ሪፖርቶች (ግምገማዎች፣ የህክምና ሪፖርቶች) ያሰባስቡና ከተቻለ ከስብሰባው አስቀድመው ያቅርቡ።<br>• የብቁነት ፓኬት ከግምገማ አካላት ጋር ቢያንስ ከሁለት ቀናት በፊት የብቁነት ስብሰባው ከመደረጉ በፊት ይገኛል። ከስብሰባው ቢያንስ ከሁለት ሳምንታት በፊት ፓኬቱን ከትምህርት ቤትዎ ልዩ ትምህርት አስተዳደር ረዳት* ጋር ለመቀበል እቅዶችን ያረጋግጡ። *በቻይልድ ፋይንድ ፕሮግራም የሚገመገሙ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ለቻይልድ ፋይንድ በ 703.228.2700 መደወል አለባቸው።<br>• የብቁነት ፓኬቱን ከግምገማ ክፍሎች ጋር በጥንቃቄ ለመገምገም ጊዜ ያውጡ።<br>• ከእርስዎ ጋር ወደ ስብሰባው የሚመጣ ሌላ ሰው እንዳለ ለትምህርት ቤትዎ ያሳውቁ ይህም ትምህርት ቤቱ ቦታና ቁሳቁሶችን በበቂ ሁኔታ ለማዘጋጀት ያስችለዋል።<br>• የወላጅ መገልገያ ማእከል (PRC) የልዩ ትምህርት ትምህርት መግቢያ ላይ ተገኝ፣ ወይም ስለ ሂደቱ የበለጠ ለማወቅ PRCን አግኝ<br>• በወላጅ መገልገያ ማእከል (PRC) *የልዩ ትምህርት መግቢያ* ኮርስ ይሳተፉ፣ ወይም ስለ ሂደቱ የበለጠ ለማወቅ PRC ያግኙ።<br><br>*ከጀርባ ይመልከቱ* |

| | |
|---|---|
| **እንደ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የእኔ ሚና**<br>*እርስዎ በትምህርት ቡድኑ በእኩል የሚታዩና ጠቃሚ አባል ነዎት፡፡* | • በስብሰባው ላይ በንቃት ይሳተፉ፡፡<br>• የእርስዎን ግብአት፣ ሃሳብና ማንኛውንም የሚያሳስቦን ነገር ለማካፈል ምቾት ይሰማዎት፡፡<br>• ጥያቄዎችን እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ማብራሪያ ይጠይቁ፡፡<br>• በብቁነት ውሳኔው ላይ መስማማትዎን ያስቡበትና ይህን ይግለጹ፡፡<br>• ስለ ስብሰባው ውጤት የሚያሳስብዎት ነገር ካለ ቡድኑን ስለሚቀጥሉት እርምጃዎች መጠየቅ የሚችሉ ሲሆን ይህም አለመግባባቶችን ለመፍታት አማራጮችን ሊያካትት ይችላል፡፡ ለተጨማሪ መረጃ PRC ማነጋገርም ይችላሉ፡፡<br><br>*ማሳሰቢያ፡ ልጅዎ ብቁ ሆኖ እንዲገኝና የልጅዎን የአካል ጉዳት ለመለየት ከማናቸውም ለውጦች በፊት የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልጋል፡፡* |

| **የመወያያ ነጥቦች** | **ጥያቄዎች** |
|---|---|
| | |

# በቨርጂኒያ የአካል ጉዳተኛ ልጆች

***በቨርጂኒያ ውስጥ የአካል ጉዳተኛ ልጆች የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞችን የሚመሩ ደንቦች***
የቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል

**"አካል ጉዳተኛ ልጅ"** ማለት በዚህ ምዕራፍ በተደነገገው መሰረት የተገመገመ ልጅ የአእምሮ እክል፣ የመስማት እክል (የመስማት ችግርን ጨምሮ)፣ የንግግር ወይም የቋንቋ እክል፣ የማየት እክል (ዓይነ ስውርነትን ጨምሮ)፣ ከባድ የስሜት እክል አለበት (በዚህ ክፍል "የስሜት እክል" ተብሎ የሚጠራው)፣ የአጥንት እክል፣ ኦቲዝም፣ አሰቃቂ የአንጎል ጉዳት፣ ሌላ የጤና እክል፣ የተለየ የትምህርት እክል፣ መስማት መሳን ወይም በርካታ የአካል ጉዳቶች በዚህ ምክንያት ልዩ ትምህርት የሚያስፈልጋቸው እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማለት ነው፡፡ የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ ይህንን ምድብ በ 8VAC20-81-80 M 3 መሰረት እንደ አካል ጉዳተኝነት ከወሰደው ይህ የእድገት መዘግየትንም ያካትታል፡፡

**"ኦቲዝም"** ማለት የቃልና የቃል-አልባ ግንኙነት እንዲሁም ማህበራዊ ግንኙነት በእጅጉ የሚጎዳ የእድገት እክል ሲሆን በአጠቃላይ ከሶስት አመት በፊት የሚታይና የልጁን የትምህርት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ብዙውን ጊዜ ከኦቲዝም ጋር የተያያዙ ሌሎች ባህሪያት በተደጋጋሚ እንቅስቃሴዎችና የተዛባ እንቅስቃሴዎች ላት ተሳታፊ መሆን፣ የአካባቢ ለውጥን መቋቋም ወይም የእለት ከእለት እንቅስቃሴዎችን መለወጥና ለስሜታዊ ልምዶች ያልተለመዱ ምላሾች ናቸው፡፡ በዋነኛነት ህጻኑ የስሜት መቃወስ ስላለበት የልጁ የትምህርት ክንዋኔ አሉታዊ በሆነ መልኩ ከተጎዳ ኦቲዝም ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ ከሶስት አመት በኋላ የኦቲዝም ባህሪያትን የሚያሳይ ልጅ በዚህ ፍቺ ውስጥ ያሉት መስፈርቶች ከተሟሉ ኦቲዝም እንዳለበት ሊታወቅ ይችላል፡፡

**"መስማት-ማየት የተሳነው"** ማለት በአንድ ጊዜ የመስማትና የማየት እክል ማለት ሲሆን ይህ ጥምረት እንደዚህ አይነት ከባድ የመግባባትና ሌሎች የእድገትና የትምህርት ፍላጎቶችን ስለሚፈጥር በልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች መስማት ለተሳናቸው ህጻናት ወይም ዓይነ ስውር ህጻናት ብቻ ሊስተናገዱ አይችሉም፡፡

**"የእድገት መዘግየት"** ማለት ከመስከረም 30 እስከ 6 ባለው ጊዜ ውስጥ ከሁለት አመት በታች የሆነ ልጅን የሚጎዳ አካል ጉዳተኝነት ነው፡፡

1. በተገቢው የምርመራ መሳሪያዎችና ሂደቶች በሚለካው መሰረት ከሚከተሉት ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ የእድገት መዘግየቶች ያጋጠመው ሲሆን፡ አካላዊ እድገት፣ የእውቀት (ኮግኒቲቭ) እድገት፣ የተግባቦት እድገት፣ ማህበራዊ ወይም ስሜታዊ እድገት፣ ወይም የመላመድ እድገት፣ ወይም የተስተካከለ የአካል ወይም የአእምሮ ሁኔታ ያለው የእድገት መዘግየት ሊያስከትል የሚችል ከፍተኛ እድል ያለው፤
2. መዘግየቱ (ቶቹ) በዋነኛነት በባህላዊ ሁኔታዎች፣ በአካባቢያዊ ወይም በኢኮኖሚያዊ እጦት ወይም በእንግሊዝኛ ችሎታ የተገደበ ውጤት አይደለም፤ እና
3. የመዘግየቱ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሰነድ ባህሪያት መኖሩ በትምህርት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል እናም ተማሪው በዚህ የዕድሜ ቡድን ውስጥ በአጠቃላይ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ለመድረስ እና እድገት ለማድረግ በልዩ ሁኔታ የተነደፈ መመሪያ እንዲኖረው አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

**"የስሜት እክል"** ማለት ከሚከተሉት ባህሪያት ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ለረጅም ጊዜ የሚያሳዩና በተወሰነ ደረጃ የልጁን የትምህርት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥር ሁኔታ ማለት ነው፡

1. በአእምሮ፣ በስሜት ህዋሳት ወይም በጤና ሁኔታዎች ሊገለጽ የማይችል ትምህርትን መማር አለመቻል፤
2. ከእኩዮችና መምህራን ጋር አጥጋቢ የእርስ በርስ ግንኙነቶችን መገንባት ወይም ጠብቆ ማቆየት አለመቻል፤
3. በተለመዱ ሁኔታዎች ውስጥ ተገቢ ያልሆኑ የባህሪ አይነቶች ወይም ስሜቶች፤
4. አጠቃላይ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ወይም የመንፈስ ጭንቀት፤ ወይም
5. ከግል ወይም ከትምህርት ቤት ችግሮች ጋር የተቆራኙ አካላዊ ምልክቶችን ወይም ፍርሃቶችን የማዳበር ዝንባሌ፡፡
6. ከግል ወይም ከትምህርት ቤት ችግሮች ጋር የተቆራኙ አካላዊ ምልክቶችን ወይም ፍርሃቶችን የማዳበር ዝንባሌ፡፡ ስሜታዊ እክል ስኪዞፈሪንያ ያጠቃልላል፡፡ የስሜታዊ እክል እንዳለባቸው ካልተረጋገጠ በስተቀር ቃሉ በማህበራዊ ደረጃ ሳይስተካከሉ የቀሩ ልጆችን አይመለከትም፡፡

**"የመስማት እክል"** ማለት በአንድ ወይም በሁለቱም ጆሮዎች በማጉያም ሆነ ያለማጉያ፣ ቋሚም ሆነ ተለዋዋጭ የመስማት ችግር ሲሆን በልጁ የትምህርት ክንዋኔ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

**"የአእምሮ ጉዳተኝነት"** ማለት ቀደም ሲል "የአእምሮ ዝግመት" በመባል የሚታወቀው ፍቺ ሲሆን ትርጉምም ዝቅተኛ የሆነ አጠቃላይ የአእምሮ እንቅስቃሴ ማለት ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ የመላመድ ባህሪ ጉድለት ያለበትና በእድገቱ ወቅት የሚታየውና በልጁ የትምህርት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

**"በርካታ የአካል ጉዳቶች"** ማለት በአንድ ጊዜ የሚፈጠሩ እክሎች (እንደ አይነ ስውርነት የአእምሮ እክል፣ የአዕምሮ እክል ከአጥንት እክል ጋር) ይህ አብሮ የሚመጣ ከሆነ ከባድ የትምህርት ፍላጎቶችን ስለሚኖሩት በልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ ለአንዱ የአካል ጉዳት ብቻ ሊስተናገዱ አይችሉም፡፡ ቃሉ መስማት-ማየት የተሳናቸው የሚለውን አያካትትም፡፡

**"የአጥንት እክል"** ማለት የልጁን የትምህርት ብቃት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ከባድ የአጥንት እክል ማለት ነው፡፡ ቃሉ በተወለዱ ሕፃናት ምክንያት የሚመጡ እክሎች፣ በበሽታ የተከሰቱ እክሎች (ለምሳሌ፣ ፖሊዮማይላይትስ፣ የአጥንት ሳንባ ነቀርሳ፣ ወዘተ) እና ሌሎች መንስኤዎች (ለምሳሌ ሴሬብራል ፓልሲ፣ መቆረጥና የሰውነት ልምሻን የሚያስከትሉ ስብራት ወይም ቃጠሎ) ያጠቃልላል፡፡

**"ሌላ የጤና እክል"** ማለት ውስን ጥንካሬ፣ ጉልበት ወይም ንቃት፣ ለአካባቢ ማነቃቂያዎች ከፍ ያለ ንቃትን ጨምሮ፣ ይህም ከትምህርት አካባቢ ጋር በተያያዘ የተገደበ ንቃትን የሚያስከትል ሲሆን ይህም እንደ አስም፣ ትኩረትን መጓደል መታወክ ወይም ትኩረትን ማጣት ሃይፐርአክቲቪቲ መታወክ፣ የስኳር በሽታ፣ የሚጥል በሽታ፣ የልብ ሕመም፣ ሄሞፊሊያ፣ በእርሳስ መመረዝ፣ ሉኪሚያ፣ ኔፍሪቲስ፣ የሩማቲክ ትኩሳትና ሲክል ሴል አኒሚያና ቱሬት ሲንድረም በልጁ የትምህርት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

**"ልዩ የመማር እክል"** እንደ የአመለካከት እክል፣ የአንጎል ጉዳት፣ አነስተኛ የአእምሮ እንቅስቃሴ መዛባት፣ ዲስሌክሲያ ና የእድገት አፍዝያ ያሉ ሁኔታዎችን ጨምሮ የማዳመጥ፣ የማሰብ፣ የመናገር፣ የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የፊደል አጻጻፍ ወይም የሂሳብ ስሌቶችን ለመስራት ፍጹም ባልሆነ ችሎታ ራስን መግለጽ መቻል ላይ በቋንቋ፣ በንግግር ወይም በጽሑፍ ከመረዳት ወይም ከመጠቀም ጋር በተያያዙት አንድ ወይም ከዚያ በላይ መሰረታዊ የስነልቦና ሂደቶች ውስጥ መታወክ ማለት ነው፡፡

የተወሰነ የመማር እክል በዋነኛነት የማየት፣ የመስማት ወይም የሰውነት እንቅስቃሴ እክል ውጤቶች የሆኑ የመማር ችግሮች፤ የአዕምሮ እክሎች፤ የስሜታዊ እክል፤ የአካባቢ፣ የባህል ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች አያካትትም፡፡

ዲስሌክሲያ ከሌሎች የመማር እክሎች የሚለየው በድምጽ ደረጃ በሚከሰት ድክመት ነው፡፡ ዲስሌክሲያ ከመነሻው ኒውሮባዮሎጂያዊ የሆነ የተለየ የመማር እክል ነው፡፡ ትክክለኛ እና/ወይም አቀላጥፎ የቃላት ማወቂያ ባላቸው ችግሮችና ደካማ የፊደል አጻጻፍና የመግለጽ ችሎታዎች ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች በአብዛኛው የሚከሰቱት ከሌሎች የግንዛቤ ችሎታዎችና ውጤታማ የክፍል ትምህርት አቅርቦት ጋር በተገናኘ ባልተጠበቀ የቋንቋ የንግግር ድምጽ አካል ጉድለት ነው፡፡ በሁለተኛ ያሉ መዘዞች የቃላትና በቅድሚያ የነበረ እውቀት እድገትን የሚያደናቅፉ የንባብ ግንዛቤ ችግሮችንና የንባብ ልምድን መቀነስ ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

**"የንግግር ወይም የቋንቋ እክል"** ማለት እንደ የመንተባተብ፣ የንግግር እክል፣ የመግለጽ ወይም የመቀበል ችግር፣ ወይም የድምጽ እክል ያሉ የልጁን የትምህርት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድርግ የተግባቦት መታወክ ማለት ነው፡፡

**"አሰቃቂ የአንጎል ጉዳት"** ማለት በውጫዊ አካላዊ ኃይል ምክንያት በአንጎል ላይ የሚገኝ ጉዳት ሲሆን ይህም አጠቃላይ ወይም ከፊል ተግባራዊ የአካል ጉዳት ወይም የስነአእምሮ ማህበራዊ እክል ወይም ሁለቱንም በልጁ የትምህርት ክንዋኔ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡ በአሰቃቂ የአንጎል ጉዳት በክፍት ወይም በተዘጉ የጭንቅላት ጉዳቶች ላይ የሚተገበር ሲሆን ይህም በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ችግሮችን ያመጣል፣ ለምሳሌ የማወቅ ችሎታ፤ ቋንቋ፤ ትውስታ፤ ትኩረት፤ ማመዛዘን፤ ረቂቅ አስተሳሰብ፤ ፍርድ፤ ችግር ፈቺ፤ የስሜት ሕዋሳት፣ የማስተዋልና የሰውነት እንቅስቃሴ ችሎታዎች፣ የስነልቦና ባህሪ፤ አካላዊ ተግባራት፤ የመረጃ ማቀነባበሪያእና ንግግር፡፡ በአሰቃቂ የአንጎል ጉዳት የተወለደ ወይም የተበላሹ በሆኑ የአንጎል ጉዳቶች ላይ ወይም በወሊድ ጉዳት ምክንያት በተፈጠሩ የአንጎል ጉዳቶች ላይ አይተገበርም፡፡

**"የእይታ እክል"** ማለት የእይታ እክል ሲሆን ማስተካከያ ቢደረግም የልጁን የትምህርት ክንውን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ቃሉ ሁለቱንም ከፊል እይታና ዓይነ ስውርነትን ያጠቃልላል፡፡

# የ IEP ስብሰባዎች
# እና
# የምደባ
# ውሳኔዎች

Arlington Public Schools

# የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ

**የተማሪ ስም:** ______________________________ **ቀን:** ________________

<table>
<tr>
<td>የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ በጨረፍታ</td>
<td>
የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም ምንድን ነው?<br>
የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የልጅዎን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት ታስቦ የተነደፈ የጽሁፍ ሰነድ ነው፡፡<br>
በተለምዶ የ IEP ቡድን አባላት እነማን ናቸው?<br>
ወላጅ/አሳዳጊ፣ ርእሰ መምህር/ረዳት ርእሰ መምህር ወይም ተወካይ፣ የክፍል መምህር፣ የልዩ ትምህርት መምህር፣ ተዛማጅ አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ልጅዎ፣ አስፈላጊ ከሆነ እና/ወይም ሌሎች በትምህርት ቤቱ እና/ወይም በቤተሰቡ የተጋበዙ፡፡<br>
በምን ጉዳይ ላይ ውይይት ይደረጋል?
<ul>
<li>የልጅዎ ጥንካሬዎችና ድክመቶች እንዲሁም ትምህርታዊ ስኬትና የተግባር አፈጻጸም ደረጃዎች (PLAFPs) ናቸው፡፡</li>
<li>የልጅዎ የትምህርት፣ የእድገትና የተግባር ፍላጎቶች፡፡</li>
<li>የልጅዎ አካል ጉዳተኝነት በአጠቃላይ ስርአተ ትምህርት ውስጥ ያለው ተሳትፎና እድገት ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚፈጥር፡፡</li>
<li>እንደ አስፈላጊነቱ የባህሪ ጣልቃገብነቶችና ስልቶች፡፡</li>
<li>የግንኙነት ፍላጎቶች፡፡</li>
<li>የቤት-ትምህርት ቤት ግንኙነት፡፡</li>
<li>እድሜያቸው 14 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ተማሪዎች፣ ከስልጠና፣ ከትምህርት፣ ከስራና ከተገቢው ነጻ የሆነ የኑሮ ችሎታ ጋር የተያያዙ የልጅዎ የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦች (በሽግግር ክፍል ውስጥ ያለ ተጨማሪ መረጃ)፡፡</li>
<li>የልጅዎ የተራዘመ የትምህርት ዘመን (ESY) አገልግሎቶችና የረዳት ቴክኖሎጂ ፍላጎትን ጨምሮ ለልጅዎ ነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) በማቅረብ ላይ የተካተቱ ነገሮች በሙሉ፡፡</li>
<li>በትንሹ ገዳቢ አካባቢ (LRE) የአገልግሎት አቅርቦት፡፡</li>
</ul>
የሚወሰነው ምንድን ነው?
<ul>
<li>ሊለኩ የሚችሉ አመታዊ ግቦችና የአጭር ጊዜ አላማዎች አስፈላጊነት፡፡</li>
<li>በስቴት፣ ክፍል እና / ወይም አማራጭ ግምገማዎች ላይ መሳተፍና የሚጠበቁ የዲፕሎማ ውጤቶች፡፡</li>
<li>ወደ አመታዊ ግቦች እንዴት መሄድ እንደሚቻል እንደሚለካ፡፡</li>
<li>የሂደት ሪፖርቶች መቼ እንደሚደርስዎ፡፡</li>
<li>የልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ድግግሞሽ፣ ቆይታና ቦታ፡፡</li>
<li>በልጅዎ ፍላጎቶች ላይ በመመስረት የጥናት ኮርስ፣ ትምህርት፣ ተዛማጅ አገልግሎቶችና የማህበረሰብ ተሞክሮዎችን ጨምሮ የሽግግር አገልግሎቶች (ከ14 አመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ልጆች የሚያስፈልግ)፡፡</li>
</ul>
</td>
</tr>
<tr>
<td>ለማዘጋጀት የሚሆኑ ጠቃሚ ምክሮች<br>ትምህርት ቤትዎ እርስዎ ለሚያደርጉት አስተዋጽኦ ዋጋ ይሰጣል፡፡</td>
<td>
<ul>
<li>የልጅዎን ጥንካሬና ድክመቶች ያንጸባርቁ፡፡</li>
<li>የልጅዎን አስተያየት ይቀበሉ፡፡</li>
<li>ለልጅዎ የአጭርና የረጅም ጊዜ ግቦችዎን ከግምት ያስገቡ፡፡</li>
<li>ልጅዎ በትምህርት ቤት ሊያስፈልጉት ይችላሉ ብለው የሚያስቧቸውን ድጋፎች ያስቡ፡፡</li>
<li>ከተቻለ ከስብሰባው አስቀድሞ አስፈላጊ መረጃዎችን፣ ግብአቶችንና አስተያየቶችን ለ IEP ቡድን ጋር ያጋሩ፡፡</li>
<li>አስፈላጊ ከሆነ ረቂቅ የ IEP ቁሳቁሶችን (ረቂቅ PLAAFPs እና ረቂቅ ግቦች ብዙውን ጊዜ በትምህርት ቤቱ ቢያንስ ከስብሰባው ሁለት ቀናት ቀደም ብለው ይላካሉ) እና የአሁኑ IEP ይጠይቁ፡፡</li>
<li>ረቂቅ ቁሳቁሶችን፣ የሪፖርት ካርዶችንና የ IEP ሂደት ማስታወሻዎችን ለመገምገም ጊዜ መድቡና ለስብሰባው ተዘጋጁ፡፡</li>
</ul>
</td>
</tr>
</table>

| | |
|---|---|
| **ለማዘጋጀት የሚሆኑ ጠቃሚ ምክሮች**<br>*(የቀጠለ)* | • ለቤተሰብዎ ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች እና ለዚህ ስብሰባ የሚፈለጉትን ውጤቶች ከግምት ያስገቡ። ሃሳቦችህን ለማደራጀት ለማገዝ የንግግር ነጥቦችን ክፍል (በቀጣዩ ገጽ) ይጠቀሙ።<br>• በቨርጂኒያ በስቴት ምዘናዎች ለመሳተፍ (የዲፕሎማ አማራጮች ላይ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል) በ VDOE ድረገጽ www.vdoe.virginia.gov ላይ መረጃን ያግኙ።<br>• ስለ ቨርጂኒያ ዲፕሎማ አማራጮች በ www.apsva.us/prc/diplomas/ መረጃ ያግኙ።<br>• በስብሰባው ወቅት ሊጠይቋቸው የሚፈልጓቸውን ጥያቄዎች በጀርባ ባለው የጥያቄዎች ክፍል ላይ ያስፍሩ።<br>• በወላጅ መገልገያ ማእከል (PRC) "የልጅዎ IEP ቡድን ንቁ አባል መሆን" ስልጠና ላይ ተሳታፊ ይሁኑ።<br>• ለዚህ ስብሰባ እንዴት መዘጋጀት እንደሚችሉ ለመወያየት PRC ያነጋግሩ። |
| **እንደ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የእኔ ሚና**<br>*እርስዎ በትምህርት ቡድኑ በእኩል የሚታዩና ጠቃሚ አባል ነዎት።* | • በስብሰባው ላይ በንቃት ተሳታፊ ይሁኑ።<br>• የእርስዎን ግብአት፣ ሃሳብና ማንኛውንም የሚያሳስብዎን ነገር ያጋሩ።<br>• ጥያቄዎችን እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ማብራሪያ ይጠይቁ።<br>• በመጨረሻው ረቂቅ የሚስማሙ ከሆነ IEP እንዲተገበር ፈቃድዎን እንዲሰጡ ይጠየቃሉ።<br>• ፈቃድ ከመስጠትዎ በፊት IEP ለመገምገም የሚፈልጉ ከሆነ የመጨረሻውን ረቂቅ ገምግመው ከስብሰባው በኋላ ለተፈረመበትን ረቂቅ ለትምህርት ቤቱ መመለስ ይችላሉ። (የጽሁፍ ፈቃድ እስኪሰጡ ድረስ፣ ትምህርት ቤቱ በአዲሱ IEP ውስጥ የተገለጹትን ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መጀመር እንደማይችል ይወቁ።)<br>• በስብሰባው መጨረሻ፣ ቡድኑ በ IEP ላይ መግባባት ላይ ካልደረሰ፣ ወይም በመጨረሻው ረቂቅ ካልተስማሙ፣ ተከታታይ የ IEP ስብሰባ የሚዘጋጅ ይሆናል።<br><br>ማሳሰቢያ፡ *የመጀመሪያ IEP ለመተግበርና በልጅዎ IEP ላይ ለሚደረጉ ማናቸውም ለውጦች የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልጋል። ልጅዎ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማግኘቱን በተመለከተ በማንኛውም ጊዜ ፈቃድዎን የመሻር መብት አለዎት።* |

| **የመወያያ ነጥቦች** | **ጥያቄዎች** |
|---|---|
| | |

# የተማሪዎች ምደበና እና አገልግሎቶች

የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) ልዩ የትምህርት አገልግሎት በማግኘት ብቁ ሆነው ለተገኙት እድሜያቸው 2 አመት እስከ 22 ዓመት የሚደርሱ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከቅድመ መዋለ ህጻናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተከታታይ አገልገሎቶችን ይሰጣል፡፡ ልዩ ትምህርት *ከምደባዎች* በተቃራኒ *አገልግሎቶችን* እንደሚያመለክት ማስታወስ ጠቃሚ ነው፡፡ ለምሳሌ ልዩ የትምህርት አገልግሎች በጠቅላላ (መደበኛ) የትምህርት ክፍሎች (ወደ አገልግሎት ማስገባት) እና/ወይም በልዩ የትምህርት አደረጃጀት (አገልግሎቶችን ማስወጣት) በቀጥታ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በሚኖራቸው ልዩ እና ግለሰባዊ የመማር ፍላጎቶች መሰረት ሌሎቹ አብዛኛውን የትምህርት ቀናቸውን በልዩ የትምህርት አደረጃጀት ሲያሳልፍ የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ አብዛኛውን የትምህርት ቀናቸውን በጠቅላላ የትምህርት አደረጃጀት ላይ ሊያሳሉፉ ይችላሉ፡፡ በብዙ አጋጣሚዎች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ወደ አገልግሎት መግባትና አገልግሎት ማግኘትን የመሳሰሉ የተቀናጁ አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

**የምደባ ውሳኔዎች**

እርስዎ የልጅዎን ምደባ የሚወስን የ IEP ቡድን ዋነኛ አባል ሲሆኑ ለዚህ ውሳኔ የእርስዎ ስምምነት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ቤተሰቦች የAPS ተከታታይ አገልግሎቶችን እንዲያውቁ ይበረታታል፡፡ ሁሉም ተማሪ ***ዝቅተኛ የተገደበ አካባቢ*** ውስጥ ***ነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት*** (FAPE) ሊሰጠው ይገባል፡፡

ምደባን በመወሰን ረገድ መጀመሪያ ግምት ውስጥ የሚገባው ልጅዎ የሚፈልገውን አገልግሎትና ድጋፍ ነው፡፡ ቡድኑ በፌደራል ህግ እንዲዳስስ የሚጠበቅበትን ቀጥሎ ግምት ውስጥ የሚገባው ልጅዎ ***በዝቅተኛው የተገደበ አካባቢ*** (LRE) ውስጥ መማሩን ነው፡፡ ይህ LRE ማለት በዋናነት በተቻለ መጠን አብሮት ከሚያድጉ አቻዎች በጠቅላላ የትምህርት አደረጋጀት የሚማሩ እና የልጁን ልዩ የመማር ፍላጎት ለማሟላት አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ከዚሁ አድረጃጅት የሚወጡ ልጆች ናቸው፡፡ በተለምዶ ተገቢ አገልገሎቶች የሚገኙ ከሆነ አገልግሎቶቹን በልጁ የአካባቢ በሆኑት አጎራባች ላይ እንዲሰጡ እንዲሁም በAPS ውስጥ አብዛኛዎቹ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በመኖሪያ አካባቢያቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች እነዚህን ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች እንዲያገኙ ሁሉም ጥረት ይደረጋል፡፡

**ዘላቂ ምደባ እና አገልግሎት ስለመኖር**

የልጆች የትምህርት ፍላጎት የተለያየ እንደመሆኑ መጠን በአርሊንግተን የሚገኙ የሕዝብ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መካከለኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙሉ የልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች የማያቋርጥ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የተወሰኑ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ፍላጎት ማሟላት ይቻል ዘንድ APS በተጨማሪም ስፔሳይዝድ ካውንቲ አቀፍ ፕሮግራም እና በስትራትፎርድ ፕሮግራም የሥራ ቅጥር ዝግጁነት (PEP) ፕሮግራም ምደባ እና ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ሁለተኛ ፕሮግራም ምደባ ይሰጣል፡፡ ወደ ካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች የሚደረግ ምደባ ይኸው ፕሮግራም ይበልጥ የሚገደብ ምደባን የሚወክል በመሆኑ የIEP ቡድን ውሳኔ በጥንቃቄ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የአካል ጉዳተኛ ካልሆኑ አቻዎቻው ጋር የማካተት እድልና ተሞክሮ ምደባ መኖሩ እንደተጠበቀ ለሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅ ነው፡፡ አልፎ አልፎ የIEP ቡድኖች ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ተማሪዎች የቤት ውስጥ አስገዳጅ መመሪያ እንዲተገበሩ ወይም በግል የትምህርት ቤት አደረጃጀት የመሳሰሉ የበለጠ የሚገድቡ አካባቢዎች እንዲመደቡ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም APS በአርሊንግተን በሚገኙ የግል ትምህርት ቤቶች በወላጆቻቸው ለተመደቡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ያገልግሎት እቅድ ይሰጣል፡፡

አገልግሎቶችን እና የካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞችን ጨምሮ ስለ APS ልዩ ትምህርት ሰፊ መረጃ በ https://www.apsva.us/student-services-special-education/special- education-office-of/ ማግኘት ይቻላል፡፡

ስለ ልዩ ትምህርት እንዲሁም የማያቋርጥ አገልግሎት ይበልጥ ለማወቅና የአርሊንግተን ትምህርት ቤት በውክልና ከሚሰሩ ወላጆች ጋር ለመገናኘት ከወላጆች ምንጭ ማእከል (PRC) ጋር እንዲገናኙ ይበረታታሉ፡፡

# የድጋሚ
# ግምገማ
# እቅድ ስብሰባ

# የድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባ

**የተማሪ ስም፡**______________________________ **ቀን፡** ______________

| | |
|---|---|
| የድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባ በጨረፍታ | **የድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባ ምንድን ነው?**<br>የድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባ ለትምህርት ቡድኖች ግምገማዎችን፣ ያሉትን መረጃዎች እና/ወይም አዲስ ግምገማዎችን/ስለ ተማሪ መረጃን እንዲገመግሙ እድል የሚሰጥ ነው፡፡<br><br>ልጅዎ አሁንም "አካል ጉዳተኛ ልጅ"* መሆኑን ለማረጋገጥ ቢያንስ በየሶስት አመቱ ትምህርት ቤቱ ድጋሚ ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ግምገማ ከመደረጉ በፊት የድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባ ይደረጋል፡፡ የድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባ ቀጣይነት ያለው ብቁነትን ለመወሰን ቡድኑ (ወላጆችን ጨምሮ) የግምገማ አስፈላጊነት ከወሰነና ወላጆች ለአዳዲስ ግምገማዎች ስምምነት ከሰጡ ተጨማሪ ግምገማዎች ያስፈልጉ እንደሆነና ለሚካሄዱ ልዩ ግምገማዎች እቅድ ለማውጣት እድል የሚሰጥ ነው፡፡<br><br>የድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባ በየሶስት አመቱ በተደጋጋሚ ሊጠየቅ የሚችልና ወላጆችን ጨምሮ በ IEP ቡድን አባላት ጥያቄ መሰረት ለተጨማሪ አላማዎች የሚደረግ ሲሆን ለምሳሌም፡<br>• አዲስ መረጃ/ሪፖርቶችን መገምገም፣ እና/ወይም<br>• የተማሪውን ወቅታዊ የትምህርት ፍላጎቶች መወሰን፡፡<br><br>**በድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባ ላይ የሚካፈለው ማነው?**<br>ወላጅ/አሳዳጊ፣ ርእሰ መምህር/ረዳት ርእሰ መምህር/ወይም ተወካይ፣ የክፍል መምህር፣ የልዩ ትምህርት መምህር፣ ተዛማጅ አገልግሎት አቅራቢዎች፣ የልዩ ትምህርት አስተባባሪ (SEC)፣ ልጅዎ፣ አስፈላጊ ከሆነ እና/ወይም ሌሎች በትምህርት ቤቱ እና/ወይም በቤተሰብ የተጋበዙ፡፡<br><br>**በምን ጉዳይ ላይ ውይይት ይደረጋል?**<br>ቡድኑ ስለልጅዎ ያለውን መረጃና ዳታ ይገመግማል እንዲሁም ለማወቅ ምን ተጨማሪ ዳታ እንደሚያስፈልግ ይወስናል፡<br>• ልጅዎ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚፈልግ "አካል ጉዳተኛ ልጅ"* ሆኖ ስለመቀጠሉ፣ እና/ወይም<br>• አሁን ላይ ያሉት የልጅዎ የትምህርት ፍላጎቶች፣ እና/ወይም<br>• የልጅዎ የትምህርት ስኬት ደረጃና ተዛማጅ የእድገት ፍላጎቶች፡፡<br><br>**የሚወሰነው ምንድን ነው?**<br>ልጅዎ ገና አካል ጉዳተኛ* ልጅ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን ማንኛቸውም ግምገማዎች እና/ወይም መረጃዎች ሊያስፈልግዎ የሚችል ከሆነ እና/ወይም በልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ላይ ማናቸውንም ተጨማሪዎች ወይም ማሻሻያዎች ያስፈልጉ እንደሆን፡፡<br><br>*ከጀርባ ይመልከቱ* |

*ከጀርባ ይመልከቱ*

* ማሳሰቢያ፡ የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ "የአካል ጉዳተኛ ልጆች" ትርጉም በዚህ መመሪያ የብቃት ክፍል ውስጥ ቀርቧል፡፡

| | |
|---|---|
| **ለማዘጋጀት የሚሆኑ ጠቃሚ ምክሮች**<br>*ትምህርት ቤትዎ እርስዎ ለሚያደርጉት አስተዋጽኦ ዋጋ ይሰጣል፡፡* | • የልጅዎን ጥንካሬና ድክመቶች ያንጸባርቁ፡፡<br>• የ IEP ሂደት ሪፖርቶች፣ የሪፖርት ካርዶች እና/ወይም ሌሎች የቅርብ ጊዜ ግምገማዎችን ይገምግሙ፡፡<br>• ማጋራት የሚፈልጉትን ማንኛውንም የግል ሪፖርቶችን ያዘጋጁና ያስገቡ፡፡<br>• ብቁነትን ወይም የልጅዎን የትምህርት ፍላጎቶች ለመወሰን ተጨማሪ ግምገማዎች ያስፈልጋሉ ብለው ያስቡ፡፡<br>• ተጨማሪ ግምገማዎች እንደሚያስፈልጉ ከተሰማዎት የሚያስፈልጉ ግምገማዎችን ይያዙና ስለፍላጎቱ (ቶቹ) ለመወያየት ዝግጁ ይሁኑ፡፡<br>• ለቤተሰብዎ ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮችና ለዚህ ስብሰባ የሚፈለጉትን ውጤቶች ግምት ውስጥ ያስገቡ፡፡ ሃሳቦችህን ለማደራጀት ለማገዝ የመወያያ ነጥቦችን ክፍል (ከታች) ይጠቀሙ፡፡<br>• በስብሰባው ላይ ለመጠየቅ የሚፈልጉትን ማንኛውንም ጥያቄዎች በጥያቄዎች ክፍል (ከታች) ውስጥ ይዘርዝሩ፡፡<br>• ለዚህ ስብሰባ እንዴት መዘጋጀት እንደሚችሉ ለመወያየት PRCን ያነጋግሩ፡፡ |
| **እንደ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የእኔ ሚና**<br>*እርስዎ በትምህርት ቡድኑ በእኩል የሚታዩና ጠቃሚ አባል ነዎት፡፡* | • በስብሰባው ላይ በንቃት ተሳትፎ ያድርጉ፡፡<br>• የእርስዎን ግብአት፣ ሃሳብና ማንኛውንም ስጋት ለማካፈል ምቾት ይሰማዎ፡፡<br>• ጥያቄዎችን እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ማብራሪያን ይጠይቁ፡፡<br><br>*ማሳሰቢያ፡ ትምህርት ቤቱ ተጨማሪ ግምገማዎችን ለማካሄድ እንዲችል የእርስዎ ፈቃድ እንደሚያስፈልግ ይወቁ፡፡ ይሁን እንጂ ትምህርት ቤቱ የእርስዎን ፈቃድ ለማግኘት ምክንያታዊ እርምጃዎችን ከወሰደና እርስዎ በዛ ላይ ምላሽ ካልሰጡ ትምህርት ቤቱ በግምገማዎች ሊቀጥልበት ይችላል፡፡* |

| የመወያያ ነጥቦች | ጥያቄዎች |
|---|---|
| | |

# የድጋሚ
# ግምገማ ስብሰባ

Arlington Public Schools

# የድጋሚ ግምገማ ስብሰባ

**የተማሪ ስም፡**______________________________________ **ቀን፡** ____________________

| | |
|---|---|
| የድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባ በጨረፍታ | **የድጋሚ ግምገማ ስብሰባ ምንድን ነው?**<br>ልጅዎ አሁንም የአካል ጉዳተኛ ልጅ መሆኑንና የልዩ ትምህርት እና/ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው መሆኑን ለማረጋገጥ ቢያንስ በየሶስት አመቱ ትምህርት ቤቱ ልጅዎን እንደገና መገምገም አለበት፡፡ ከድጋሚ ግምገማው ስብሰባ አስቀድሞ የቀጣይ ብቁነትን ለመወሰን ተጨማሪ ግምገማዎች (ምርመራ፣ ምልከታዎችና ሌሎች መረጃዎች) አስፈላጊነት ላይ ለመወሰን የድጋሚ ግምገማ እቅድ ስብሰባ ይካሄዳል፡፡<br><br>**ብዙውን ጊዜ በድጋሚ ግምገማ ስብሰባ ላይ የሚሳተፈው ማነው?**<br>ወላጅ/አሳዳጊ፣ ርእሰ መምህር/ረዳት ርእሰ መምህር/ወይም ተወካይ፣ የክፍል መምህር፣ የልዩ ትምህርት መምህር፣ ተዛማጅ አገልግሎት አቅራቢዎች፣ የልዩ ትምህርት አስተባባሪ (SEC)፣ ልጅዎ፣ አስፈላጊ ከሆነ እና/ወይም ሌሎች በትምህርት ቤቱ እና/ወይም በቤተሰቡ የተጋበዙ፡፡<br><br>**በምን ጉዳይ ላይ ውይይት ይደረጋል?**<br>• ቡድኑ ነባር መረጃዎችንና ሁሉንም የተጠናቀቁ ግምገማዎችን ይገመግማል፡፡<br>• ቡድኑ ልጅዎ እንደ "ትምህርቱ ላይ ተጽእኖ የሚኖረው አካል ጉዳተኛ ልጅ" መስፈርቶቹን ማሟላቱን የቀጠለ እንደሆን ለማረጋገጥ ይወያያል፡፡<br>• የቡድን አባላት በብቁነት ውሳኔው መስማማታቸውን ወይም አለመስማማታቸውን ይገልጻሉ፡፡<br><br>**የሚወሰነው ምንድን ነው?**<br>ቡድኑ ልጅዎ እንደ "አካል ጉዳተኛ ልጅ፣ በዚህም የተነሳ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው" መስፈርቱን ማሟላቱን ይቀጥል እንደሆነ ይወስናል፡፡ |
| **ለማዘጋጀት የሚሆኑ ጠቃሚ ምክሮች**<br>*ትምህርት ቤትዎ እርስዎ ለሚያደርጉት አስተዋጽኦ ዋጋ ይሰጣል፡፡* | • የልጅዎን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ያንጸባርቁ፡፡<br>• የ IEP ሂደት ሪፖርቶች፣ የሪፖርት ካርዶች እና/ወይም ሌሎች የቅርብ ጊዜ ግምገማዎች፡፡<br>• ለዚህ ስብሰባ የቤተሰብዎን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮችና የሚፈለጉትን ውጤቶች ግምት ውስጥ ያስገቡ፡፡ ሃሳቦችህን ለማደራጀት ለመርዳት ከዚህ በታች ያለውን "የመወያያ ነጥቦች" ክፍል ተጠቀም፡፡<br>• ለዚህ ስብሰባ እንዴት መዘጋጀት እንደሚችሉ ለመወያየት PRCን ያነጋግሩ፡፡ |
| **እንደ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የእኔ ሚና**<br>*እርስዎ በትምህርት ቡድኑ በእኩል የሚታዩና ጠቃሚ አባል ነዎት፡፡* | • በስብሰባው ላይ በንቃት ተሳትፎ ያድርጉ፡፡<br>• ሃሳብዎን፣ ግብአትዎንና ማንኛውንም የሚያሳስብዎትን ነገር ለማካፈል ምቾት ይሰማዎ፡፡<br>• ጥያቄዎችን እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ማብራሪያን ይጠይቁ፡፡<br>• አስፈላጊ ከሆነ የ IEP ስብሰባ መርሐግብር ያውጡ/ይጠይቁ፡፡<br><br>*ማሳሰቢያ፡ ትምህርት ቤቱ በብቁነት ላይ ውሳኔ ለመወሰን፣ በልጅዎ ብቁነት ላይ ማናቸውንም ለውጦችን ለማድረግ እና/ ወይም ብቁነትን እንዲያቋርጥ ለማድረግ እንዲቻል የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልጋል፡፡*<br><br>*ከጀርባ ይመልከቱ* |

| የመወያያ ነጥቦች | ጥያቄዎች |
| --- | --- |
| | |

# የቡድን ትብብር

# የቤተሰብ/የትምህርት ቤት ተሳትፎ እና ትብብር

ከተሞክሮ እና ከምርምር እንደምንገነዘበው የወላጅ/አሳዳጊ ተሳትፎ የተማሪው በትምህርት ቤት ስኬት ጠንካራ አመላካች ነው፡፡ እርስዎ የልጅዎ ኢጋዥ እና ቋሚ የልጅዎ የትምህርት ቡድን አባል ነዎት፡፡ የቡድኑ ውጤታማ አባል ለመሆን፣ አወንታዊ እና የትብብር አጋርነቶችን ለመገንባት የተወሰኑ ምክሮች እዚህ አሉ፡

***የጋራ ግቦችን እውቅና መስጠት:*** የእርስዎ ቡድን ልጅዎ ተገቢ ትምህርታዊ ፕሮግራም ማግኘቱን እንዲያረጋግጡ ጠቃሚ ግብ ያጋራዎታል፡፡ በዚሁ ግብ ዙሪያ በጋራ መስራት ጠቃሚ ነው፡፡

***ዝግጁ መሆን:*** የልዩ ትምህርት ስብሰባዎችን ለማዘጋጀት እና ሙብትዎንና ኃለፊነትዎን ለማወቅ አስተያየትዎን እና ግብዓትዎን ለማደራጀት በዚሁ መመሪያ ያሉትን ምንጮች ይገምግሟቸው፡፡ መረጃን ያጋሩ፡፡ የልጅዎን የትምህርት ፍላጎት ቡድንን ለማሳወቅ እንዲረዳዎ ስለልጅዎ ክህሎት፣ ጥንካሬ እና ድክመት ተገቢ የግል ሪፖርቶች ወይም ምሳሌዎች ቅጅውን ያቅርቡ፡፡ ከወላጅ የምንጭ ማእከል (PRC) የልጅዎ የትምህርት ቤት ቡድን እና ሌሎች ወላጆች ምግብ ወይም ሀሳብ ወይም አስተያየት ለመጠየቅ ምንም አያመንቱ፡፡

***ውጤታማ ተግባቦት:*** በጋራ ግቦች የተነሳሱ ተባባሪ ቡድኖች በሚዘጋጁበት ወቅት የቡድኑ ዓባላት እርስ በእርሳ መከባበር እና ዋጋ መስጠት፣ የእያንዳንዱ የቡድኑ አባል አስተዋጽኦ እውቅና መስጠትና የተለየ አተያይ እና አስተሳሰብ መቀበል፡፡ የቡድን ዓባላት ንቁ የማድመጥ ክህሎቶችን እንዲጠቀሙ አስፈላጊ ሲሆን ጥያቄዎችን እና ማብራሪያዎችን እንዲጠይቁ እንዲሁም በግልጽ እና በቀጥታ እንዲገናኙ ይበረታታሉ፡፡ የተግባቦት “ድልድዮች” የተወሰኑ ምሳሌዎችን ከታች ይመልከቱ፡

- አስደሳች ሀሳብ ነው፡፡ ስለዚሁ የበለጠ ሊነግሩን ይችላሉ፡፡
- ስለዚህ ለእኔ መስሎ የሚታየኝ...
- በአስተሳሰብዎ ደስተኛ ነኝ
- ይህ በትምህርት ቤት ውስጥ ምን እንደሚመስል ለማሳየት ሊመሩኝ ይችላሉ?
- በግልጽ አልገባኝም፡፡ ይህንን አስተሳሰብ ይበልጥ ሊያብራሩት ይችላሉ?
- በትክክል እርስዎን ተገንዝቤ ከሆነ የእርስዎ አቋም....
- የቤተሰባችን አስተሳሰብ ለመግለጽ ብሞክር እወዳለሁ...
- ጥቂቶቹ አማራጮች ምንድ ናቸው?
- ዛሬ ስለ ልጃችን ስለተነጋገርነው ጉዳይ ለመግለጽ ጥቂት ጊዜ እንዲኖረው ቤተሰቤን እደግፋለሁ፡፡
- ከ......መስማቱን እወዳለሁ
- አሁን ስለዚሁ ውሳኔ እርግጠኛ ካልሆንን የሚቀጥለው እርምጃ ምን ሊሆን ይችላል፡፡
- ይህንን በተጨማሪ እንድናወራ በመፍቀድህ አመሰግናለሁ፡፡

***ምስጋናን መግለጽ:*** የቡድን ባለደረቦችዎን አስተዋጽኦ ያመስግኑ እንዲሁም በጥሩ ሁኔታ ስለሚሰራው ጉዳይ አስተያየትዎን ያጋሩ፡፡ ስለልጅዎ እድገት እንዳስተዋሉ ሠራተኞቹ ማወቃቸውን ለማረጋገጥ ያለሰለ ማስገንዘቢያ ይላኩ፡፡

***ትኩረትዎን በተማሪው ላይ ያደርጉ:*** በጋራ በመስራት ሂደት የቡድኑ የተጋሩት የጋራ ግብ ......የልጅዎን በጎ ውጤት መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ በልጁ ላይ ትኩረትና ኢላማ ያደረገ ንግግር መኖር ወደ ምርታማ እና ፍሬማ ውጤት ያመራል፡፡ መፍትሄ አዋቂ ይሁን፡፡ ቡድንዎ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻለ ላለመግባባት በማክበር ይስማሙ፡፡ እንዲሁም ስለሚቀጥለው እርምጃ ይጠይቁ፡፡ መረጃን ከ PRC ማግኘት የሚችሉ ሲሆን VDOE ደግሞ አለግባባቶችን በመፍታት ሂደት ቡድኖቹን የሚያግዝበት መመሪያ በ [http://www.doe.virginia.gov/special_ed/resolving_disputes/](http://www.doe.virginia.gov/special_ed/resolving_disputes/) አለው፡፡

***ስኬትን ማክበር:*** የእርስዎ ልጅ ስኬት ለመላው የቡድኑ ዓባላት አስደሳች ነው፡፡ ልጅዎ ተከታታይ ድጋፍ የሚያስፈልግበት ነጥብ ላይ ትኩረት ማድረግ ጠቃሚ ቢሆንም በቡድን ስብሰባ ወቅት ስለ እድገት፣ አካላዊ ለውጥና አዲስ ስኬት መነሳቱንና መገለጹን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡

# የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች

## የተማሪ አገልግሎት ክፍልና የልዩ ትምህርት ልዩ ትምህርት ቢሮ

### የግንኙነት ፍሰት ቻርት

**የቤተሰብ የመጀመሪያ ግንኙነት**

የተማሪ መምህር
ወይም
ጉዳዩን የያዘው

የትምህርት ቤት ርእሰ መምህር

የተገዢነት አስተባባሪ

የማማከር ተቆጣጣሪ

የልዩ ፕሮግራሞች ተቆጣጣሪ

የተማሪ አገልግሎት ዳይሬክተር

የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር

ረዳት የበላይ ተቆጣጣሪ፣ የተማሪዎች አገልግሎት መምሪያና ልዩ ትምህርት

ተቆጣጣሪ

የትምህርት ቤት ቦርድ

**ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮችን መፍታትና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፡**

ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረገ የልዩ ትምህርት አስተባባሪ (SEC)

ልዩ ባለሙያዎች (የኦቲዝምልዩ ባለሙያዎች፣ የባህሪ ልዩ ባለሙያዎች፣ የትምህርት ልዩ ባለሙያዎች፣ ሌሎች)

የተማሪ አገልግሎት ሰራተኞች (አማካሪዎች፣ የስነልቦና ሃኪሞች፣ ማህበራዊ ሰራተኞች)

የወላጅ መገልገያ ማእከል

ሌሎች APS ክፍሎች፡
- መመሪያ
- መጓጓዣ
- ሰራተኞች

PACER CENTER
**ACTION**
INFORMATION SHEETS

# በወላጅ-ትምህርት ቤት አጋርነት ውስጥ የወላጅ የስኬት ቁልፎች

## ወላጆች እንደ የትምህርት ቤት አጋሮች

የተለያዩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በአንድ የጋራ ግብ ላይ ለመስራት አንድ ላይ ሲገናኙ አጋርነት የሚሰረታል። ከግቡ በስኬት ለመድረስ የጋራ ትብብር እና ኃላፊነት መጋራትን ያስፈልገዋል። በተለያዩ መንገዶች በሚከናወንበት ጊዜ የግለሰብና የስራ አጋርነትን ለማርካት የሚንጠቀምባቸው መርሆች በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው።

እንደ ወላጅ እርስዎ የልጅዎ የመጀመሪያው እና በጣም አስፈላጊ መምህር ነዎት። የእርስዎ ልጅ ትምህርት ቤት በሚገባበት ጊዜ ሁለታችሁም ትርፋማ እና የረጅም ጊዜ ጥምረትን ተስፋ የምታደርጉበት እርስዎ እና ትምህርት ቤቱ አጋሮች የምትሆኑበት ነው።

በዚሁ ጠቃሚ አውድ የጋራ ግቡ የልጅዎን ስኬታማ እድገትና የሚሰንቀው ትምህርት ነው። በአመታት የተከናወኑ ጥናቶች ብዙ ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ላይ ተሳታፊ መሆናቸው ልጁም በትምህርት ቤትም ሆነ በህይወት መንገድ የተሻለ ስኬታማ እንደሚሆኑ ያሳያል። በወላጅ-ትምህርት ቤት አጋርነት ውስጥ አጋሮችን በመምረጥ ሂደት ለምርጫ መጠነኛ አማራጭ አለ። ይሁንና አጋሮች በጎ አጋርነትን የሚያሳድግን መንገድ እንዲያስቡ እና እንዲንቀሳቀሱ ይመርጣሉ። ውጤታማ የሆነ የወላጅ-ትምህርት ቤት አጋርነት ለዋና ተጠቃሚው ለሆነው - ለልጅዎ ትልቅ ትርፍ ያስገኛል።

PARENT LEADERSHIP

## የአጋርነት አስፈላጊ ነገሮች

### መልካም ተግባቦት

- ለልጅዎ መምህራን፣ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር እንዲሁም ሌሎች የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ራስዎን ያስተዋዉቁ። የክፍት ወይም ሌላ "ወደ ትምህርት ቤት መመለስ" ዝግጅት አጭር እና ግለሰባዊ ግንኑነት ለመፍጠር እጅግ በጣም ጥሩ ጊዜ ነው። እንዲሁም በቀላሉ እጅዎን በሰላምታ በመዘርጋት "ሃይ እኔ የጂሚ እናት ነኝ፣ በዘንድሮው አመት ከእናንተ ጋር በአጋርነት ለመስራት ተስፋ አደርጋለሁኝ" የሚል ቃል ለወደፊቱ ተግባቦት በጎ ዜማ/ስሜት ሊፈጥር ይችላል።
- ከዝቅተኛ የጊዜ አጠቃቀም የተነሳ ብዙ ጊዜ የተሳሳተ ተግባቦት ሊከሰት የሚችል እንደሚሆኑ በሠራተኞች ለመነጋር ጊዜው ተገቢ መሆኑን ማወቁ ጠቃሚ ነው። እንደ አጠቃላይ መመሪያ ተማሪዎች በተገኙበት ማንኛውም ጊዜ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ከአንድ ወይም ከሁለት ደቂቃ በላይ ለወላጆች ትኩረት በመስጠት ሀሳባቸውን መበታተን የለባቸውም።

  ግለሰባዊ ግንኙነት የተፈለገ እንደሆነ የሚገናኙበትን እቅድ ማውጣት። በስልክ እየተገናኙ ከሆነም መምህራን የድምጽ መልእክታቸውን በማጣራት ጊዚያውን መገደብ እንዳለባቸው ዘወትር ማስታወስ ያስፈልጋል። መምህራን በተመደቡበት "የዝግጅት ጊዜ" ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ይመለሳሉ ወይም ጥሪዎችን ይቀበላሉ። አስቸኳይ ፍላጎት ያለዎት እንደሆነም የእርስዎን መልእክት እንድትጽፍና በቀጥታ ለመምህሩ እንድታደርስ የትምህርት ቤቱን ጻሀፊ ይጠይቁ።
- ከትምህርት ቤቱ ሠራተኛ መምህራን ጋር በመገናኘት ምርጥ መንገዶችን ማፈላለግ። የተወሰኑ ግለሰቦች የስልክ ጥሪውን የሚመርጡ ሲሆን ሌሎቹ ለኢሜል ወይም የጹሁፍ ማስታወሻ ምላሽ የሚሰጡ ናቸው።
  የተግባቦቱ ዓላማ ስልቱን የሚወስን መሆን አለበት። ለምሳሌ ምንም እንኳን ኢሜል ፈጣን እና ውጤታማ የመልእክት ዜዴ ቢሆንም እንዲሁም በቀላሉ በተሳሳተ መልኩ ሊተጠረጎም ይችላል። የኢሜል መገናኛዎች በጣም አጭርና እብጭን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይሞክሩ። ስሜቶችን በአካል ወይም በስልክ አማካኝነት በቃላት ሊገልጿቸው ይችላሉ።
- ከእርስዎ ጋር የሚገናኙበትን የሚመች ሰዓትና ስልት ለትምህርት ቤቱ ይስጡ። ማንኛውም ዓይነት ለውጥ በሚኖሩበት ጊዜ የሚገኙበት ወቅታዊ መረጃ ያስቀምጡ። ለትምህርት ቤቱ ተግባቦቶች በተቻለ ፍጥነት አሟልተው ይመልሱ።
- የትምህርት ቤቱን ማስታወሻዎች፣ ጋዜጦች ወይም ሌላ ተግባቦቶች በየቀኑ የልጅዎን የጀርባ ቦርሳ የትምህርት ቤቱንና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ድህረ ገጽ ተደራሽ የሚሆንበትን መንገድ ማፈላለግና ለወቅታዊ መረጃ በየጊዜው ይመልከቱ።
- እንግሊዝኛ ለእርስቆ ሁለተኛ ቋንቋ ከሆነ መረጃን በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ እንዲሰጥዎ ይጠይቁ፡ በትምህርት ቤት የልጅዎን ትምህርት ክንውን ወይም ባህሪ ሊጎዳ የሚችል ቤቱ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ክስተት መረጃውን ማጋራት አለበት። ለምሳሌ አዲስ ወንድም/እህት መወለደ፣ የወላጅ መታመም ወይም የቅርብ ቤተሰብ ሞት የመሳሰሉ የልጅዎን ትኩረት የመስጠት ችሎታ ላይ ጊዜአዊ ተጽእኖ ሊኖራቸው ይችላል።

PACER CENTER
CHAMPIONS FOR CHILDREN WITH DISABILITIES
8161 Normandale Blvd
Minneapolis, MN 55437-1044
952.838.9000
952.838.0190 TTY
952.838.0199 fax
PACER@PACER.org
www.PACER.org

ስለጁ ስለዚሁ ሁኔታ የሚያውቅ ከሆነ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ፈተናዎችን ለማስተላለፍ፣ የቤት ሥራ እንዲያስተካክሉ ወይም ተጨማሪ ድጋፍ ለመስጠት ያስችላል፡፡

- ጠቃሚ መረጃ በጹሁፍ መድረስ አለበት፡፡
- ሲከፋ ወይም ግራ ሲጋባ፣ የክስ መግለጫዎችን ከመናገር ይልቅ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡ ሊሆን የሚችለው የመረጃ ገደብ መሰረት ያደረገ አጣዳፊ ውሳኔ ከመስጠት ይቆጠቡ፡፡ እርስዎ የሚያውቋቸውን ቃላት በመጠቀም ነገሮችን እንዲያብራሩ የትምህርት ቤቱን ሰራተኞች ይጠይቁ፡፡
- የድምጾችን ቅላጼ፣ አካላዊ ወይም የፊታችን አገላለጽ እንዲሁም አካላዊ ቋንቋ ከቃላት በላይ ጎልተው እንደሚናገሩ ያስታውሱ፡፡
- ጥሩ አድማጭ ይሁኑ፡፡ ሙሉ እና የተሟላ ትኩረት ይስጡ፡፡ ለማቋረጥ መሞከር የለብዎትም፡፡ ሌላኛው ግለሰብ እየተናገረ ሳለ ምላሽዎን በማዘጋጀት መጀመር የለብዎትም፡፡
- አስተያየቶችን እንደ አስተያየት ደረጃ መስጠት፡፡ ማንኛውም ሰው ከመሞገት ይልቅ አንድን ሀሳብ እንደ ጭብጥ ከጠቀሰ ይህንን የሚደግፍ ዳታውን (ተጨባጭ መረጃውን) ይጠይቁ፡፡
- በተቻለ መጠን "እኛ" የሚለውን ቋንቋ ይጠቀሙ፡፡ የልጅዎ ትምህርት የቡድን ጥረት ውጤት ነው፡፡ "አንተ/አንቺ" የሚል ቋንቋ መጠቀም ይህንን የሚሰማው/የምትሰማው ግለሰብ ተባባሪ ከሆን ይልቅ የንዴት ስሜት ውስጥ ሊከት ይችላል፡፡

## ታማኝነት፣ ተጠያቂነት እና እምነት

- የተሟላ እና ትክክለኛ መረጃ ይስጡ እንዲሁም ይጠብቁ፡፡
- ቁርጠኝነትዎን ይቀጥሉበት፡፡ የትምህርት ቤቱ ጉባኤ እና የስብሰባ ቀን በጊዜ መቆጠሪያዎ ላይ በማስታወሻነት በመያዝ በየጊዜው ይመልከቱ፡፡ በስብሰባው ወቅት መገመት የማይችሉ ከሆነ አስቀድመው በመደወል ደግመው ቀጠሮ ይያዙ፡፡
- ሚስጥራዊ መረጃዎችን በሚስጥራዊነታቸው መጠበቅ፡፡ የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች መረጃን በመስጠት የሚያምኑ ከሆነ መረጃውን በአግባቡ በመጠቀም የተጣለብዎነት እምነት ያክብሩ፡፡
- የተሟላ እምነት በጊዜ ሂደት ይዳብራል፡፡ የመጠራጠርን ጥቅም ለሰዎች ይስጡ፡፡ ራሳቸው ካላረጋገጡ በስተቀር እነሱ ቡድንዎ ውስጥ እንዳሉ አድርገው ይንቀሳቀሱ፡፡

## መከባበር

- ከእነሱ የሚጠብቁትን እና እርስዎን እንዲያከብሩ በሚፈልጉት መጠን ልክ ሌሎቹን በተመሳሳይ ደረጃ ማክበር፡፡
- ትምህርት ቤታቸውን እና መምህራንን በተመለከት እርስዎ ያለዎትን አመለካከት ልጅዎ ከውስጡ የሚያስረጹው መሆኑን ዘወትር ያስታውሱ፡፡ ልጅዎ ስለትምርት ቤታቸው እና መምህርዎቻቸው የሚሰማቸው ስሜት በትምህርታዊ ሂደታቸው ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡
- በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እንደ አባልና ኢጋር ለእርስዎ ልጅ ግለሰባዊ ፍላጎቶች ሙብትን እየተከራከሩ ቢሆንም የሌሎችን ተማሪዎች እና ሠራተኛ አባላት የተለያዩ ፍላጎቶችን እና አሳሳቢ ጉዳዮችን ያክበሩ፡፡

## የባህል ተሳትፎ

- እንደ ወላጅ፣ ለወላጅ -ትምህርት ቤት ኢጋርነት የእርስዎ የላቀ ጠቃሚ አስጽኦ ልጅዎን ለትምህርት ቤት እንዲዘጋጅት እና የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማጠናከር እርስዎ ከትምህርት ቤት ውጪ የሚያደርጉት ድጋፍ ነው፡፡
- እርስዎ ማድረግ የሚወዱትን፣ በጥሩ ሁኔታ የሚያደርጉትን እንዲሁም ያለዎትን ጊዜ መሰረት በማድረግ ለልጅዎ የመማሪያ ክፍል ወይም ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አስተዋጽኦ የሚያበረኩቱበትን መንገድ ያፈላልጉ፡፡ ለምሳሌ ካሜራ ካለዎትና ፎቶ ግራፍ ማንሳት የሚያስፈልገዎት ከሆነ በትምህርት ቤት ዝግጅት በፈቃድዎ ፎቶ ግራፎችን ማንሳት፡፡ ለአዘጋጅነት የተወለዱ/አዘጋጅነት የሚያሳካለት አይነት ሰው ከሆኑ የመማሪያ ክፍል ፓርቲን ለማቀድ በኮሚቴ ያገልግሉ፡፡
- በትምህርት ቤት-አቀፍ ዝግጅቶች የበኩልዎን ድጋፍ ለማድረግ ያሉትን እድሎች ይጠቀሙባቸው፡፡ በጎ ፈቃደኝነት ከሌሎች ወላጆች፣ ተማሪዎች እና ሠራተኛ አባላት ጋር የሚገናኙበትን እና በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ እንደተካተቱ እንዲሰማዎት እድል ይሰጣል፡፡ ለልጅዎ መልካም አርዓያነትዎ ከውስጡ እንዲኖር በማድረግ እርስዎ ለትምህርት ቤቱ የሰጡትን ዋጋ አስመልክቶ ጠንካራ መልእክት የሚያስተላልፉበት ይሆናል፡፡
- በአካል ተገኝተው መሳተፍ የማችሉ ቢሆንም እንኳን የበኩልዎን አስተዋጽኦ የማድረግ ፍላጎት እንዳለዎት ይግለጹ፡፡ የሥራ ሰዓትዎ በትምህርት ቤቱ በትምህርት ሰዓታት በጎ ፍቃደኛ ለመሆን አዳጋች ከሆነ ከቤት ውስጥ አስተዋሽ ጥሪ እንዲኖር ማድረግ እና የስም ምልክቶችን/ታጎችን መተው ወይም ቤቱ ውስጥ ሆኖ ሊሰሩ በሚችሉ ሌሎች ፕሮጀክቶች መስራት እና ከልጅዎ ጋር ወደ ትምህርት ቤት መመለስ፡፡
- በትምህርት ቤቱ ሳይት ምክር ቤት፣ የወላጅ ተሳትፎ ኮሚቴ ወይም ሌላ ትምህርት ቤት ወይም የዲስትሪክትው አማካሪ ኮሚቴ በመሆን ማገልገልን ከግምት ያስገቡ የወላጅ ግብዓት በውሳኔ አሰጣጥና ፖሊሲ ደረጃ ጠቃሚ ነው፡፡ የወላጅ አባላት ስለ ቤተሰቦቻው ፍላጎቶች፣ ጥቅሞቻቸውንና የሚያሳስባቸውን ጉዳይ መግለጽ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የአካል ጉዳተኛ ልጅ ያላቸው ቤተሰቦች እይታ ከሚፈለገው በታች የተወከለ በመሆኑ በልዩ ሁኔታ ያስፈልጋል፡፡ አባላት ለሥራ ኃላፊነት ስለሚያመለክቱበት መንገድ ዳይሬክተሩን ይጠይቃል፡፡ አብዛኞቹ ስብሰባዎች ለህዝቡ ክፍት እንደመሆናቸው እርስዎ ለመቀጠል የሚፈልጉት አንዱ እድል ከሆነ መወሰንዎ በፊት እንደ ጎብኚ መገኘት ይችላሉ፡፡

## የእያንዳንዱ ወላጅ አስተዋጽኦን ማመስገን

- ግለሰቦች ጥሩ ሥራ ሲሰሩ ሰዎች እንዲያዉቁት ማድረግ፡፡ የልጁን በእርስዎ ከአጭር ማስታወሻ ጋር ቤት ውስጥ የተሰራው ካርድ ለመምህር፣ ነርስ ወይም ሌላ ሠራተኛ ግለሰብ የላቀ አበረታችና አነሳሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ምስጋናን የሚገልጽ አጭር ኢሜል ወይም የድምጽ መልእክት ለመተው አንድ ወይም ሁለት ደቂቃ ብቻ ይወስዳል፡፡ ይህ ለሠራተኛው ግለሰብ ተቆጣጣሪ በጎ መልክእት መላክ የተለየ ውጤት ሊኖረው ይችላል፡፡

## ሁለተኛው እድል እና አዲስ ጅምር

- የተፈጸመ እንደሆነ በአስቸኳ ሙሉ በሙሉ እንዲፈቱ መሞከር፡፡ ቀጥሎ የመልእክት ቦርዱን በማጽዳት ወደፊት ያስተላልፉ፡፡ የዚህ ግብ በልጅዎት ሴከታማ ትምህርት ላይ በዚህ ኢጋርነት ውስጥ ያለውን ኃይል እና ጥረት ይጠቁማል፡፡
- ያለፉ ጉዳዮች ወይም ግጭቶች ቢኖሩም እንኳን በእያንዳንዱ አዲስ የትምህርት አመት ለአዲስ ጅምር እንደ መልካም እድል ለመጠቀም መሞከር፡፡

## የአጋርነት ተግዳሮቶች

### የተለያዩ የሚጠብቋቸው ነገሮች፣ እይታና ሀሳቦች

- የጋብቻ አጋርነት ላይ ሁለቱም ሰዎች ተመሳሳይ ከሆኑ ቀጥሎ ከሁለቱም አንዳቸው አያስፈልጉም ይላል! አጋርነትን ይሄን ያህል አዳጋች የሚያደርገው መሰረታዊ ትልቁ ልዩነት የግንኙነቱ ጥንካሬ ልሆን እንደሚችል ነው። ልጆች እና ፍላጎቶቻቸው የተወሳሰቡ እና ከአንድ በሆነ መንገዶች መጨረሻ ላይ ተፈተው የማየት ጥቅም ነው።
- አካርነት እያንዳንዱ ግለሰብ ለውይይት ባቀረበው ሀሳብ መሰረት የሚመሰረት ነው። በወላጅ፣ ትምህርት ቤት አጋርነት እርስዎ እንደወላጅ በልጅዎ ላይ ኤክስፐርት/ባለሙያ ነዎት። የሁሉም ትምህርት ቤት ሠራተኛ አጋር የራሱ ወይም የራሷ የተለየ ትምህርታዊ እውቀት ወይም ተሞክሮ ይኖረዋል/ይኖራታል። እያንዳንዱ የአንድ ልጅ እድገታዊና ትምህርታዊ ፍላጎቶችን ይበልጥ ለማማላት ከሌላው ይማራል።

### እኩል ያሆነ እውቀት ወይም ስልጣን

- ወላጆች ስለልጆቻቸው የተሻለ እውቀት እያላቸው በአጠቃላይ ስለትምህርታዊ ስርዓት እና በተለይ ስለ ልዩ ትምህርት እውቀት ላይ ስንመጣ ብዙ ጊዜ ተጠቃሚ አይሆንም። ወላጆች ስለሚኖራው መብትና ሃላፊነት እንዲሁም ስርዓቱ እንዴት እንደሚሰራ መገንዘባቸው ጠቃሚ ነው። የትምህርት ቤቱን ዲክትሪክ እና/ወይም የአካቢውን ትምህት ቤት ወላጅ ሀንድ ቡክ ጠይቀው ያንብቡ። ለአካል ጉዳተኛ ልጆች ወላጆች መብቶች እና ግዴታዎች ነፃ የመመሪያ መጽሃፍ ፣ ***Parents Can Be the key*** ፣ ከ PACER ማእከል፣ እንዲሁም ሌሎች ብዙ ለወላጆች ተስማሚ የሆኑ ቁሳቁሶች እና ግብአቶች ይገኛል።

### የሚናዎች እና ኃላፊነቶች የተሳሳተ ግንዛቤ

- ብዙ ጊዜ በአጋርነት ውስጥ ስለ እያንዳንዱ አጋር ሚና እና ለተለያዩ ሥራዎች ኃላፊው ማን እንደሆነ የተሳሳተ ግንዛቤ እና አዳጋችነት ሊስተዋል ይችላል። ስለተለያዩ ጉዳዎች ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው የትኛው ሠራተኛ አባል እንደሆነ ለማወቅ ጥያቄዎችን ይጠይቁ። "የትእዛዝ ሰንሰለት" የቱ እንደሆነ ማግኘትና የተሻለ ተገቢነት ያለው ሰው የለዎትን ጥያቄ ወይም አሳሰቢ ጉዳይ እንዲደርሰው ይሞክሩ።
- በልዩ ትምህርት ጉዳይ ስንመጣ  ስለተማሪው ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው ሰው የለም። ውሳኔዎች ወልጅን የሚያካትት በIEP ቡድን በሚደረስ ስምምነት መሆን አለበት፡

### ግጭት

- የማይስማማሙ መሆን ሳያስፈልግ ላለመስማማት እቅድ ያድርጉ። ግለሰቡን ከችግሩ ይለዩት። በአብዛኛው አለመስማማቱን/ግጩቱ ካለፈ ከረጅም ጊዜ በኋላ ከትምህርት ቤቱ ጋር ግንኙነት የሚኖራችሁ እርስዎን እና ልጅዎ ናችሁ። ጉልህ አለመስማማት ቢኖርም እንኳን ግንኙነቱን መጠበቁ ለልጅዎ ምርጥ ጥቅም ሲባል ነው።
- የአዋቂዎችን ጉዳዮች በአዋቂዎች መካከል እንዲጠበቁ፣ ልጆች በግጭቱ በመካተታቸው በፍጹም ተጠቃሚ የማያደርጋቸው ግጭቱ ወይም አለመስማማቱ ካለፈ ከረጅም ጊዜ በኋላ አሉታዊ ተጽእኖ ሊሰማው ይችላል።
- ከአንድ የተለየ ሠራተኛ ግለሰብ ተከታታይ እና ዘላቂ የሆነ ግጭት ያላቸው እና ጉዳዮችን በመካከላችሁ በቀጥታ በስኬት መፍታት ካልቻላችሁ ከቅርብ ኃላፊያቸው ጋር ለመነጋገር ይጠይቁ።
- ችግሩን በመግለጽ እና በመሰንጠቅ ያላችሁን ጉልበት በመወያየት ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ በሚቻል ማስተካከያ ወይም የመፍትሄ ሀሳብ ላይ ማተኮር።
- አሳሳቢ የሆነው ጉዳይ የምትዩዙበት ስልት ላይ አለመስማማት በሚኖርበት ጊዜ ለሙከራ ያህል የሆነን አዲስ ነገር ለመሞከር ፈቃደኛ ይሁኑ። አዲስ እቅድ መቀጠል እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ለመወሰን ሙከራ በሚደረግበት ወቅት መረጃ ለመሰብሰብ እቅድ መኖሩን እርግጠኛ መሆን።

ጉዳዩን በጥሩ ሁኔታ በትክክል በሚፈታበት ጊዜ ግጭት ለልጅዎ በአጠቃላይ ወደ በጎ ውጤት ሊያመራ ይችላል። በአጋርነት በሚሰሩበት ጊዜ አዳጋች ሊሆን እንዲሁም ሊያስመሰግን የሚችል ይሆናል። አጋሮች አዳዲስ እይታዎችን ማግኘትና አዳዲስ ክህሎቶችን መማር ይችላሉ። በጋራ ትብብር እና ሃላፊነቶችን በመጋራት አማካኝነት የወላጅ-ትምህርት ቤት አጋርነት ልጅዎ ለትምህርትና በህይወት ሴኬታማ መሆን የሚያስችሉትን አጠቃላይ ግቦችን ማሟላት ይችላል።

PACER CENTER
ACTION
INFORMATION SHEETS

# በልዩ የትምህርት ሂደት ውስጥ ተግባቦት

ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባዎችና ሌሎች የትምህርት ቤት ስብሰባዎች ስለ ልጁ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ጠቃሚ አካላት ናቸው፡፡ የወላጅ ኃላፊነት ስምምነትን ከመስጠትና መግለጫዎችን ከመቀበል በላይ ይሻገራል፡፡ ጥያቄችን መጠየቅ ጉዳዎችን ለውይይት ማቅረብ፣ መረጃ መሰብሰብ እና መጥቦችን ወይም ጉዳዮችን ማብራራት በሙሉ የአንድ ወላጅ ሚና አካል ናቸው፡፡

ወላጆች በልዩ የትምህርት ስብሰባ ወቅት ማንኛውም ሰው ይዘው መምጣት ይችላሉ፡፡ ልጁን ለመጥቀም ሁሉም ተሳታፊዎች በጋራ ይሰራሉ፡፡ አንድ ወላጅ የቡድኑ በጣም ጠቃሚ አባል ነው፡፡

እንከን አልባ ተግባቦት ስለ ልጁ ተምህርታዊ ፕሮግራም ግንዛቤውን ማመንጨትና ውጤታማ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልገውን በሙሉ ባለሙያውን እና ወላጅን መደገፍ የሚል ሁለት መንገድ አለው፡፡ ትርጉም ያለው ተግባቦት ለማጠናከር ወላጆች ማድረግ የሚችሉት፡

- ትኩረቱ ልጁ ላይ መቆየቱን ማረጋገጥ፡፡
- ዝግጁ ይሁኑ፡፡ የሚወያዩባቸውን ጠቃሚ ነጥቦች እና የሚጠይቁአቸውን ጥያቄዎች በቅድሚያ ማወቅ፡፡
- ያዳምጡ፡፡ ማድመጥ ስለ ልጅዎ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያግዝዎ ሲሆን ሌላ እይታን ለመገንዘብ ያግዝዎታል፡፡

- ዝግጁ ይሁኑ፡፡ የሚወያዩባቸውን ጠቃሚ ነጥቦች እና የሚጠይቁአቸውን ጥያቄዎች በቅድሚያ ማወቅ፡፡
- ያዳምጡ፡፡ ማድመጥ ስለ ልጅዎ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያግዝዎ ሲሆን ሌላ እይታን ለመገንዘብ ያግዝዎታል፡፡
- ጉዳዎን በግለጽ ይጥቀሱ፡፡ በቀናነት በቀጥተኛ መንገድ ይነጋገሩ፡፡
- ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡ ጥያዎቆችን መጠየቅ አንድ ነጥብ ለማብራራት ውጤታማ መንገድ እንዲሆንና የተግባቦት መስመር ግልጽነትን እንዲጠብቅ ያስችላል፡፡
- አስተያየትዎና ጥያቄዎት የተሻለ ሊፈታቸው ወይም ሊመልሳቸው ወደ ሚችለው ግለሰብ መመራት አለባቸው፡፡
- መጀመሪያ ላይ ካልተደመጡ የሚያሳስብዎትን ጉዳይ በድጋሚ ይግለጹ፡፡
- በራስዎ ይተማመኑ፡፡ አንድ ወላጅ ጥያቆችን በመጠየቅ ወይም ለልጁ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ አጽኖ ሰጥቶ በመናገሩ ሀፍረት ወይም መሸማቀቅ ሊሰማው አይገባም፡፡ ይህ የእርስዎ ሚና እና የእርስዎ መብት ነው፡፡
- በጋራ መስራት፡፡ እናንተም ሆነ ባለሙያዎቹ እነዚህን መልሶ በሙሉ እንደሌላችሁ አስታውሱ፡፡ መፍትሄዎችን ለማግኘት እንደ ቡድን በጋራ መስራት፡፡ ስብሰባ ላይ የተገኘው ሰው በሙሉ ለልጁ ተገቢ ትምህርታዊ ፕሮግራም እንዲሰጥለት-ተመሳሳይ ግብ አለው፡፡

የእንከል አልባ ተግባቦት ቁልፍ በልጁ ትምህርታዊ ፕሮግራም እቅድ ላይ በንቃት ለመሳተፍ ዝግጅትና ፍቃደኝነት ነው፡፡

PACER CENTER
CHAMPIONS FOR CHILDREN WITH DISABILITIES
8161 Normandale Blvd
Minneapolis, MN 55437-1044
952.838.9000
952.838.0190 TTY
952.838.0199 fax
PACER@PACER.org
www.PACER.org

# ቁልፍ እውቂያዎች

# የእኛ ቡድን

ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ: ______________________ ተማሪ: ______________________

ትምህርት ቤት: ______________________ የትምህርት ዘመን: ______________________

| የትምህርት አባል | ስም | ኢሜል | ስልክ |
|---|---|---|---|
| ጉዳዩን የያዘው/ተቆጣጣሪ/ የልዩ ትምህርት መምህር(ሮች) | | | |
| የልዩ ትምህርት ረዳት(ቶች)/ ፓራፕሮፌሽናል(ሎች) | | | |
| አጠቃላይ ትምህርት መምህር(ሮች) | | | |
| የንግግርና የቋንቋ ፓቶሎጂስት | | | |
| የትምህርት ቤት አማካሪ | | | |
| የእንቅስቃሴ ሐኪም | | | |
| የሽግግር አስተባባሪ (ሁለተኛ) | | | |
| ስፔሻሊስቶች (ኦቲዝም፣ ኦዲዮሎጂ፣ እይታ፣ መስማት፣ ባህሪ፣ ኢጋዥ ቴክኖሎጂ፣ ወዘተ) | | | |
| ርእሰ መምህር/ረዳት ርእሰ መምህር/ተወካዮች | | | |
| የልዩ ትምህርት አስተባባሪ (SEC) | | | |
| ነርስ/ክሊኒክ ረዳት | | | |
| የትምህርት ቤት የስነልቦና ሐኪም | | | |
| የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ | | | |

| ተጨማሪ የቡድን አባላት* | ስም | ኢሜል | ስልክ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

* ቡድኑ ኦዲዮሎጂስት፣ የመስማት ችግር ያለበት መምህር፣ የእይታ ባለሙያ፣ የስራ አሰልጣኝ፣ የሰውነት ሐኪም (ቴራፒስት)፣ የተለያየ ኤጀንሲ ተወካዮችና ሌሎችንም ሊያካትት ይችላል፡፡

## የልዩ ትምህርት የወላጅ ግንኙነቶች

ከትምህርት ቤትዎ ቡድን አባላት በተጨማሪ፣ የወላጅ መገልገያ ማእከል (PRC) እና የአርሊንግተን ልዩ ትምህርት የወላጅ መምህር ማህበር (SEPTA) እንደ ልዩ ትምህርት የወላጅ መገናኛ ሆነው እንዲያገለግሉ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ቢያንስ 1-2 ወላጆችን ለመለየት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የወላጅ ማገናኛዎች ልጅ ያላቸው የልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ ወላጆች ሲሆኑ በPRC፣ SEPTA፣ የአካባቢ ትምህርት ቤት PTAs እና ቤተሰቦች መካከል ለቤተሰቦች እና የመረጃ ማስተላለፊያዎች የመገናኛ ነጥቦች ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የማገናኛ አድራሻ መረጃ በ www.apsva.us/prc/parentliaisons/ ላይ ሊታይ ይችላል፡፡

| የልዩ ትምህርት የወላጅ ግንኙነት(ቶች) | ስም | ኢሜል | ስልክ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |

# ሽግግሮች

# ቁልፍ ሽግግር እና እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል

ከልጅነት ጊዜ ጀምሮ እስከ ወጣትነት ባሉ የጊዜ ሂደቶች ሁሉም ልጆች በበርካታ ሽግግር ደረጃዎች ያልፋሉ፡፡ ሽግግር አንድ ልጅ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላኛው ክፍል ሲዛወር በእያመቱ የሚከሰት እና እንዲሁም ልጆች ከአንዱ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም ወደ ሌላው ሲዛወሩ ይከሰታል፡፡

አልፎ አልፎ እነዚህ የሽግግረ ሂደቶች ለተማሪዎችና ወላጆቻቸው ያለመረጋጋትና ጭንቀት እንደሚያስከትልባቸው እናውቃለን፡፡ የታቀዱ ሽግግሮች ከአንድ ፕሮግራም፣ ክፍል እና/ወይም ትምህርት ቤት ወደ ሌላው በቀላሉ እንዲዛወሩ ያስችላል፡፡ ለሽግግር የሚዘጋጁ እንደሆነ ልጅዎ ወደ አዲስ አካባቢ የሚሸጋገር እንደመሆኑ ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ለመለየት እንዲሁም ስለ ፕሮግራም አማራጭ ራስዎን ለማስተማር ከልጅዎ የትምህርታዊ ቡድን በንቃትና በቅርበት መስራት ያስፈልጋል፡፡

የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) በየአመቱ መዋለ ህጻናትን፣ መካከለኛ ትምህርት ቤቶችን፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የኮሌጅ መረጃ ምሽቶችን ያስተናግዳል፡፡ እነዚህ ግዙፍ ስብስቦች በሁሉም ቤተሰቦች ስለ ትምህርት ቤት እና ፕሮግራም አማረጭ መረጃ ለመስጠት የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ከAPS የመረጃ ልውውጦች በተጨማሪ የወላጅ የምንጭ ማእከል (PRC) የሚገኙ ባለሙያዎች  በተለይ  ከአካል ጉዳተኛ ልጆች ጋር የተያያዙ በርካታ ሽግግሮች መረጃን ማበርከት እና በሽግግር ሂደት ወቅት ስለውሳኔ አሰጣጥ መረጃ ለማግኘት ቤተሰቦችን ከምንጭ እና ከወላጅ ተወካዮች ጋር ለማገኛት ደስተኞች ናቸው፡፡

በአርሊንግተን የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ዘላቂ አገልግሎት የሚያበረክቱ ሲሆን በተጨማሪ ከቅደመ መዋለ ህጻናት (Pre-K) እስከ 22 ዓመት እድሜ ድረስ የሚገኙ የልዩ ካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች አሉ፡፡ ስለ APS ልዩ የትምህርት ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ https://www.apsva.us/countywide-programs/ ይጎብኙ፡፡

ቤሰቦች እንዲዘጋጁባቸው የሚያስፈልጉ የሚተነበዩ ልዩ ሽግግሮች የሚያካትቱት፡

**ከህጻንነት እስከ ቅድመ መዋለ ህጻናት**

በአርሊንግተን፣ ልጆች ከቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች (ብዙውን ጊዜ የወላጅ የሕጻናት ትምህርት (PIE) ፕሮግራም እየተባለ የሚጠራው) ሽግግር እና ከሚከተሉት ካሉ ወደ የሕዝብ ትምህርት ቤት የቻይልድ ማግኛ ስርአት መግባት ይችላሉ፡

- እስከ ቀጣይ ትምህርት መስከረም 30 ድረስ 2 ዓመት ከሆናቸው፣ እና
- በአርሊንገትን የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና/ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ሌላ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለልዩ የትምህርት አገልገሎቶች ብቁ ሆኖነው ከተገኙ የቅድመ መዋለ ህጻናት የሕዝብ ትምህርት ቤት ቻይልድ ፋይንድ ስርአት መግባት ይችላሉ፡

ልጆች እድሜያቸው ሶስት ዓመት ከሞላቸው ለ PIE የሕጻናት የክትትል አገልግሎት ብቁ አይሆኑም፡፡ APS ለልዩ ትምህርት ብቁ ሆነው ለተገኙ ተማሪዎች ዘላቂ ፕሮግራምና አገልግሎቶች ያበረክታል፡፡ የአብዛኛዎቹ የመጀመሪያ ትምህርት ቤቶች በካንቲነም ከሚገኙት በርካታዎቹ መካከል የቅድመ መዋለ ህጻናት ልዩ ትምህርታዊ ፕሮግራም ያላቸው ሲሆን የቅድመ መዋለ ህጻናት ፕሮግራም ፍላጎት ያላቸው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአጎራባች የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ይማራሉ፡፡ ይሁንና ከጊዜ ወደ ጊዜ በIEP ቡድን ሌላ ምደባ ምክረ ሀሳብ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በPRC የሚገኙ ሠራተኞች  እንደልጃቸው የIEP ቡድን አንድ አካል ስለምደባ መረጃን መሰረት ያደረገ ውሳኔ ለመስጠት ወላጆች/ቤተሰቦችን ለማገዝ መረጃ መስጠትና ጥያቄዎችን መመለስ ይችላሉ፡፡

**ከቅድመ መዋለ ህጻናት እስከ መዋለ ህጻናት**

የተወሰኑ ወላጆች ልጆቻቸው በመስከረም 30 ላይ 6ኛ አመታቸው እስኪሞላ ድረስ እንዲቆዩ ቢመርጡም የአብዛኛዎቹ ልጆች ወደ መዋለ ህጻናት ፕሮግራም የሚሸጋገሩበት ወቅት በመስከረም 30 እድሜያቸው 5 ዓመት ሲሞላ ነው፡፡ ልጅዎ ለልዩ ትምህርት ብቁ ሆኖ ከተገኘ እርስዎ እና ሌሎች የIEP አባላት ለልጅዎ በልዩ የመማር ፍላጎቱ መሰረት ተገቢ ምደባውን ለመወሰን በጋራ የምትሰሩ ይሆናል፡፡ ቤሰቦች ስለ መዋለ ህጻናት ሽግግር የPRC ወርክሾፖች ላይ መገኘት እና ለወደ ፊቱ ወላጅ የሚሆኑ ቤሰቦች ክፍት በሚሆንባቸው ሰዓታት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለመጎብኘት መምረጥ አለባቸው፡፡ የPRC ሠራተኞች ቤሰቦች ለዚሁ ሽግግር እንዲዘጋጁ በመርዳት ጥያቄዎችን በመመለስ ሊያግዙአቸው ይችላል፡፡

**ከአንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች)**

በአርሊንግተን፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከቅድመ መዋለ ህጻናት እስከ 5ኛ ክፍልን ያካትታሉ፡፡ ከስድስተኛ ክፍል የሚያድጉ ተማሪዎች ከአርሊንግተን መለስተኛ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ይማራሉ፡፡ ልጅዎ አምስተኛ ክፍል ሲቃረብ፣ የ IEP ቡድንዎ በመለስተኛ ደረጃ ስለልጅዎ ፍላጎቶች መወያየት እና የልጅዎን ሽግግር ማቀድ ይጀምራል፡፡ ቤተሰቦች ስለ አርሊንግተን መለስተኛ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች ለመማር የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መረጃ ምሽት ላይ እንዲገኙ የሚበረታቱ ሲሆን ለመረጃ እና ድጋፍ PRC ማነጋገር አለባቸው፡፡

**ከመካከለኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች)**

የአርሊንግተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍልን ያጠቃልላሉ፣ ከስትራትፎርድ ፕሮግራም እና ከHB-ዉድላውን ፕሮግራም በስተቀር፣ ከ6 እስከ 12ኛ ክፍልን ያካትታል፡፡ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጨረሻ አካባቢ፣ የIEP ቡድን ለተማሪዎ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመሸጋገር ማቀድ ይጀምራል፡፡ ለተጨማሪ መረጃ እና ድጋፍ ወላጆች PRC ማነጋገር ይችላሉ፡

**14 ዓመት**

በቨርጂንያ *የትምህርት መምሪያ ልዩ ትምህርትን የሚመራ ህግ*፡ ልጅዎ ሁለተኛ (ከፍተኛ) ደረጃ ትምህርት ቤት ከመግባቱ በፊት ነገር ግን ልጅዎ እድሜ 14 ዓመት ሲሞላ (ወይም ከዚያ በታች -የ IEP ቡድን ተገቢ ነው ብሎ ከወሰነ) ተፈጻሚ የሚሆን ከመጀመሪያ IEP ሳይዘገይ ከሆነ የልጅዎ IEP ማካተት ያለበት

- ከስልጠና፣ ትምህርት፣ የሥራ ቅጥር እና አግባብነት ካለው የተማሪው ራሱን ችሎ የመኖር ክህሎት የተያያዙ የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ግቦች፣ እና
- የትምህርት ኮርስ እንዲሁም ተግባራት ለምሳሌ ቋንቋ፣ ተዛማጅ አገልግሎት እና የማህበረሰቡ ልምድን ጨምሮ የሽግግር አገልግሎቶች፡፡

**የአብዛኛው እድሜ**

የእርስዎ ልጅ የአብዛኛው እድሜ (18) ዓመት ከመድረሱ ቢያንስ አንድ ዓመት በፊት IEP ቡድን እርስዎና ልጅዎ በ18 ዓመት እድሜው ሙብት ከእርስዎ ወደ ልጅዎ እንደሚተላለፍ መረጃ እንደነበራችሁ የሚገልጽ መግለጫ ማካተት አለባቸው፡፡ ይሁንና በሞግዚትነት አሰራር፣ በውክልና ስልጣን ወይም ማረጋገጫ አማካኝነት ለልጅዎ ትምህርታዊ ውሳኔን በመስጠት የሚቀጥሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይችላሉ፡፡ ለተጨማሪ መረጃ www.doe.virginia.gov/special-ed/index.shtml ይመልከቱ፡፡

- የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እስታንዳርድ ወይም የከፍተኛ ትምህርት ዲፐሎማ፣ እና ወይም እድሜአቸው 22 ዓመት እስኪሞላ ድረስ ልዩ ትምህርት ማግኘቱን መቀጠል ይችላሉ፡፡ *(ከመስከረም 30 በኋላ እስካሁን ድረስ እስታንዳርድ ወይም የከፍተኛ ትምህርት ዲፐሎማ ያለገኙ እና ወይም እድሜአቸው 22 ዓመት ያልሞላ ተማሪዎች ለዚህኛው የትምህርት ዘመን አገልግሎቱን ለማግኘት ብቁ ሆነው ይቆያሉ፡፡)* በ IEP ቡድን ውሳኔ መሰረት በርካታ ተማሪዎች በአጎራባች ትምህርት ቤታቸው መቆየት ወይም የስትራትፎርድ ፕሮግራም ወይም የሥራ ቅጥር ዝግጁነት ፕሮግራም (PEP) የመሳሰሉትን አገልግሎቶች በካውንቲ አቀፍ ፕሮግራም ማግኘት ይችላሉ፡፡ የሥራ ቅጥር ዝግጁነት ፕሮግራም (PEP) በአርሊንግተን የሙያ ማእከል ለተደገፈ የሥራ ልምድ፣ የተደገፈ የጉዞ ስልጣና ራስን ችሎ የመኖር ስልጠና ማህበረሰብ መሰረት ያደረገ ክፍል ነው፡፡

**ከከፍተኛ እስከ ኮሌጅ ወይም የሙያ ትምህርት ቤት**

የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሽግግር እቅድ ለዚህኛው ሽግግር ከበርካታ አመታት በፊት ይጀምራል፡፡ በ IEP ሂደት ውስጥ የተማሪዎቹን ጥንካሬ፣ ምርጫና ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ እድሜን እና ምዘናን መሰረት ያደረገ ወላጆች፣ ተማሪዎችና ሠራተኞች ስለ ድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ግቦች ላይ ውይይት ይጀምራሉ፡፡ በተጨማሪም የIEP ቡድኖች በዲፕሎማ አማራጮች ዙሪያ ይወያያሉ፡፡ የአርሊንግተን ከፍተኛ ትምህርት ቤት ይህንን ሂደት ለማገዝ እያንዳንዳቸው የሽግግር አስተባባሪ አላቸው፡፡ የሽግግር አስተባባሪዎችን ለ IEP ቡድኖች ቴክኒካዊ ድጋፍና እገዛ ያመለክታሉ፡፡ የትምህርት ቤታችሁን የሽግግር አስተባባሪ እንዴት እንደምታገኙ እና ለPRC የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ሽግግር ወርክሾፖች አንዳቸው እንዴት እንደሚመድብ ለማወቅ ከትምህርት ቤታችሁ ወይም PRC ቡድን ጋር ይገናኙ፡፡ በተጨማሪም በ APS የሽግግር አገልግሎት መረጃን ለማግኘት እባክዎን http://www.apsva.us/page/20922 ድረገጹን ይመልከቱ፡፡

**ቤተሰቦች ለሽግግር  እንዴት ይዘጋጃሉ?**

- ላልተስተጓጎለ ሽግግር ለመዘጋጀት ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው መውሰድ ስለሚችሉዋቸው እርምጃዎች ለማወቅ ከወላጅ ምንጭ ማእከል (PRC) ጋር መገናኘት፡፡
- ስለ ወላጅ የትምህርት አማራጮችና የAPS የመረጃ ሌሊቶች ማስታወቂያዎቹን ለማግኘት (በwww.apsva.us/ APS ትምህርት ቤት ንግግር መምረጥና እንደ አማራጭ የወላጅ አካላዊና የልዩ ትምህርት/ወላጅ የምንጭ ማእከል መምረጣችሁን እርግጠኛ ሁኑ)፡፡ የAPS ትምህርት ቤት ንግግርን ይምረጡ፡፡ PRC በሽግግር ላይ በርካታ የወላጅ የትምህርት ጊዜዎቹን ይሰጣል፡፡ ለመከታተል ይመዝገቡ ያድርጉ፡፡
- በትምህርት ቤት አማራጮች፣ ካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች እንዲሁም የትምህርት ቤት ዝውውር አማራጮች ላይ መረጃ ለማግኘት በ https://www.apsva.us/school-options/ የAPS ድረገጽ መጎብኘትና "የትምህርት ቤት አማረጭ" ገጽ ላይ ማሰስ፡፡
- በአመቱ መጀመሪያ ላይ ከልጅዎ የIEP ቡድን ጋር ነግግግርን ይጀምሩ፡፡ ቤተሰባችሁ ያለው ጥያቄ ዝርዝርን ማዘጋጀትና በሽግግር ወቅት ስለ ልጃቻችሁ ፍላጎት መረጃ ይጠይቁ፡፡ የ IEP ቡድኖች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አማራጭ ፕሮግራሞችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይችላሉ፡፡ በካውንቲ አቀፍ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም https://www.apsva.us/student-services-special-education/special-education-office-of/countywide-programs መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡
- የAPS *የቨርጂኒያ ዲፕሎማ አማራጭና የሚኖር ውጤት (በዚህ መመሪያ የተካተተ) ይመልከቱ/ይዳስሱ፡፡*
- *የቨርጂኒያ I'm Determined* ፕሮጀክት ነኝ ድረገጽ www.imdetermined.org ይጎብኙ፡፡
- የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሞክሮዎችን የሚፈልጉ የተማሪዎች ወላጆች በ www.going-to- college.org እና www.thinkcollege.net ስለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ስለኮሌጅ ድጋፍና ፕሮግራም የበለጠ ማወቅ ይችላሉ፡፡
- ግለሰብን-ማእከል ያደረገ እቅድ በተመለከተ ከ http://www.personcenteredpractices.org/launch_vpbs.html የበለጠ ይገንዘቡ፡፡
- የAPS የመረጃ ሌሊቶች፣ ትምህርት ቤት፣ ክፍት ቤቶች፣ PRC የሽግግር ክፍለ ጊዜዎች እና "የወደፊት ጥያቄ" (ከአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች፣ ወላጆችና ባለሙያዎች ነጻ፣ ቀጠናዊ የባለሙያዎች እና ጆሌጅ ፎረም) ይሳተፉ፡፡ ስለ የወደፊት ጥያቄ የበለጠ ለማወቅ http://futurequest.gmu.edu/ ይጎብኙ፡፡

VIRGINIA DEPARTMENT OF EDUCATION

# ፈጣን እውነታዎች (ሚያዚያ 2010)

## ሁለተኛ ሽግግር፡ የአስቀድሞ ማቀድ ጠቀሜታ ምንድን ነው፡፡

*የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌ* (IDEA) 2004 የትምህርት ውጤትን ለማሻሻል እና የተግባር አፈጻጸምን ከትምህርት ቤት ወደ ድህረ-ትምህርት እንቅስቃሴዎች ለማቀላጠፍ ያተኮረ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ሽግግርን በውጤት ተኮር ሂደት ውስጥ የተነደፈ የተቀናጀ የተግባር ስብስብ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በ14 እና 16 ዓመት እድሜ ለወጣቶች የሽግግር እቅድ አላማ ተመሳሳይ ሆኖ ጥሩ እቅድ ከትምህርት ቤት ወደ ድህረ ትምህርት ቤት ተግባራት የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት የተቀናጀ ሥራ ቅጥር፣ ዘላቂ እና የአዋቂዎች ትምሀርት፣የአዋቂዎች አገልግሎት፣ ራስን ችሎ መኖር እና የማህበረሰብ ተሳትፎ የመሳሰሉትን እንቅስቃሴዎችን የሚያመቻች የአካዳሚክ ስኬትንና ተግባራዊ ክንውን የሚዳስስ መሆን አለበት፡፡

የአካባቢ ትምህርታዊ ኤጀንሲዎች(LEA) ተማሪው 14 ዓመት ሲሆነው ተፈጻሚ እንዲሆኑ ከመጀመሪያው ግለሰባዊ የተደረገው የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ሳይቆይ መጀመር የለባቸው ምክንያቱም ከ8ኛ ክፍል በፊት አስቀድሞ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ አማራጮች እና የሚወሰዱ ትምህርቶች ውይይት መጀመራቸው ተማሪውን ለምረቃ የሚያስፈልገውን የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርሶችን ተደራሽ እንዲሆን ስለሚያስችለው ነው፡፡ የIEP ቡድን አባላት በዲፕሎማ ምርጫዎች ላይ ሲወያዩ፣ በ *ቨርጂኒያ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እውቅና መስጫ ደረጃዎችን የሚያቋቁሙ ደንቦች* ውስጥ ያሉትን የምረቃ መስፈርቶች መጥቀስ አለባቸው፡፡ በሁቱም እድሜዎች 14 እና 16 እቅዶች የተማሪውን ግለሰባዊ ፍላጎት፣ ጥንካሬ ምርጫዎችና ፍላጎቶቹን የሚያመላክት እድሜን መሰረት ያደረገ ተገቢ የሽግግር ምዘና የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ የሽግግር ምዘናዎች ወይም ጥናቶች ምልከታዎችን፣ ቆጠራዎችን፣ በየጊዜ የሚከናወን ዳሰሳ፣ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ጥናቶችና ዳሰሳዎችን እንዲሁም አካዳሚካዊ ጥናቶቸን ሊያካትት ይችላል፡፡ የሽግግር አገልግሎቶች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ግቦችን ለመደገፍ በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና የትምህርት ኮርሶች ግብ ላይ ለመድረስ ተማሪውን ለመርዳት የሚያስፈልጉ ተግባራትን ያካትታል፡፡ የሽግግር ተግባራት መመሪያ (የትምህርት መማሪያ ቋንቋ) ተዛማጅ አገልግሎቶች፣ የማህበረሰበ ተሞክሮ፣ የሥራ ቅጥር እና ሌሎች አዋቂዎች የሚኖሩባቸው አላማዎች/ግቦች፣ የእለት ተእለት ኑኖር ክህለቶች፣ ተግባራዊ-ሙያዊ ግምገማዎችን ሊያካትት ይችላል፡፡ ለተማሪው የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ግቦችን ወይንም የድህረ ትምህርት ቤት ራዕዮችን ለመወሰን ከተማሪው እንዲሁም ከወላጆች እና እንዳስፈላጊነቱ ከሌሎች ጋር ውይይት መካሄድ አለበት፡፡

የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ግቦች የሚለኩና አስፈላጊ ሲሆን ከስልጠና፣ ትምህርት፣ የሥራ ቅጥር እንዲሁም ራስን ችሎት የመኖር ክህሎት ጋር የተያያዘ እድሜን መሰረት ያደረገ ተገቢ የሽግግር ምዘና ወይም ጥናት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ግቦች ጥንካሬዎችን፣ ምርጫዎችንና ፍላጎቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት በተማሪው ግለሰባዊ ፍላጎት ላይ የተተራሱ መሆን አለባቸው፡፡ IEP በየአመቱ ወቅታዊ የሚደረግ እንደመሆኑ ተማሪው እድሜው በተጨረ ቁጥር ለውጦች ሊስተዋሉ ይችላሉ፡፡ በ 16ኛ ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ላይ አግባብነት ካለው የኤጀንሲዎችና ኃላፊነቶችና ትስስር በዚሁ IEP ውስጥ መፈታት አለባቸው፡፡

ከሁለተኛ ደረጃ መርሃ ግብር ሲወጡ የክንውን/የአፈጻጸም ማጠቃለያ ለተማሪ መሰጠት አለበት፡፡ ተማሪው ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አደረጃጀት ሽግግሩን ሲያገኝ የሚያግዘው ይህ ማጠቃለያ የሚያካትተው፡

- አካዳሚካዊ ስኬቶች - ወጣቱ/ወጣቷ የሚያውቀውን/የምታወቀውን ፊደል፣ አኃዝ፣ ደንበኛ፣ የግል ፋይናንስ እንዲሁም የመማር ክህሎቶቹን፣ ምክንያታዊነት፣ ተግባቦት፣ የድርጊት ሂደቶችን እንዲሁም አስፈላጊ እገዛዎችን፣ ድጋፎችንና ማሻሻያዎችን ወዘተ የመሳሰሉትን የሚያካትት፣

- ተግባራዊ ክንውን - ወጣቱ/ወጣቷ በትምህርት ቤት፣ በማህበረሰብ ውስጥ፣ በሥራ፣ በራስ እንክብካቤ፣ እንቅስቃሴ፣ በራስ መወሰን፣ ደህንነት፣ ከፍተኛ የተግባር ክህሎቶች እንዲሁም አስፈላጊ እገዛዎችን፣ ድጋፎችንና ማሻሻያዎችን ወዘተ የመሳሰሉትን የሚያካትት፣

- ድጋፎች - ተማሪዎች በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካባቢ ስኬታማ እንዲሆኑ ሊያስፈልጋቸው የሚችል ልዩ ድጋፍ፣ ማሻሻያዎች፣ አጋዥ ቴክኖሎጂ ወይም ሌላ ድጋፍ፣ እና

- ቀጣይ እርምጃ - የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ግቦችን ለማሳካት የኮሌጅ ቅድመ ገለጻ ላይ እንዲገኙ ፣ ከማቋቋሚያ አገልግሎቶች መምሪያ ጋር እንደገናኙ፣ በማህበረሰብ ኮሌጅ ከአካል ጉዳተኛ አገልግሎት አማካሪ ጋር እንዲገናኙ፣ ወቅታዊ የአካል ጉዳተኛ ሰነድ ፋይል እንዲይዙ የሥራ ቅጥር ማመልከቻዎችን እንዲያጠናቅቁ ወዘተ የመሳሰሉትን ምክረ ሀሳብ፡፡

**ለበለጠ መረጃ፡**

የበርጂኒያ ትምህርት መምሪያ ድረገጽ www.doe.virginia.gov መጎብኘት ወይም በ 804-225-2932፣1-800-422-2083 የልዩ ትምህርት እና የተማሪ አገልግሎ ክፍል ጋር መገናኘት ወይም የጽሁፍ ተጠቃሚዎች በ711 (ቨርጂኒያ ሪለይ) ይደውሉ፡፡

# የቨርጂኒያ ዲፕሎማ አማራጮችና ሊሆኑ የሚችሉ ውጤቶች

ARLINGTON PUBLIC SCHOOLS
ASPIRE2EXCELLENCE

ቅድመ-K፣ K፣ 1 | ክፍሎች 3፣ 4፣5 | ክፍሎች 6፣ 7፣ 8 | ክፍሎች 9፣ 10፣ 11፣ 12

| | የላቀ ጥናቶች ዲፕሎማ | መደበኛ ዲፕሎማ | የተተገበሩ ጥናቶች ዲፕሎማ |
|---|---|---|---|
| ዝቅተኛ የሚያስፈልጉ መደበኛ ክሬዲቶች > | 26 | 22 | |
| እንግሊዘኛ | 4 | 4 | |
| ሒሳብ | 4 | 3 | |
| የሳይንስ ላብራቶሪ | 4 | 3 | |
| ታሪክና ማህበራዊ ሳይንስ | 4 | 3 | |
| ጤናና የሰውነት ማጎልመሻ | 2 | 2 | |
| የውጭ ቋንቋ | 3 | 2 | |
| ጥበባት ወይም ሙያ/ቴክኒክ | 1 | | |
| ኢኮኖሚክስና የግል ፋይናንስ | 1 | 1 | |
| ተመራጮች | 3 | 4 | |

**የላቀ ጥናቶች ዲፕሎማ:**

**9 የተረጋገጡ ክሬዲቶች __መሆን አለባቸው*__**

2 እንግሊዘኛ
2 ሒሳብ
2 የሳይንስ ላብራቶሪ
2 ታሪክ /ማሕበራዊ ሳይንስ
1 በተማሪ-የተመረጠ ፈተና

**መደበኛ ዲፕሎማ:**

**9 የተረጋገጡ ክሬዲቶች __መሆን አለባቸው*__**

2 እንግሊዘኛ
1 ሒሳብ
1 የሳይንስ ላብራቶሪ
1 ታሪክ /ማህበራዊ ሳይንስ
1 በተማሪ-የተመረጠ ፈተና

*መደበኛ ዲፕሎማ በጠቅላላው 2 ክሬዲቶች በተዋሃዱ ምድብ ውስጥ ቢያንስ አንድ የስነ ጥበብ ወይም የሙያ/ የቴክኒክ ክሬዲት ያስፈልገዋል፡፡*

**የተተገበሩ ጥናቶች ዲፕሎማ:**

የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የግለሰባዊ የትምህርት መርሃ ግብራቸውን (IEP) መስፈርቶችን ያሟሉ እና ለሌሎች ዲፕሎማዎች መመዘኛዎችን የማያሟሉ ተማሪዎች በ IEP ቡድን የተግባር ጥናት ዲፕሎማ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

- የሙያ፣ የቴክኒክና የንግድ ትምህርት ቤት
- ኮሚኒቲ ኮሌጅ
- የ 4 ዓመት ኮሌጅ / ዩኒቨርሲቲ
- ወታደራዊ አገልግሎት (ASVAB መውሰድ አለበት)
- ልምምዶች
- የአመት ፕሮግራም ክፍተት
- የአገልግሎት ትምህርት ፕሮግራም
- ሙያዊ ልምምዶች
- የአዋቂዎች ትምህርት

- የ APS ፕሮግራም ለስራ ዝግጁነት (PEP)
- የአዋቂዎች ትምህርት
- ኮሚኒቲ ኮሌጅ
- የሙያ ስልጠና
- ልምምዶች
- ወታደራዊ አገልግሎት (ASVAB መውሰድ አለበት
- የ አመት ፕሮግራም ክፍተት
- አገልግሎት ትምህርት ፕሮግራም

ብቁ ከሆነ፣ የአዋቂዎች አገልግሎት ኤጀንሲ ድጋፍ

**ስራ**

** የተረጋገጠ ክሬዲት ኮርሱን በተሳካ ሁኔታ በመጨረስና በ SOL ፈተና የማለፊያ ነጥብ ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ለበለጠ መረጃ፣ ፍቺዎችን ይመልከቱ፡፡*

## መደበኛ የዲፕሎማ ኮርስ መስፈርቶች (8 VAC 20-131-50.B)

| የትምህርቱ አካባቢ | መደበኛ ክሬዲቶች፡ በ2011-2012 እና ከዚያም በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር ውጤታማ የሆነ | የተረጋገጡ ክሬዲቶች፡ በ2003-2004 እና ከዚያም በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤታማ የሆነ |
|---|---|---|
| **እንግሊዘኛ** | 4 | ***በሁለቱም*** SOL የማለፊያ ነጥብ ማግኘት አለበት፡<br>• እንግሊዝኛ 11 ምንባብ<br>• እንግሊዝኛ 11 መጻፍ |
| **ሒሳብ**<br>ከመካከላቸው ***ቢያንስ ሁለት*** የተለያዩ ኮርሶችን ይምረጡ፡ አልጀብራ I፣ ጂኦሜትሪ፣ የአልጀብራ ተግባራት እና የመረጃ ትንተና፣ አልጀብራ II፣ ወይም ሌሎች ከአልጀብራ II ደረጃ በላይ የሆኑ የሂሳብ ትምህርቶች፡፡ | 3 | ከሚከተሉት SOL ***በአንዱ*** የማለፊያ ነጥብ ማግኘት አለበት፡፡<br>• አልጀብራ 1<br>• ጂኦሜትሪ<br>• አልጀብራ II |
| **የላቦራቶሪ ሳይንስ**<br>***ቢያንስ ከሁለት*** የተለያዩ የሳይንስ ዘርፎች ኮርሶችን ይምረጡ፡ የመሬት ሳይንስ፣ ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ ወይም ፊዚክስ፡፡ | 3 | ከሚከተሉት SOL ***በአንዱ*** የማለፊያ ነጥብ ማግኘት አለበት፡<br>• የመሬት ሳይንስ<br>• ባይሎጂ<br>• ኬሚስትሪ |
| **ታሪክ እና ማህበራዊ ሳይንሶች**<br>ይህንን መስፈርት ለማሟላት የተጠናቀቁ ኮርሶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡<br>***ሁለቱም*** የዩኤስ/ቨርጂኒያ ታሪክ እና የዩኤስ/ቨርጂኒያ መንግስት - እንዲሁም አንድ ኮርስ በአለም ታሪክ ወይም በአለም ጂኦግራፊ ወይም በሁለቱም፡፡ | 3 | ከሚከተሉት SOL ***በአንዱ*** የማለፊያ ነጥብ ማግኘት አለበት፡<br>• የዓለም ታሪክ እስከ 1500 ዓ.አ<br>• የዓለም ታሪክ ከ1500 ዓ.አ<br>• የዓለም ጂኦግራፊ<br>• የዩኤስ/ቨርጂኒያ ታሪክ |
| **ጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት** | 2 | |
| **የውጭ ቋንቋ፣ ጥበባት ወይም ሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት**<br>ለዚህ መስፈርት የተገኙ ክሬዲቶች በጥሩ ወይም በኪነጥበብ ወይም በሙያ እና በቴክኒክ ትምህርት ***አንድ*** ክሬዲት ማካተት አለባቸው፡፡ | 2 | |
| **ኢኮኖሚክስ እና የግል ፋይናንስ** | 1 | |
| **ተመራጮች**<br>ይህንን መስፈርት ለማሟላት ኮርሶች ***ቢያንስ ሁለት ተከታታይ ምርጫዎችን*** ማካተት አለባቸው፡፡ | 4 | |
| **በተማሪ የተመረጠ ፈተና**<br>የተረጋገጠ ክሬዲት ለማግኘት ተማሪው ተጨማሪ ፈተናዎችን ሊጠቀም ይችላል፡<br>ኮምፒውተር ሳይንስ፣ቴክኖሎጂ፣ሙያ/የቴክኒክ ትምህርት፣ኢኮኖሚክስ፣ወይም ሌሎች ዘርፎች | | ከላይ ከተዘረዘሩት የትምህርት አካባቢዎች ከእንግሊዝኛ በስተቀር ***አንድ*** ተጨማሪ SOL ይምረጡ፡፡ |
| **ጠቅላላ** | **22** | **6** |

***ማሳሰቢያ፡*** በ2013-2014 ለመጀመሪያ ጊዜ ዘጠነኛ ክፍል ከሚገቡ ተማሪዎች ጀምሮ፣ ተማሪው የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡

- በቦርድ የጸደቀ የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ምስክር ወረቀት ያግኙ፣ እና
- አንድ ምናባዊ (ቨርቹዋል) ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ያጠናቅቁ፣ ይህም ክሬዲት ያልሆነ ሊሆን ይችላል፡፡

## የላቀ ጥናቶች ዲፕሎማ ኮርስ መስፈርቶች (8 VAC 20-131-50.C)

| የትምህርቱ አካባቢ | መደበኛ ክሬዲቶች፡ በ 2011-2012 እና ከዚያም በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር ውጤታማ የሆነ | የተረጋገጡ ክሬዲቶች፡ ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በ 2000-2001 እና ከዚያ በኋላ ውጤታማ የሆነ |
|---|---|---|
| **እንግሊዘኛ** | 4 | ***በሁለቱም*** SOL የማለፊያ ነጥብ ማግኘት አለበት፡<br>• እንግሊዝኛ 11 ምንባብ<br>• እንግሊዝኛ 11 መጻፍ |
| **ሒሳብ**<br>ከመካከላቸው ***ቢያንስ ሶስት*** የተለያዩ ኮርሶችን ይምረጡ፡<br>አልጀብራ I፣ ጂኦሜትሪ፣ አልጀብራ II፣ ወይም ሌሎች ከአልጀብራ II ደረጃ በላይ የሆኑ የሂሳብ ትምህርቶች፡፡ | 4 | ከሚከተሉት SOL ***በሁለቱ*** የማለፊያ ነጥብ ማግኘት አለበት፡<br>• አልጀብራ 1<br>• ጂኦሜትሪ<br>• አልጀብራ II |
| **የላቦራቶሪ ሳይንስ**<br>***ቢያንስ ከሶስት*** የተለያዩ የሳይንስ ዘርፎች ኮርሶችን ይምረጡ፡<br>የመሬት ሳይንሶች፣ ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ እና ፊዚክስ፡፡ | 4 | ከሚከተሉት SOL ***በሁለቱ*** የማለፊያ ነጥብ ማግኘት አለበት፡<br>• የመሬት ሳይንስ<br>• ባዮሎጂ<br>• ኬሚስትሪ |
| **ታሪክና ማህበራዊ ሳይንሶች**<br>ይህንን መስፈርት ለማሟላት የተጠናቀቁ ኮርሶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡<br>**ሁለቱም** የዩኤስ/ቨርጂኒያ ታሪክ እና የዩኤስ/ቨርጂኒያ መንግስት - በዓለም ታሪክ ወይም በዓለም ጂኦግራፊ ወይም በሁለቱም ውስጥ ***በተጨማሪ ሁለት*** ኮርሶች፡፡ | 4 | ከሚከተሉት SOL ***በሁለቱ*** የማለፊያ ነጥብ ማግኘት አለበት፡<br>• የዓለም ታሪክ እስከ 1500 ዓ.አ<br>• የዓለም ታሪክ ከ1500 ዓ.አ<br>• የዓለም ጂኦግራፊ<br>• የዩኤስ/ቨርጂኒያ ታሪክ |
| **ጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት** | 2 | |
| **የውጪ ቋንቋ**<br>ይህንን መስፈርት ለማሟላት ኮርሶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:<br>***የሶስት*** አመት የአንድ ቋንቋ፡፡<br>***ወይም***<br>***ሁለት*** ዓመት እያንዳንዳቸው ሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች፡፡ | 3 | |
| **ስነ ጥበባት ወይም ሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት** | 1 | |
| **ኢኮኖሚክስ እና የግል ፋይናንስ** | 1 | |
| **ተመራጮች** | 3 | |
| **የተማሪ የተመረጠ ፈተና**<br>የተረጋገጠ ክሬዲት ለማግኘት ተማሪው ተጨማሪ ፈተናዎችን ሊጠቀም ይችላል፡<br>ኮምፒውተር ሳይንስ፣ቴክኖሎጂ፣ሙያ/የቴክኒክ ትምህርት፣ኢኮኖሚክስ፣ወይም ሌሎች ዘርፎች፡፡ | | ከላይ ከተዘረዘሩት የትምህርት አካባቢዎች ከእንግሊዝኛ በስተቀር ***አንድ*** ተጨማሪ SOL ይምረጡ፡፡ |
| **ጠቅላላ** | **26** | **9** |

***ማሳሰቢያ፦*** በ 2013-2014 ለመጀመሪያ ጊዜ ዘጠነኛ ክፍል ከሚገቡ ተማሪዎች ጀምሮ፣ ተማሪ አንድ ቨርቹዋል ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ አለበት፣ ይህም ክሬዲት ያልሆነ ሊሆን ይችላል፡፡

# ትርጓሜዎችና ደጋፊ መረጃዎች

**የእድሜ ብቁነት**

“የእድሜ ብቁነት” ማለት በቨርጂኒያ ህገ ደንብ መሰረት (2-21 አካታች) በመስከረም 30 ወይም ከዚያ በፊት 22ኛ ዓመት የሞላቸውን እና ሁለተኛው የጹሁፍ ቀናቸው በመስከረም 30 የሚውል በአካል ጉዳተኝነታቸው ምክንያት ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎት ፍላጎት ያላቸውን በስታንዳርድ ወይም የከፍተኛ ሁለተ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፍተኛ ዲፕሎማ ያልተመረቁ ሁሉም የአካል ጉዳተኛ ልጆች ናቸው፡፡

**የብዙዎች እድሜ**

“የአብዛዎቹ” እድሜ ማለት የጥበቃ ቅደም ተከተል/ደንብኛ ሌሎች መብቶች ለተማሪው የሚተላለፈውን ለአካል ጉዳተኛ ተማሪ ወላጅ ወይም ወላጆች የተሰጡ ሌሎች መብቶች በሚኖሩበት ጊዜ ያለው እድሜ ነው፡፡ በቨርጂኒያ የአብዛኞቹ እድሜ ማለት 18 ዓመት ነው፡፡ የአብዛኛው እድሜ ማስታወቂያ የተማሪው አስራ ስምንተኛ አመት የልደት ባአሉ ከመድረሱ ቢያንስ ከአንድ አመት በፊት መሰጠት አለበት፡፡

**መደበኛ እና የተረጋገጡ ክሬዲት**

አንድ መደበኛ ክሬዲት የትምህርት መማሪያ ዝቅተኛ 140 ሰዓት እና የኮርሱን ስኬታማ መጠናቀቅ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

የተረጋገጠ ክሬዲት በትምህርት ቦርድ እንደጸደው ዝቅተኛው መማሪያ 140 ሰዓታት፣ የኮርሱን መስፈርቶች በስኬት ማጠናቀቅ እና በኮርሱ መጨረሻ ላይ የኤስኦኤፍ ነጥብ ፈተና ወይም ተጨማሪ ፈተና በስኬት ማለፍን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የማለፊያ ነጥቡ 400 ነው፡፡

**መደበኛ ዲፕሎማ ከክሬዲት ማስተናገጃ ጋር**

የክሬዲት ድጋፍ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በመደበኛ ዲፕሎማ ለመመረቅ የሚያስፈልገውን መደበኛ እና የተረጋገጠ ክሬዲት አማራጭን ይሰጣል፡፡

የክሬዲት ማስተናገጃዎች፡

- ክሬዲት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከተማ
- በዋና የትምህርት ይዘት ዙሪያ በአካባቢው የሚሰጥ የተረጋገጠ ክሬዲት
- የመደበኛ ክሬዲት መስፈርቱን ለማማሏላት የሚሰጥ አማራጭ ኮርስ

እነዚህ ከተማሪው የስምንተኛ ክፍል የትምህርት አመት በኋላ በማንኛውም ጊዜ አግባብነት ሲኖረው ተማሪውን ጨምሮ  በተማሪው የIEP ቡድን የሚወሰን ይሆናል፡፡

አንድ ተማሪ ብቁ ለመሆን የሚከተሉተን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡

- ከመደበኛ-መሰረት ያደረገ የይዘት ግብ ወይም 504 እቅድ ጋር ወቅታዊ IEP መኖር፡፡
- የክፍል ደረጃ ከሚጠበቀው የክፍል ደረጃ ጋር ይህንን ከማሳካት እና ከግብ ከማድረስ የሚከለክል ነገር ግን የክፍል ደረጃ ይዘትን የሚማር የአካል ጉዳት፡፡
- የክፍል ደረጃ SOL ይዘት እና ስኬትን በማሳየት ጠቃሚ የመማሪያ ቋንቋ ተደራሽ መሆን የሚያስፈልገው፡፡
- ባለፈው ክንውን በርካታ የመከኪያ አላማዎች መሰረት ተማሪው በመደበኛ የጊዜ ማእቀፍ ውስጥ የሚያስፈልገውን መደበኛ እና የተረጋገጠ የክሬዲት መለኪያ ለማሳካት ላይጠበቅበት ይችላል፡፡

**ማሳሰቢያ፡** ድጋፉን የሚያገኙ ተማሪዎች በመደበኛ ዲፕሎማ ለመመረቅ አሁን 22 መደበኛ ክሬዶችንና 6 የተረጋገጠ ክሬዲት ማግኘት ያስፈልገዋል፡፡

የክሬዲት ድጋፍ ለከፍተኛ ትምህርት ዲፕሎማ **አይገኝም**፡፡

የተሻሻለው መደበኛ ዲፕሎማ በ2013 -2014 የትምህርት ዓመት መጀመሪያ በሚጀምርበት ጊዜ 9ኛ ክፍል ለሚገቡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አማራጭ አይደለም፡፡ የክሬዲት ድጋፎች መደበኛ ዲፕሎማ ለማግኘት ከዚህ በፊት የተሻሻለ መደበኛ ዲፕሎማ ቀጥለው ለነበሩ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ይፈቅዳል፡፡

**የሁለትዮሽ ምዝገባ**

የሁለትዮሽ ምዝገባ ማለት በከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኮሌጅ ደረጃ ኮርሶችን ጎን ለጎን የሚወስድ ተማሪ ነው፡፡ በውጤት፣ ምክረ ሀሳብና የፈተና ውጤት መሰረት ጥቂት የሶፍመር/ሁለተኛ ተማሪዎች ብቁ መሆን ቢችሉም የሁለትዮሽ ምዝገባ ኮርሶች ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያለመ ነው፡፡ የሁለትዮሽ ምዝገባ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ እና የሂሳብ ዝግጁነታቸውን ማሳየትና ጠንካራ የክፍል ላይ መገኘትና በሳል ባህሪ ማሳየት አለባቸው፡፡ የኖርዘር ቨርጅኒያ ኮሚኒቲ ኮሌጅ (NVCC) ጥቂት ኮርሶች ተማሪው የከፍተኛ ሁለተኛ ረደጃ ዳይሬክተር በቅድሚያ የተጻፈ ፍቃድ ወይም ቤቱ ውስጥ ለተማሪ ተማሪ አግባቡነት ያለው ባለስልጣን ፈቃድ ካለው የቨርጅኒያ ሁለተኛ/ከፍተኛ ትምህርት ቤት የምረቃ መስፈርቶችን ሊያሟላ ይችላል፡፡ በሌላ አገላለጽ የNVCC ቨርጂኒያ ኮሚኒቲቭ ኮሌጅ የኮሌጅ ክሬዲት እየወሰዱ ባሉበት የተገኘው የኮሌጅ ክሬዲት ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ማመልከት የሚችሉበት በአካባቢው ከመሚገኙ የሕዝብ/የመንግስት ትምህርት ቤቶች አሁን ላይ የሁለትዮሽ ምዝገባ አለው፡፡

ሁለት ጊዜ ለመመዝገብ ምክንያቶች፡

- ኮርሱ በትምህርት ቤታችሁ ያልተሰጠ ሲሆን
- አስቀድማችሁ የኮሎጅ ትምህርትን በመፈለጋችሁ
- የባለሙያ ክህሎት መማር በመፈለጋችሁ

**አርሊንግተን የሙያ ማእከል ለስራ ዝግጁነት ፕሮግራም (PEP)**

ለስራ ቅጥር ዝግጅቱነት (PEP) የባለሙያ ማእከል መርሃ ግብር/ፕሮግራም አብዛኛውን የአካዳሚክ ፕሮግራሙን ያጠናቀቁ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚያስፈልጉአቸውን የሽግግር ዝግጁነት ለማሟላት ፈጣንና ትኩረት የተደረገበት ስልትን የሚጠቀም ዘርፈ ብዙ ዘዴ ያጣመረ ፕሮግራም ነው፡፡ እድሜያቸው 18-21 የሞላቸው ተማሪዎች በአሁኑ ገበያ ዘላቂ የሥራ ቅጥር የማገኘት እድላቸውን ከፍ የሚያደርግ ክህለትን የሚሰጥ ለወቅታዊ የሥራ አውድ ተቢ የሆነ የተረጋገጠ ልምድና የመማር እድል ይሰጣል፡፡ ከተጨባጭ የሥራ ላይ ስልጠና ህክሎች ጋር የተገቢ የቴክኖሎጂና ማህበራዊ ክህሎቶች ትኩረት የተሰጣቸው ናቸው፡፡

ይህ ፕሮግራም ተማሪዎች ክፍያ የሌለውና/ክፍያ ያለው የስራ ላይ ልምዶችን እና በሚመረቁበት ወቅት ለስራ ማረጋገጫ/ፈቃድ፣ የኮሌጅ ክሬዲት፣ የኔትወርኪንግ ኮሌክሽንስ (የግንኙነት መረብ) እና ወይም በቀጥታ የስራ ቅጥር እንዲያገኙ የተዘጋጀ ነው፡፡ ተማሪዎች በሁለተኛ/ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጨረሻ ዐመት የትምህርት ተሳትፎአቸው ወቅት ለPEP ሪፈራል መሰጠት አለበት፡፡ የተማሪዎች ተሳትፎ በፍላጎታቸው መሰረት በተናጠል የተደረጉ እና ለተማሪው አግባብነት ካለው የሙያ እና ቴክኒካዊ ትምህርት (CTE) ኮርሶቹን አንድ ላይ መወሰድ ይችላሉ፡፡

**የጎልማሶች የአገልግሎት አጄንሲ**

ጥቂት ጎልማሶች የትምህርት ቤቱን ስርዓት በሚለቁበት ወቅት ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ የጎልማሶች አገልግሎት ኤጀንሲዎች እገዛ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የብቁነት መስፈርቶችና ድጋፍ አይነቶች በኤጀንሲዎች መካከል ትልቅ ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በዋናነት ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ከከፍተኛ/ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከመልቀቃቸው አስቀድሞ ተገቢነት ካለው ከወደፊቱ ኤጀንሲዎች ጋር ይገናኛሉ፡፡

***ለበለጠ መረጃ እባክዎን ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ፡***
***የትምህርት እቅድ - www.apsva.us/academicplanning***
***የሽግግር አገልግሎቶች - www.apsva.us/transitionservices***

# የአኔ ልጅ

# ልጄን ከትምህርት ቤትዎ ጋር ማስተዋወቅ

**የተማሪው ስም፡** ____________________________________________________

**ክፍል፡** __________ **የትምህርት ዘመን፡** ________________ **ትምህርት ቤት፡** _______________

*( የልጅዎን ፎቶ ለማያያዝ ያስቡ፡፡)*

*ይህንን የልጅዎን መግለጫ ለመሙላት መምረጥ እና ለተማሪ ጥናት ኮሚቴ፣ IEP ቡድን ወይም ከልጅዎ አዲስ አስተማሪ(ዎች) ወይም ሐኪም ( ሞች) ጋር መጋራት ይችላሉ፡፡*

ስለ ልጄ ትንሽ . . . (የልደት ትእዛዝ፣ ስብእና፣ ማንኛውም ማቅረብ የሚፈልጉት መረጃ)፡

ልጄን በደንብ የሚገልጹት ሶስት ቃላት፡

የልጄ ጥንካሬዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

የልጄ ተግዳሮቶች ወይም የችግር አካባቢዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

ለልጄ ያሉኝ ህልሞች፡ (*ስለ ልጅዎ የወደፊት ሁኔታ ያለዎትን ራእይ ይግለጹ፡፡*)

ልጄ እምቅ ችሎታውን እንዲያሳካ የሚፈልጋቸው ድጋፎች የሚከተሉትን ያካትታሉ ብዬ አስባለሁ፡

ልጄ ፍላጎቱ/ፍላጎቷ የሚታወቀው በ፡ (*ድምጾችን፣ ቃላትን ወይም ምልክቶችን በመጠቀም*?)

ልጅዎ ሌሎች የሚናገሩትን ምን ያህል በሚገባ ይረዳል?

ልጄ አብዛኛውን ጊዜ ለሌሎች ልጆችና አዋቂዎች ምላሽ የሚሰጠው በ፡

ልጄ የሚወዳቸው እንቅስቃሴዎች፡

ልጄ የሚወዳቸው ምግቦች፡

ሌሎች የቡድን አባላት ስለ ልጄ እንዲያውቁ የምፈልገው በጣም አስፈላጊው ነገር፡

በትምህርት ቤት ልጄን በተመለከተ በጣም የምፈልገውና የሚያሳስበኝ ነገር፡

እንዲሁም እንዲያውቁልኝ የምፈልገው ነገር . . .

ከእኔ ጋር ለመገናኘት/ለመነጋገር በጣም የተሻለው መንገድ፡

# *የእኔ ምርጥ ቀን፡*
# *ለክፍልህ አዲስ ነኝ፣ እራሴን እንዳስተዋውቅ ፍቀድልኝ*

**ስም፡** ______________________________

**ክፍል፡** __________ **ቀን፡** ______________ **ክፍል፡** ____________________

*(የራስህን ፎቶ አያይዝ፡፡)*

*ይህንን የራስህን መግለጫ ለመሙላት መምረጥና ለአዲሱ መምህር (ሮች) ወይም ሐኪም (ሞች) ማጋራት ትችላለህ፡፡*

እኔን በደንብ የሚገልጹኝ ሶስት ቃላት. . .

የሚከተለው ቢሆን በትምህርት ቤት ምርጥ ቀኔ ይሆን ነበር . . . (የምትወደውንና የሚያስደስትህን ነገር ግለጽ)

እነዚህን ጨምሮ በጣም የምወዳቸው ነገሮች አሉ . . .

በተለይ የምኮራባቸው አንዳንድ ነገሮች. . .

አንዳንድ የማልወዳቸው ወይም ማስቀረት የምፈልጋቸው ነገሮች . . .

የሚከተለው ነገር ሲሆን ለእኔ አስቸጋሪ ጊዜ ይሆንብኛል . . .

የምወዳቸው እንቅስቃሴዎች . . .

የምወዳቸው ምግቦች . . .

ነገር ግን . . . እንድበላ አይጠይቁኝ ምክንያቱም እኔ (አልወድም ወይም አለርጂክ ነኝ) . . .

ቤት ስላለኝ አኗኗር በጥቂቱ . . . (በቤተሰብ ውስጥ ያለህን ቦታ፣ ስብእና፣ የምትወዳቸውንና የማትወዳቸውን ነገሮች ግለጽ)

ከእኔ ጋር ለመነጋገር በጣም ጥሩ መንገዶች . . .

ሌሎች ስለ እኔ እንዲያውቁ የምፈልገው በጣም ጠቃሚ ነገር . . .

# የተማሪ መዛግብት

# መዛግብትን መያዝ

እርስዎ የልጅዎ የትምህርት ቡድን ምርጥና ጠቃሚ አባል መሆንዎን ያውቃሉ፡፡ እርስዎ የልጅዎን የግል ታሪክ እንዲሁም የእሱ/የእሷ ጥንካሬ እና ፍላጎት ያውቃሉ፡፡ እርስዎ የልጅዎን ትምርታዊ፣ የህክምና እና የልዩ አገልግለሎት ታሪክ ያውቃሉ፡፡ እነዚህ መረጃዎች ስለ ልጅዎ ሌሎች እንዲያውቁ እና የተሻለ እንዲገነዘቡ ለማገዝ እንዲሁም ተገቢ አገልግሎቶችን እና ምንጮችን በመወሰን የልጅዎን የትምህርት ቡድንን ለማገዝ አግባቡነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

በርካታ ቤተሰቦች የትምህርት፣ የህክምና እንዲሁም የልዩ አገልግሎት መረጃዎችን ወቅታዊ ሆነው እንዲጠበቁ የግል "መዝገብ የመያዝ ስርአት" ማቋቋም ጠቃሚ ሆኖ አግኝተውታል፡፡
ቤሰቦች እነዚህ ቁልፍ አመላካቾች ይጋሯቸዋል፡

- ዘወትር ስለልጅዎ (የህክምና፣ የትምህርት፣ የአገልግሎት ዳሰሳ/ጥናት ወዘተ) ሪፖርቶች  ሰነዶች **ቅጅዎችን** መጠየቅና ማስቀመጥ
- መረጃውን **በጊዜ ቅደም ተከተል** ያደራጁ
- ሪፖርቶቹን እና መዛግብቶችን ለማስቀመጥ **ፋሎችን**፣ **የማስታወሻ ደብተር** እና/ወይም **የኤሌክትኖሪን ማስቀመጫ** ይጠቀሙ
- ልጅዎ ስም፣ የአገልግሎት ቀን፣ የአገልግሎት ዓይነት እና የተግባቦች መረጃን ጨምሮ በህይወት ዘመኑ የሚያገኘውን አገልግሎት በሙሉ **መዝግበው የያዙ**

ይህ መረጃ ልጅዎል ለመቆጣጠር ወይም ለመከታተል ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ መረጃ ለልጅዎ የትምህርት ቤቱን ማጋራት ተገቢነቱን ካመኑበት ቀጥሎ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎችና ዳታዎች በቀላሉ ለማግኘት ወይም ለማስታወስ ከመቸውም በላይ ዝግጁ መሆን ያስፈልገዋል፡፡

ልጅዎ ትምህርት ቤት ላይ የሚያገኘውን አገልግሎት ለመወሰን ከማገዙ በተጨማሪ ይህ መረጃ ልጅዎ ከትምህርት ቤት አደረጃጀት ወደ አዋቂነት እርከን በሚሸጋገርበት ጊዜ ለአዋቂዎች አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

# ስለ ልጁ የቅድመ ታሪክ መረጃ

*ይህ ቅጽ ተዘጋጅቶ የቀረበው ኢጋዥ መሳሪያ ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ለመጋራት ለሚፈልግ ቤተሰብ ነው፡፡ ይህ ቅጽ የልጅዎን ጠቃሚ መዝገቦች ለመከታተል እንዲያግዝዎ ለግል መጠቀሚያ የተዘጋጀ ነው፡፡ መረጃው ከልጅዎ የትምህርት ቡድን ጋር መጋራት ተገቢ ይሆናል ብለው ካሰቡ፣ ይህ ቅጽ ተገቢውን መረጃና ዳታን ለማግኘት ወይም ለማስታወስ ቀላል ያደርግልዎታል፡፡*

# የግምገማዎች/የምርመራ ሙከራ ማጠቃለያ

| ቀን | የተደረጉ ምርመራዎች | ልዩ ባለሙያ/መገልገያ፣ የመገኛ መረጃ | ቁልፍ ግኝቶች/ምርመራዎች/ውጤቶች |
|---|---|---|---|
| | | | |

*ይህ ቅጽ ተዘጋጅቶ የቀረበው ኢጋዥ መሳሪያ ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ለመጋራት ለሚፈልግ ቤተሰብ ነው፡፡ ይህ ቅጽ የልጅዎን ጠቃሚ መዝገቦች ለመከታተል እንዲያግዝዎ ለግል መጠቀሚያ የተዘጋጀ ነው፡፡ መረጃው ከልጅዎ የትምህርት ቡድን ጋር መጋራት ተገቢ ይሆናል ብለው ካሰቡ፣ ይህ ቅጽ ተገቢውን መረጃና ዳታን ለማግኘት ወይም ለማስታወስ ቀላል ያደርግልዎታል፡፡*

# የአገልግሎቶችና ህክምናዎች ማጠቃለያ

| የልዩ ባለሙያ ስምና ስልክ/ኢሜል | የሚሰጡ አገልግሎቶች፣ ድግግሞሽ፣ ቀናት |
| --- | --- |
| | |

# የሕክምና ማረጃ

*ይህ ቅጽ ተዘጋጅቶ የቀረበው ኢጋዥ መሳሪያ ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ለመጋራት ለሚፈልግ ቤተሰብ ነው፡፡ ይህ ቅጽ የልጅዎን ጠቃሚ መዝገቦች ለመከታተል እንዲያግዝዎ ለግል መጠቀሚያ የተዘጋጀ ነው፡፡ መረጃው ከልጅዎ የትምህርት ቡድን ጋር መጋራት ተገቢ ይሆናል ብለው ካሰቡ፣ ይህ ቅጽ ተገቢውን መረጃና ዳታን ለማግኘት ወይም ለማስታወስ ቀላል ያደርግልዎታል፡፡*

# መድሃኒቶች፣ ህመምና የህክምና ቀጠሮዎች

| ህመም/ምልክቶች/ስጋቶችና ቀናት | የታየበት/የታከመ በት የዶክተር ወይም ተቋም ስምና አድራሻ | የታዘዘ መድሃኒት፣ መጠን፣ ቀናት፣ ለምን እንደታዘዘ | ምላሾች/የጎንዮሽ ጉዶች |
|---|---|---|---|
| | | | |

*ይህ ቅጽ ተዘጋጅቶ የቀረበው አጋዥ መሳሪያ ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ለመጋራት ለሚፈልግ ቤተሰብ ነው። ይህ ቅጽ የልጅዎን ጠቃሚ መዝገቦች ለመከታተል እንዲያግዝዎ ለግል መጠቀሚያ የተዘጋጀ ነው። መረጃው ከልጅዎ የትምህርት ቡድን ጋር መጋራት ተገቢ ይሆናል ብለው ካሰቡ፣ ይህ ቅጽ ተገቢውን መረጃና ዳታን ለማግኘት ወይም ለማስታወስ ቀላል ያደርግልዎታል።*

# የወደፊት የሕክምና ቀጠሮዎችና ጥያቄዎች

| የቀጠሮ ቀን | ለምንና ከማን ጋር | ጥያቄዎች/አስተያየቶች |
|---|---|---|
| | | |

# የትምህርት ቤት ግምገማዎች

# የሂደት ሪፖርቶች

# የቀድሞ IEP

# የግል ሪፖርቶች

# ግብአቶች

# የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መርጃዎች

**የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ልዩ ትምህርት አገልግሎቶች**

https://www.apsva.us/student-services-special-education/special-education-office-of/

703-228-6040

የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የልዩ ትምህርት ቢሮ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች (ከ2 እስከ 22 አመት)፣ ለወላጆች፣ ለርእሰ መምህራንና ለትምህርት ቤት ሰራተኞች በግምገማ፣ በመለየት፣ በምደባ፣ በትምህርትና በሽግግር አገልግሎቶች ላይ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ APS ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች፣ ከቅድመ ትምህርት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ተከታታይ አገልግሎቶችን ያቀርባል፡፡ አንድን ተማሪ ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ መሆኑን ለመለየት የሚወሰዱት እርምጃዎች በስቴትና በፌደራል ደንቦች የሚመራ በጥንቃቄ የሚተዳደር ሂደት ነው፡፡

**የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ልዩ ትምህርት የወላጅ መርጃ ማእከል (PRC)**

https://ww.apsva.us/prc

703-228-7239

የ PRC አላማ የአርሊንግተን ወላጆች ከትምህርት ቤት ስርአት ጋር ሲሰሩ የልጃቸውን ልዩ የመማር ፍላጎት ለማሟላት ሲሰሩ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍና መረጃ መስጠት ነው፡፡ PRC ድጋፍና እርዳታ ማድረግ፣ የቤተመጻሕፍት ውሰት፣ የወላጅ ጋዜጣ፣ የወላጅ ትምህርት አውደ ጥናቶችና ትምህርታዊ ክፍሎች መስጠት፣ የአካል ጉዳተኛ ልጆች ወንድሞችና እህቶች የሱፐር ሲብስ ክለብ እንዲሁም ለቤተሰቦችና ሰራተኞች የመረጃና ሪፈራል ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የቋንቋ ትርጉም አገልግሎት አለ፡፡ በእያንዳንዱ ሕንጻ ውስጥ እንደ ልዩ ትምህርት የወላጅ ግንኙነት ሆነው የሚያገለግሉ ወላጆችን ለመለየት PRC ከአርሊንግተን SEPTA ጋር ይተባበራል፡፡ ማገናኛዎች በ PRC፣ SEPTA፣ የትምህርት ቤት PTAs እና የአካል ጉዳተኛ ልጆች ቤተሰቦች መካከል እንደ የመገናኛ ነጥቦችና የመረጃ ማስተላለፊያዎች ሆነው ያገለግላሉ፡፡

**የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የልጅ ፍለጋ ፕሮግራም**

https://www.apsva.us/student-services-special-education/special-education-office-of/child-find/

703-228-2700

በእውቀት፣ ተግባቦት፣ በመስማት፣ በእይታ፣ በማህበራዊ-ስሜታዊ ችሎታዎች እና/ወይም የሰውነት እንቅስቃሴ ክህሎቶች መዘግየቶች ይኖርባቸዋል ተብለው የተጠረጠሩ ልጆች፣ ልጁ ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ግምገማን ይፈልግ እንደሆነ ለማወቅ ወደ የተማሪ ጥናት ኮሚቴ ይላካሉ፡፡

**የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ የወላጅነት ፕሮግራሞች**

https://www.apsva.us/school-overviews/teenage-parenting-program/

703-228-8700

የእነዚህ ፕሮግራሞች ተልእኮ በአርሊንግተን ካውንቲ ውስጥ ለሚገኙ ነፍሰጡር እና ታዳጊ ወጣቶች የትብብር፣ አጠቃላይ አገልግሎቶችን አመራር መስጠት ነው፡፡ ፕሮግራሞቹ የድጋፍ ቡድን ስብሰባዎችን፣ መረጃዎችን፣ ግብአቶችንና የመዝናኛ ዝግጅቶችን ያቀርባሉ፡፡

**የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች - የትምህርት ቤት ቦርድ**

www.apsva.us/schoolboard

703-228-3456

የትምህርት ቦርዱ አምስት አባላትን ያቀፈ ሲሆን በተደራቢነት ለአራት ዓመት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ መደበኛ የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባዎች በወሩ የመጀመሪያና ሶስተኛ ሐሙስ በቦርድ ክፍል የትምህርት ማእከል 1426 N. Quincy Street ውስጥ ይደረጋሉ፡፡ የቦርድ ስብሰባዎች በቀጥታ በVerizon Channel 70 እና FIOS channel 41 የሚተላለፉ ሲሆን በሚቀጥለው አርብ በ9፡00 ፒኤም እና በሚቀጥለው ሰኞ በ 7፡30 ፒ.ኤም ይደገማሉ፡፡ በስብሰባዎች ወቅት ዜጎች ስርጭቱን ከድረገጽ ላይ ማውረድ ይችላሉ፡፡ የትምህርት ቤቱ ቦርድ ሰኞ 5፡00 ፒ.ኤም እስከ 7፡00 ፒ.ኤም ድረስ *ትምህርት ቤት በሚሰጥባቸው ቀናት* ክፍት የስራ ሰዓቶችን ናቸው፡፡ ዜጎች በእነዚህ ጊዜያት ከቦርድ አባል ጋር በመገናኘት እንዲገናኙ እና ለበለጠ መረጃ ወደ ትምህርት ቤት ቦርድ ቢሮ እንዲደውሉ ተጋብዘዋል፡፡

# የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች ኮሚቴዎች/ማህበራት

**የአርሊንግተን ልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ (ASEAC)**
https://www.apsva.us/special-education-advisory-committee/
ASEAC የተቋቋመው በቨርጂኒያ ስቴት ውስጥ ሲሆን አላማውም በአካል ጉዳተኛ ልጆች ትምህርት APS ያልተሟሉ ፍላጎቶች ላይ ለማማከርና የአካል ጉዳተኛ ልጆችን አፈጻጸም ለማሻሻል እቅዶችን በማዘጋጀትና በማዳበር ላይ ለማገዝ ነው፡፡ ASEAC በወላጅ የሚመራ ኮሚቴ በየወሩ የሚሰበሰብና ለቤተሰቦች ስጋቶችን ለማንሳት፣ ባለስልጣናትን ለማሳተፍ፣ ለመተባበርና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ወክሎ ለመሟገት ይፋዊ መድረክን የሚሰጥ ነው፡፡

**የአርሊንግተን ልዩ ትምህርት የወላጅ መምህራን ማህበር (አርሊንግተን SEPTA)**
www.ArlingtonSEPTA.org
ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆችና የአርሊንግተን ልዩ ትምህርት ፕሮግራሞችን ለመደገፍ፣ ለማጠናከርና ለማበረታታት የአርሊንግተን SEPTA በ 2010 ተቋቋመ፡፡ የ SEPTA አባልነት ለአንድ ትምህርት ቤት ብቻ የተወሰነ ያይደለና ይልቁንም በአርሊንግተን ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ትምህርት ቤቶች የሚገለግል ነው፡፡ አባላት ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች፣ ተንከባካቢዎች፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ጓደኞችና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለመደገፍ ፍላጎት ያላቸውን የማህበረሰብ አባላት አካተው ይዘዋል፡፡ የአርሊንግተን SEPTA እንደ ስሜታዊ ተስማሚ የፊልም ማሳያ፣ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎችና ማህበራዊ ስብሰባዎች ያሉ ዝግጅቶችን የሚያደራጅና ለመምህራን አነስተኛ ድጎማዎችን መስጠትን ጨምሮ ትምህርታዊ ተነሳሽነቶችን ለመደገፍ ገንዘብ ይሰበስባል እንዲሁም በአርሊንግተን ውስጥ ለዝግጅት አቀራረብ ዋና ባለሙያዎችን ያመጣል፡፡

# ቁልፍ ህትመቶችና መርጃዎች

***የወላጅ የልዩ ትምህርት መመሪያ፣*** የቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል (VDOE)፣ የልዩ ትምህርት እና የተማሪ አገልግሎት ክፍል፣ የተሻሻለው 2010
www.doe.virginia.gov/special_ed/parents/parents_guide.pdf

***ለአካል ጉዳተኛ ልጅዎ የወደፊት እድልን ማስጠበቅ፡ በአሌክሳንድሪያ ከተማና አርሊንግተንና ፌርፋክስ ካውንቲዎች ውስጥ የአዋቂዎች አገልግሎት የወላጅ መመሪያ፣*** የሰሜን ቨርጂኒያ አርክ፣ ሕዳር 2010፣
https://thearcofnova.org/content/uploads/sites/6/2015/08/SECURING-March2015Update.pdf

***የልዩ ትምህርት የቤተሰብ ግብአትና መረጃ ጠራዥ፡*** የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች 2012፣ የተሻሻለው 2016
www.apsva.us/prc/family resource guide/

**የስልጠና/የቴክኒክ ድጋፍ ማእከላት (T/TAC)** መርጃዎች፣ ነጻ የመስመር (ኦንላይን) ላይ የስልጠና ሞጁሎች እንዲሁም የትምህርት እድሎችን ለማሻሻልና ለአካል ጉዳተኛ ልጆችና ወጣቶች ስኬት አስተዋጽኦ ለማድረግ የተነደፈ የቴክኒክ ድጋፍ (ከውልደት - 22 አመት) ያቀርባል፡፡
www.ttaconline.org

*ይህ የፕሮግራሞች፣ ቢሮዎች፣ ድርጅቶችና እድሎች ዝርዝር ለመረጃ አገልግሎት ብቻ ተብሎ የቀረበ ሲሆን ከአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች ወይም ከአርሊንግተን ካውንቲ ድጋፍ እንዳለው ኢድርጎ ወይም እሱን በሚያመለክት መልኩ መተርጎም የለበትም፡፡*

***ቤተሰብዎ የሚኖረው የልዩ ትምህርት መብቶች - የቨርጂኒያ የስርአት ጥበቃዎች ማሳሰቢያ፣*** የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE)፣ http://www.doe.virginia.gov/special_ed/regulations/state/procedural_safeguards/english_procedural_safeguards.pdf

ኦቲዝም ስፒክስ ***የ 100 ቀን ስብስብ*** እና ***አስፐርገር ሲንድሮም እና በፍተኛ ደረጃ የሚሰራ የኦቲዝም መሳሪያ ስብስብ*** ልጃቸው ኦቲዝም ወይም AS/HFA እንዳለበት ከታወቀ በኋላ ባሉት 100 ቀናት ውስጥ በተቻለ መጠን ለመጠቀም አዲስ ምርመራ ለሚያደርጉ ቤተሰቦች መሳሪያዎችን ያቀርባሉ፡፡ www.autismspeaks.org/family-services/tool-kits/100-day-kit

***የኦቲዝም ስፔክትረም መታወክና ወደ አዋቂነት መሸጋገር፡*** የቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል (VDOE) የልዩ ትምህርትና የተማሪ አገልግሎት ቢሮ፣ ጥቅምት 2010 www.doe.virginia.gov/special_ed/disabilities/autism/

***የኦቲዝም ስፔክትረም መታወክ ያለባቸውን ተማሪዎች የማስተማሪያ መመሪያ፡*** የቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል (VDOE) የልዩ ትምህርትና የተማሪ አገልግሎት ቢሮ፣ ጥቅምት 2010 www.doe.virginia.gov/special_ed/disabilities/autism/

***Models of Best Practices in the Education of Students with Autism Spectrum Disorders***, Virginia Department of Education (VDOE) Office of Special Education and Student Services, May 2011 www.doe.virginia.gov/special_ed/disabilities/autism/

**የቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ ዩኒቨርሲቲ የኦቲዝም የልህቀት ማእከል (VCU-ACE)** በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያና በባህሪ ጤናና ልማት አገልግሎቶች መምሪያ (DBHDS) የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ነው፡፡ VCU-ACE ለትምህርት ቤቶችና ቤተሰቦች የስልጠና ሞጁሎችንና የመስመር (ኦንላይን) ላይ የሚያበድሩ ቤተመጻሕፍትን ከVCU ማገገሚያ ጥናትና ስልጠና ማእከል ጋር በመተባበር በስራ ቦታ ድጋፍና በስራ መያዝ ላይ ያቀርባል፡፡ www.vcuautismcenter.org

# የአርሊንግተን ካውንቲ ፕሮግራሞች እና ቢሮዎች

**የአርሊንግተን ካውንቲ የባህሪ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት (BIS)**
703-228-1539
የዚህ ፕሮግራም ተልእኮ የባህሪ አስተዳደር አገልግሎቶችን ለሚፈልጉ ልጆች የበለጠ ገዳቢ ፕሮግራም ወይም ከቤት ውጭ ምደባን መከላከል የሚገኝ ነው፡፡ ልዩ ባለሙዎች ወላጅ ወይም ተንከባካቢዎችን የሚያስተምሩና የሚያአለጥኗቸው እንደ ራስን የመጉዳት ባህሪ፣ ጠበኝነት፣ ታዛዥ አለመሆንና ንዴት የመሳሰሉ አሳሳቢ ባህሪያትን በሚመለከቱ የባህሪ አስተዳደር ዘዴዎች ላይ ነው፡፡

**የአርሊንግተን ካውንቲ የባህሪ ጤና አጠባበቅ**
https://health.arlingtonva.us/behavioral-healthcare/
703-228-3000
የአርሊንግተን ነዋሪዎች የአደጋ ጊዜ አገልግሎቶችን፣ የአዋቂዎች የአእምሮ ጤና እና የቀውስ ጣልቃ ገብነትን ጨምሮ የአይምሮ ጤንነታቸውንና የአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም ጉዳዮችን እንዲያሸንፉ ወይም በተሻለ ሁኔታ እንዲቆጣጠሩ ለመርዳት የተለያዩ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች አሉ፡፡

**የአርሊንግተን ካውንቲ የሕጻናት እንክብካቤ ቢሮ**
https://family.arlingtonva.us/child-care/
703-228-1685

ይህ ቢሮ ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን እንዲደግፉ ለመርዳት ብዙ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ነው፡፡ በአርሊንግተን ካውንቲ ደንብ በምዕራፍ 52፣ "የህጻናት ማቆያ ማእከላት፣ ቅድመ ትምህርት ቤቶች፣ የህጻናት ትምህርት ቤቶች፣ የወላጅ ቀን መውጫ ፕሮግራሞችና የትብብር የጨዋታ ቡድን ፕሮግራሞች" ስር በየአመቱ ፈቃድ ያላቸው የቅድመ ልጅነት ፕሮግራሞችና የቤት ውስጥ እንክብካቤ አቅራቢዎች ማውጫን ያዘጋጃል፡፡

### የአርሊንግተን ካውንቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ቦርድ (ACCSB)

https://commissions.arlingtonva.us/community-services-board/

703-228-4871

የአርሊንግተን ካውንቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ቦርድ (ACCSB) በአእምሮ ጤና፣ በአእምሮ እክልና በአደንዛዥ እጽ አላግባብ መጠቀም ለተቸገሩ ሰዎች በሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ የሚሰጠውን አገልግሎት እንዲቆጣጠሩ የተሾሙ የማህበረሰብ አባላትን አቅፎ የያዘ ነው፡፡ ACCSB ለነዋሪዎችና የአገልግሎቶች ሸማቾች የአገልግሎቶቹን አቅጣጫ እንዲገመግሙ፣ አስተያየት እንዲሰጡና ተጽእኖ እንዲያደርጉበት የርእሰ መምህር ፎረም ያቀርባል፡፡ ACCSB እንደ ጠበቃ፣ አስተማሪ፣ የማህበረሰብ አደራጅና የአገልግሎቶች የማህበረሰብ እቅድ አውጪ ሆኖ ይሰራል፡፡

### የአርሊንግተን ካውንቲ የፓርኮች፣ የመዝናኛና የባህል ሀብቶች መምሪያ የመዝናኛ መዝናኛ (TR)

https://parks.arlingtonva.us/therapeutic-recreation/

703-228-4740

የአርሊንግተን ካውንቲ በሁሉም እድሜ ላይ ለሚገኙ አካል ጉዳተኞች ልዩ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ ለአካላዊ፣ ማህበራዊ ወይም አእምሯዊ ችግሮች ተጋላጭ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው፡፡ ልዩ አገልግሎቶች ማህበራዊ ክበቦችን፣ ቤተሰብን ያማከለ ፕሮግራም፣ ካምፖች፣ የተስተካከሉ ክፍሎችና የመዝናኛ ትምህርትን ያካትታሉ፡፡ በካውንቲው አጠቃላይ የመዝናኛ ፕሮግራሞች ላይ ለመሳተፍ ሁሉም ሰው ተጋብዟል፡፡ በሁሉም DPR እና በኮንትራት ፕሮግራሞች ውስጥ ምክንያታዊ መስተንግዶ መደረጉን ለማረጋገጥ የ TR ቢሮ ለአካል ጉዳተኞች በአውደ ጥናቶች፣ ካምፖችና ክፍሎች ውስጥ አካታች ድጋፍ ይሰጣል፡፡

### የአርሊንግተን ካውንቲ ቤተሰቦች

https://family.arlingtonva.us/arlingtonfamilies-com/

703-228-1550

የአርሊንግተን ቤተሰቦች በአርሊንግተን፣ ቨርጂኒያ ቤተሰብ ውስጥ ስለሚሆነው ነገር ለወላጆችና ተንከባካቢዎች መርጃዎችን ይሰጣል፡፡ የመጫወቻ ቦታ ለማግኘት ድረገጹን ይጎብኙ፤ በአውደ ጥናት ውስጥ ከሌሎች ወላጆች ጋር ይገናኙ፤ ስለትምህርት ቤት አማራጮች ይወቁ፤ በሳምንቱ መጨረሻ አንድ አስደሳች ነገር ያግኙ ወይም ከተግባራዊ የወላጅነት ምክሮችና ሀሳቦች ጋር ግንኙነት ይፍጠሩ፡፡ መረጃው የእድሜ ቡድንን መሰረት በማድረግ የተደራጀ ነው፡፡

### የአርሊንግተን ካውንቲ አእምሯዊና የእድገት የአካል ጉዳት አገልግሎቶች

https://aging-disability.arlingtonva.us/programs/dev-disability/

703-228-1700

የአርሊንግተን ካውንቲ ዕድሜያቸው 3 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ነዋሪዎችና የአእምሮ ችግር እና/ወይም የእድገት እክል ላለባቸው አዋቂዎችና ቤተሰቦቻቸው የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ለማግኘት እና ለመጠቀም እርዳታ ይሰጣል፡፡ አገልግሎቶቹ ተገቢ አገልግሎቶችን ለማግኘት የድጋፍ ማስተባበርን ሊያካትቱ ይችላሉ፤ ነፃነትን ከፍ ለማድረግ አድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የመኖሪያ አገልግሎቶች ይኖራል፤ ስራ፣ ማቋቋሚያና ማኳኳዣ አዋቂዎች ለተግባራዊ ክህሎቶች እና እራስን መቻልን ለማሳደግ ትርጉም ባለው ስራ እና/ወይም ስልጠና ላይ መሳተፍ እንዲችሉ ይደረጋል፡፡ አገልግሎቶቹ በገንዘብ አቅርቦትና በብቁነት መስፈርቶች ላይ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

### የአርሊንግተን ካውንቲ የወላጅነት መርጃዎች

https://family.arlingtonva.us/early-childhoodparent-resources/

703-228-1551

ይህ ፕሮግራም ለቤተሰቦች ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ጤናማ እና እንክብካቤ መስጫ አካባቢ እንዲኖር ለማድረግ የሚረዱ መሳሪያዎችን፣ ስልቶችንና ክህሎቶችን ይሰጣል፡፡ ፕሮግራሙ ክፍሎች፣ አውደ ጥናቶች፣ የመስመር (ኦንላይን) ላይ ፕሮግራም እንዲሁም መረጃና ሪፈራል አገልግሎቶችን ለሌሎች የአርሊንግተን ካውንቲና ሰሜናዊ ቨርጂኒያ መርጃዎች በእንግሊዝኛና በስፓኒሽ ያቀርባል፡፡

**የአርሊንግተን ካውንቲ የወላጅ-ጨቅላ ትምህርት (PIE) ፕሮግራም**
https://health.arlingtonva.us/public-health/health-clinics-services/parent-infant-education-program-pie/
703-228-1630
የ PIE መርሃ ግብር አላማ የእድገት መዘግየቶችና የአካል ጉዳተኞች እድገት በጨቅላ ህጻናትና ታዳጊ ህጻናት እድገት ላይ ከውልደት እስከ 2 አመት እድሜ ድረስ ለቤተሰቦች የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን መስጠት ከልጃቸው ጋር ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲሰሩ መርዳት ነው፡፡

**የአርሊንግተን ካውንቲ ፕሮግራም ለሴቶች፣ ጨቅላ ህጻናት እና ህፃናት (WIC)**
https://health.arlingtonva.us/public-health/health-clinics-services/women-infants-children-wic-program/
703-228-1260
ይህ በፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት መርሃ ግብር የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን መከላከልና በአገልግሎት ሰጪዎች መካከል የተሻለውን እድገትና ልማትን መደገፍ እንደ አላማው አድርጎ የተነሳ ነው፡፡ መርሃግብሩ ቀጥተኛ የተመጣጠነ ምግብ ማሟያዎችን፣ የተመጣጠነ ምግብን ትምህርትና የጤና እንክብካቤ እንዲሁም ማህበራዊ አገልግሎቶችን ተደራሽነት ህክምና ለሚያፈልጋት ነፍሰ ጡር፣ ጡት ለሚያጠቡና ድሕረ ወሊድ ላይ ላሉ ሴቶች ጨቅላ ልጆቿና ታዳጊ ልጆቿ እስከ አምስት አመት እድሜ ድረስ ይሰጣል፡፡

**የአርሊንግተን ካውንቲ ፕሮጀክት ቤተሰብ**
https://family.arlingtonva.us/project-family/
703-228-1549
የፕሮጀክት ቤተሰብ ነጻ የቅድመ ልጅነትና የወላጅነት ፕሮግራም ሲሆን ከውልደት ጀምሮ እስከ አምስት አመት እድሜ ድረስ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ሳምንታዊ የቅድመ ወሊድ፣ የጨቅላና የቅድመ ልጅነት ትምህርቶችን ይሰጣል፡፡
ክፍሎች አሳታፊና በቀላሉ በአርሊንግተን ካውንቲ ባሉ ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ የፕሮጀክት ቤተሰብ በልጁ ላይ ጠቅላላ ትኩረት የሚያደርግና ወላጆች የልጁን አካላዊ፣ ቋንቋ፣ የግንዛቤና ማህበራዊ-ስሜታዊ እድገት ለማሳደግ እንቅስቃሴዎችን የሚያስተምር ሲሆን ይህም የዘወትር ተግባራትንና በጨዋታ የመማርን አስፈላጊነት ላይ አጽንኦት ይሰጣል፡፡ ትምህርቶቹ ባህልን ከግምት የሚያስገቡ፣ ድጋፍና የግንኙነት እድሎችን የሚሰጡ እንዲሁም ወላጆችን ከልጆች እድገት፣ ጤና፣ ደህንነትና አመጋገብ ጋር በተያያዙ በጣም ጠቃሚ ልምዶችን ያስተዋውቃሉ፡፡ ትምህርቶቹ በስፓኒሽ፣ በእንግሊዝኛ እና በሁለት ቋንቋ ይሰጣሉ፡፡

**የአርሊንግተን አጋርነት ለልጆች፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች (APCYF)**
https://apcyf.arlingtonva.us/
703-228-1667
የAPCYF ተልእኮ በአርሊንግተን ውስጥ የህጻናትን፣ ወጣቶችንና ቤተሰቦችን ጤና፣ ደህንነትና ደህንነት ማሻሻል የወጣቶችን ፍላጎት በመመርመር፣ የተሻሻሉ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን በመደገፍ እነዚያን ፍላጎቶች ለማሟላት እንዲሁም ሁሉንም የማህበረሰባችን አባላት እንደ የመፍትሄው አካል አድርጎ ማሳተፍ ነው፡፡

# የአርሊንግተን የድጋፍ ቡድኖችና ኔትዎርኮች

**አርሊንግተን ADHD ድጋፍ ቡድን እና ሊስትሰርቨር**
የአርሊንግተን የ ADHD ድጋፍ ቡድን ADHD/ADD ያለባቸው ልጆች ወላጆች/አሳዳጊዎች መረጃንና መርጃዎችን፣ ልምድንና ምክሮችን እንዲያካፍሉ ነው፡፡ ወላጆች/አሳዳጊዎች ልምድ ያካፍላሉ፣ ልጆችን የረዱ ቴክኒኮችን ይወያያሉ እንዲሁም ሀሳብ ይለዋወጣሉ፡፡ ስብሰባዎች አልፎ አልፎ የሚካሄዱ ሲሆን ነገርግን አብዛኛው ግንኙነት በ listserver በኩል ይደረጋል፡፡ listserver ለመቀላቀል፣ ናዲን አሰፍ-ሳርጀንትን በ nadine.asef@gmail.com ያግኙ፡፡

**አርሊንግተን ኦቲዝም አባቶች ቡድን**
ይህ ኦቲዝም ላለባቸው ልጆች መረጃን፣ ልምዶችንና ድጋፍን ለመለዋወጥ የሚፈልግ ቡድን ነው፡፡ ዳን ማርክስን በ autismdadsgroup@gmail.com ወይም dwmarx@gmail.com ያግኙ፡፡

**አርሊንግተን ኦቲዝም ቡድን (AAG) እና ሊስትሰርቭ**
AAG የቤተሰብ ድጋፍ ቡድንና የኦቲዝም መረጃ ሊስትሰርቭ ነው፡፡
ቡድኑ ጽሑፎችንና ምርምርን ያጋራል፣ የዝግጅት ማስታወቂያዎችን ያሰራጫል እንዲሁም በአርሊንግተን ካውንቲ ውስጥ የጥብቅና ስራዎችን እንዲሁም አልፎ አልፎ በአመቱ ውስጥ የማህበራዊ ዝግጅቶችን በማዲሰን ማኖር ፓርክ ቡና፣ ምሳንና አመታዊ የበጋ ፖትሉክ በማዘጋጀት ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ዶና በድዌይን በ donnabudway@aol.com ያግኙ፡፡

**አርሊንግተን አካታች ግብረሃይል**
በወላጅ የሚመራው የአርሊንግተን አካታች ግብረ ኃይል በ የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) ውስጥ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ትክክለኛና የተደገፈ አካታች እድሎችን ለመጨመር በሰኔ 2014 ተመሰረተ፡፡ ታውና ዛማንስኪን በ arlingtoninclusion@gmail.com ያግኙ፡፡

**አርሊንግተን የማንበብ ቡድን**
https://groups.yahoo.com/neo/groups/ArlingtonReading/info
ይህ በአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የማንበብ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ወላጆች የድጋፍ ቡድን ነው፡፡ ቡድኑ ለአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መምህራንና አስተዳደር ክፍት ነው፡፡ አባላት ልጆች እንዲያነቡ ለመርዳትና ከትምህርት ቤቱም ሆነ ከስርአቱ ውጪ የሚፈልጉትን ግብአትና ድጋፍ ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት በምክርና መረጃ በመለዋወጥ እርስ በርስ ይደጋገፋሉ፡፡

**የአርሊንግተን ልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ (ASEAC)**
https://www.apsva.us/special-education-advisory-committee/
ASEAC የተቋቋመው በቨርጂኒያ ስቴት ሲሆን የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ትምህርት ያልተሟሉ ፍላጎቶችን APSን ለመምከር እና የአካል ጉዳተኛ ልጆችን አፈፃፀም ለማሻሻል ዕቅዶችን በማዘጋጀትና በማዳበር ላይ እገዛን ያደርጋል፡፡ ASEAC በየወሩ የሚሰበሰብና ባለስልጣናትን ለማሳተፍ ስጋቶችን ለማንሳት ለቤተብ ይፋዊ መድረክ የሚሰጥና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ወክሎ በተሟጋችነት የሚተባበር በወላጅ የሚመራ ኮሚቴ ነው፡፡

**የአርሊንግተን ልዩ ትምህርት የወላጅ መምህራን ማህበር (አርሊንግተን SEPTA) እና ሊስትሰርቭ**
www.ArlingtonSEPTA.org
ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች እና የአርሊንግተን ልዩ ትምህርት ፕሮግራሞችን ለመደገፍ፣ ለማጠናከር እና ለማበረታታት የአርሊንግተን SEPTA በ 2010 ተቋቋመ፡፡ የ SEPTA አባልነት ለአንድ ትምህርት ቤት ብቻ ተብሎ የተገደበ አይደለም ይልቁንም በአርሊንግተን ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ትምህርት ቤቶች የሚያገለግል ነው፡፡ አባላት ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች፣ ተንከባካቢዎች፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ጓደኞች እና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለመደገፍ ፍላጎት ያላቸውን የማህበረሰብ አባላት አካተው ይይዛሉ፡፡
የአርሊንግተን SEPTA እንደ ስሜታዊ ተስማሚ የፊልም ማሳያዎች፣ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች እና ማህበራዊ ስብሰባዎች ያሉ ዝግጅቶችን ያዘጋጃል እንዲሁም ለመምህራን አነስተኛ ድጎማዎችን መስጠትን እና መሪ ባለሙያዎችን በጣም ጥሩ ዘዴዎችን ወደ አርሊንግተን ማምጣትን ጨምሮ የትምህርት ተነሳሽነትን ለመደገፍ ገንዘብ ያሰባስባል፡፡

**አስፐርገርስ ህመም መረጃና ድጋፍ (ASIS) ቡድንና ሊስትሰርቭ**
https://groups.yahoo.com/neo/groups/ArlingtonASIS/info
ASIS በሰሜን ቨርጂኒያ ውስጥ ለወላጆች፣ ለአያቶች እና አስፐርገርስ ሲንድሮም ያለባቸው ልጆች ተንከባካቢዎች፣ ከፍተኛ የሚሰራ ኦቲዝም ወይም የቃል ላልሆኑ የመማር እክል ያለባቸው ልጆች የመስመር (ኦንላይን) ላይ የውይይት ቡድን ነው፡፡ እድሜያቸው ከ3-30 ዓመት የሆኑ ልጆች ያሏቸው ከ150 በላይ ቤተሰቦች የዚህ ቡድን አካል ናቸው፡፡

**የሰሜን አርሊንግተን እናቶች (MONA) - ልዩ የእናቶች ድጋፍ ቡድንና ሊስትሰርቭ**

www.monamoms.org

ይህ ቡድን ወላጆች እንዲገናኙና ምክርን፣ ስጋቶችንና ድጋፍን እንዲለዋወጡ እድል ይሰጣል። ቡድኑ የተቋቋመው በሰሜን አርሊንግተን ቢሆንም፣ በስቴቱ የመጡ የቤተሰብ አባላት ይቀበላል። ቡድኑ በሊስትሰርቨር ላይ መረጃን ያካፍላል እንዲሁም በየወሩ የመጀመሪያ አርብ በ 9 ኤኤም ላይ ይገናኛል። ካትሪን ሃሪስን በ harriskath@gmail.com ያግኙ።

**ብሔራዊ የአእምሮ ሕመም ጥምረት (NAMI)**

NAMI ስለ ልጅ፣ በአስራዎቹ እድሜ ያለ ታዳጊ፣ ወጣት አዋቂ ወይም ሌላ የሚወዱት ሰው ከአእምሮ ጤና ሁኔታዎች ጋር ለሚታገል ለወላጆችና ለሌሎች ተንከባካቢዎች የተለያዩ ከክፍያ-ነጻ የድጋፍ ቡድኖችንና ክፍሎችን ይሰጣል። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- እድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች ላሏቸው ወላጆች የድጋፍ ቡድን (ከቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እስከ 12 ክፍል)። ይህ የድጋፍ ቡድን በወሩ 2ኛ እና 4ኛ እሁድ ከ 7፡00 ፒኤም እስከ 8፡30 ፒኤም በቼሪዴል ባፕቲስት ቤተክርስትያን፣ 3910 Lorcom Lane፣ Arlington ይገናኛል። ለበለጠ መረጃ ሚሼል ቤስትን በ mczero@yahoo.com ያግኙ።

- የድጋፍ ቡድን ለወላጆች፣ በአስራዎቹ እድሜ ያሉ ታዳጊዎችና አዋቂዎች። ይህ የድጋፍ ቡድን በየወሩ ሶስተኛውን እሁድ ከ1፡00 ፒኤም እስከ 2፡30 ፒኤም በትሪኒቲ ፕሪስባይቴሪያን ቤተክርስቲያን፣ 5533 N. 16th St, Arlington ይገናኛል። ለበለጠ መረጃ ናኦሚን ቨርዱጎን በ verdugo.naomi@gmail.com ወይም 703-862-9588 ያግኙ።

- የስፓኒሽ ቋንቋ ድጋፍ ቡድን። ይህ የድጋፍ ቡድን በየወሩ የመጨረሻውን እሮብ ከ 7፡00 እስከ 9፡00 ፒኤም በሜሪፊልድ ሴንተር፣ Willow Oaks Corporation Dr., Room #1-328, Fairfax, VA ይገናኛል። ለመመዝገብና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ሮሲታ ክሊን፣ MSW፣ በ 703-256-7021 ወይም r.arancibiakline45@gmail.com ያግኙ።

# የሰሜን ቨርጂኒያ ድጋፍ ሰጪ ቡድኖች

**ACCESS የማክሊን መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን አገልግሎት**

http://mbctysons.org/pages/page.asp?page_id=84047

703-639-2000

ACCESS ሚኒስቴር "Breakout Fridays" እና "Breakout Saturdays" (ወርሃዊ እረፍት) እና የወላጅ ለወላጅ ድጋፍ ቡድንን ጨምሮ ለልዩ ፍላጎት ቤተሰቦች አገልግሎት ይሰጣል። አመታዊው የተደራሽነት ጉባኤ ለወላጆችና ለባለሞያዎች የሚዘጋጅ የአካል ጉዳት ጉባኤ ነው።

**አለርጂና አስም ኔትዎርክ የአስም እናቶች**

www.aanma.org, info@aanma.org

1-800-878-4403

ይህ ቡድን በአስም፣ በአለርጂዎች፣ በምግብ አለርጂዎችና ተዛማጅ ሁኔታዎች ውስጥ ለሚኖሩ ታካሚዎችና ቤተሰቦች ድጋፍን በስልክና በኢሜል ጥያቄዎችን በመመለስ መረጃን፣ ግብዓቶችን፣ ጋዜጣዎችንና መጽሄቶችን ያቀርባል። ብዙ ህትመቶች በስፓኒሽ ይገኛሉ።

**የታላቁ ዋሽንግተን አስፐርገር አዋቂዎች**
www.aagw.net
AAGW እድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ የሆኑ በስቴቱ ውስጥ ለሚኖሩና አስፐርገርስ፣ ከፍተኛ ኦቲዝም፣ የቃል ያልሆነ የመማር ችግር፣ የትርጉም ፕራግማቲክ መታወክ ወይም PDD-NOS ላለባቸው አዋቂዎች ድጋፍ የሚያደርግና ማህበራዊ ቡድን ነው፡፡ ቡድኑ በየወሩ ይገናኛና በመጀመሪያው ስብሰባቸው ላይ የሚሳተፉ አባላት የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ይዘው መምጣት ይችላሉ፡፡ ማርክን በ info@aagw.net ያግኙ፡፡

**የሰሜን ቨርጂኒያ ኦቲዝም ማህበር (ASNV)**
www.asnv.org
703-495-8444
ASNV ኦቲዝም ላለባቸው በሁሉም እድሜ ክልል ላሉ ዜጎች ይሟገታል፤ ለቤተሰብና ለተንከባካቢዎች ድጋፍ ያደርጋል፤ የትምህርት፣ የሙያ ስልጠና፣ የመኖሪያ ቤት፣ የመጓጓዣ፣ የመዝናኛና ሌሎች በህይወት ላይ የሚኖሩ ፍላጎቶችን ተደራሽነት ያረጋግጣል፤ ስለ ኦቲዝም መረጃን ለመሰብሰብና ለማሰራጨት እገዛ ያደርጋል እንዲሁም ኦቲዝም ያለባቸው አዋቂዎችን፣ ወላጆችንና ኦቲዝም ያለባቸውን ሰዎች ወንድምና እህቶች መብት ያጠናክራል፡፡ Info@asnv.org፣ assistant.director@asnv.org ወይም director@asnv.org ያግኙ፡፡

**የአንጎል ጉዳት አገልግሎቶች ማህበር**
www.braininjurysvcs.org
703-451-8881
የአእምሮ ጉዳት አገልግሎቶች ልጆችና ጎልማሶች የአእምሮ ጉዳት ያለባቸው ሰዎች የተሟላና ውጤታማ ህይወት ለመምራት የሚያስፈልጋቸውን ችሎታና በራስ መተማመን እንዲገነቡ ያግዛል፡፡

**ዲሴብሊቲ ስኩፕ**
www.disabilityscoop.com
ይህ ድረገጽ ስለ ኦቲዝም፣ የአእምሯዊ እክል፣ ሴሬብራል ፓልሲ፣ የአእምሮ መዘግየትና ሌሎችም ወቅታዊ ታሪኮችን ሽፋን አካቶ ከእድገት አካል ጉዳተኞች ማህበረሰብ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ዜናዎችና መረጃዎችን ያቀርባል፡፡

**የሰሜን ቨርጂኒያ የአእምሮ መዘግየት ማህበር (DSANV)**
www.dsanv.org
የዚህ ድርጅት አላማ ሁሉም የአእምሮ መዘግየት ያለባቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦቻቸው በማህበረሰባቸው ውስጥ ለመሳተፍ፣ አስተዋጽኦ ለማበርከትና የህይወት እርካታን ለማግኘት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡

**ትምህርት፣ መረጃ እና ክንውኖች – በየሁለት ሳምንቱ በኦቲዝም ላይ መጽሄድ**
የአካባቢው ነዋሪና የሰሜን ቨርጂኒያ የኦቲስቲክ ልጆች ወላጆች መስራች ተዛማጅ ዜናዎችን፣ ጽሁፎችን፣ ጥናቶችን እንዲሁም ለኦቲዝም ማህበረሰቡን የሚሰቡ ክስተቶችን የሚዘረዝር በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ የሚዘጋጅ የኢሜል መረጃ ያጠናቅራል፡፡ ሁሉን አቀፍ ጽሁፎች የሚቀርቡት በነጻ ነው፡፡ CampbellsServices@gmail.com ያግኙ፡፡

**የመስማት ችግር ድጋፍ ቡድን እና ሊስትሰር**
kidswithhearingloss-subscribe@yahoogroups.com

**የጁዊሽ ማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ**
www.jssa.org
JSSA ሰፋ ያለ የምክር፣ የትምህርትና የሙያ አገልግሎቶች፣ የቤት ውስጥ ድጋፍ፣ ሆስፒስና ነርሲንግ እንክብካቤ እንዲሁም ከፍተኛ ችሎታ ባለውና ተንከባካቢ የአእምሮ ጤናና የነርስ ባለሙያዎች የሚሰጡ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ያቀርባል፡፡ JSSA በአመት ከ 25,000 ለሚበልጡ ከትንሽ ጀምሮ እስከ አዛውንት ድረስ ላሉ ግለሰቦች አገልግሎትና ድጋፍ ይሰጣል፡፡ JSSA በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦችን ያገለግላል፡፡

**ብሄራዊ ካፒታል አካባቢ፡ የአስፐርገር/ከፍተኛ ኦቲዝም የወላጅ ድጋፍ ቡድኖች**
aspergers_nca@hotmail.com

**የሰሜን ቨርጂኒያ መስማት ለተሳናቸውና የመስማት ችግር ያለባቸው ሰዎች ማህበር (NVRC)**
www.nvrc.org, info@nvrc.org
NVRC አቀራረቦችን፣ የመቋቋሚያ ክህሎት ክፍሎችን፣ የቴክኖሎጂ ማሳያዎችን፣ ኤግዚቭኖችንን፣ የኢሜል ዜና አገልግሎትን፣ የግል ማማከርንና ሌሎችንም ጨምሮ ሰፊ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡

**የሰሜን ቨርጂኒያ ብዙሃን ወላጆች (NVPOM)**
membership@nvpom.com
ይህ ድርጅት ለብዙሃን ወላጆችን ምግብና መጠጥ ያቀርባል፡፡ የአባልነት ጥቅማጥቅሞች ወርሃዊ ስብሰባዎች፣ ወርሃዊ ጋዜጣ፣ አዲስ የእናቶች ቡድን፣ ሊስትሰርቭ፣ የጋራ ሀሳቦችና ልምዶች እና ሌሎችንም ያካትታሉ፡፡

**የመስመር (ኦንላይን) ላይ አስፐርገርስ ህመም መረጃና ድጋፍ (OASIS)**
www.aspergersyndrome.org
የOASIS ማእከል የአስፐርገር ህመም፣ ኦቲዝምና የተስፋፋ የእድገት መታወክ/ያልተገለጸ (PDD/NOS) ችግሮችን ለሚቋቋሙ ቤተሰቦች፣ ግለሰቦችና የህክምና ባለሙያዎች ከ MAAP አገልግሎቶች ለኦቲዝምና አስፐርገር ሲንድረም ጋር ተቀላቅሏል፡፡ ድረገጹ ስለ ሕክምናዎች፣ ትምህርት ቤቶችና ተዛማጅ ጉዳዮች መረጃ እንዲሁም ከሌሎች ቡድኖች፣ ህትመቶች እና ምንጮች ለቤተሰቦች፣ ተማሪዎችና አዋቂዎች አገናኞችን ይሰጣል፡፡

**ወላጆች ለኦቲስቲክ የልጆች ትምህርት (PACE)**
በየወሩ በፌርፋክስ ሆስፒታል የትምህርት ጉባኤ ማእከል ይገናኛል፡፡
ያግኙን: pace-tm@excite.com

**የሰሜን ቨርጂኒያ ኦቲስቲክ ልጆች ወላጆች (POAC-NOVA) እና ሊስትሰርቭ**
www.poac-nova.org, president@poac-nova.org
POAC-NOVA ኦቲዝም ላለባቸው ልጆች ቤተሰቦችና በሰሜን ቨርጂኒያ ኦቲዝም ካለባቸው ልጆች ጋር ለሚሰሩ ባለሙያዎች ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ድርጅቱ ለጥያቄዎች በስልክና በኢሜል ምላሽ ይሰጣል፤ ወርሃዊ የድጋፍ የቡድን ስብሰባዎችን፣ መረጃዎችንና ግብአቶችን እንዲሁም ማህበራዊ ዝግጅቶችን ያቀርባል፤ በስራ ላይ ያለ ሊስትሰርቭ አለው፤ ጋዜጣ ያሰራጫል እንዲሁም ኦቲዝም ላለባቸው ልጆች በተለያዩ የስልጠና እድሎች ይሰጣል፡፡

**ንቁ የወላጆች ድጋፍ ቡድን**
ይህ ቡድን ሁሉም አይነት የአካል ጉዳት ላለባቸው ልጆች ቤተሰቦች ነው፡፡ ቡድኑ በየወሩ በኪንግስ ፓርክ ላይብረሪ፣ 9000 Burke Lake Road፣ Burke, Virginia ከ 7-9 ፒኤም ይገናኛል፡፡ ያግኙን: troutmanbeth@yahoo.com

**የብሔራዊ ካፒታል አካባቢ ስፒና ቢፊዳ ማህበር**
www.sbanca.org
ይህ ምዕራፍ በቨርጂኒያ እና አካባቢው የሚኖሩ ስፓይና ቢፊዳ ያለባቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን ያገለግላል፡፡ የአባላት አገልግሎቶች ወርሃዊ የድጋፍ ቡድኖችን፣ አመታዊ በአላትን እና የበልግ ሽርሽርን፣ ነጻ ህትመቶችን፣ SBAA እና CPSBA ጋዜጣዎችን፣ የግለሰብ ድጋፍና መረጃን፣ የወንድምና እህት ድጋፍን፣ ቤተሰብን ማዛመድና የአደጋ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍን በእያንዳንዱ ጉዳይ ያጠቃልላል፡፡

**ተንደር ኸርትስ**
www.tender-hearts.net, info@Tender-Hearts.net
ተንደር ኸርትስ ሲወለዱ ጀምሮ የልብ ጉድለት ላለባቸው ልጆች ቤተሰቦች የድጋፍ ቡድን ሲሆን በዋሽንግተን ዲሲ ሜትሮ አካባቢ ላሉ ቤተሰቦች የጋራ ድጋፍን፣ ተስፋን፣ የቤተሰብ ዝግጅቶችን፣ ተናጋሪዎችን፣ ግብአቶችንና የገንዘብ ማሰባሰቢያ እድሎችን ይሰጣል፡፡ ቡድኑ ሊስትሰርቭ፣ ጋዜጣ፣ የወላጅ ማገናኛ ፕሮግራምና ማህበራዊ ዝግጅቶችን ያቀርባል፡፡

**የእይታ እክል ላለባቸው ልጆች ወላጆች የቨርጂኒያ ማህበር**
www.vaapvi.org
ይህ ማህበር ማየት ለተሳናቸውና የማየት ችግር ላለባቸው ከ 0-21 አመት እድሜ ያላቸው ህጻናት ቤተሰቦችና ተንከባካቢዎች ድጋፍ ያደርጋል፡፡ የድጋፍ ቡድን ስብሰባዎችን፣ መረጃዎችንና ግብዓቶችን፣ የመርጃ ማዕከልን፣ ማህበራዊና መዝናኛ ዝግጅቶችን፣ ጋዜጣን፣ የቤተሰብ ማገናኛ መርሃ ግብርን፣ ጥብቅና፣ አውደ ጥናቶችንና ጥያቄዎችን በስልክና በኢሜል ይሰጣል፡፡

**ቨርጂኒያ ስማይልስ**
www.virginia-smiles.org, info@virginia-smiles.org
ይህ ድርጅት የተሰነጠቀ ከንፈር እና/ወይም የተሰነጠቀ ላንቃ ይዘው ለተወለዱ ሰዎች ትምህርት፣ መረጃና አእምሮአዊ ድጋፍ የሚሰጥና በህክምና ማህበረሰብ ውስጥ ተሰንጥቀው ለተወለዱ ሕክምና ለሚያደርጉ አካላት እንደ ግብአት ያገለግላል፡፡ የድጋፍ ቡድን ስብሰባዎችን፣ የበጋ ሽርሽርና የበአል ድግስን ጨምሮ ለወላጆችና ለህክምና ማህበረሰቡ የኔትዎርክ የዜና መጽሄት፣ የውይይት ሴሚናሮች፣ ቆንጆ ልጅ በሚል ርእስ ቤተሰብን ያማከለ ቪዲዮና ማህበራዊ ዝግጅቶችን ያቀርባል፡፡ እንዲሁም ከንፈራቸው/ላንቃቸው ተሰንጥቆ ለተወለዱ በቨርጂኒያ ውስጥ ላለ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፍተኛ የኮሌጅ የነጻ ትምህርት እድል ይሰጣል፡፡

# ጥብቅና/ክፍሎች/ስልጠና/ድጋፍ

**የሰሜን ቨርጂኒያ አርክ**
www.thearcofnova.org
703-208-1119
የአእምሯዊ እና የእድገት እክል ላለባቸው ሰዎች (The Arc) የአእምሮ እና የእድገት እክል ያለባቸውን ግለሰቦች ሰብአዊ መብቶችን የሚያስተዋውቅና ጥበቃ የሚያደርግ ሲሆን በህይወት ዘመናቸው ሙሉ በማህበረሰብ ውስጥ እንዲካተቱና እንዲሳተፉ በንቃት ድጋፍ ያደርጋል፡፡ አርክ በተደጋጋሚ እንደ የንብረት እቅድ ማውጣት፣ ሜዲኬድ መልቀቂያዎችና አስማሚ ግንኙነት ባሉ ርዕሶች ላይ አውደ ጥናቶችን ያቀርባል፡፡ ይህ ድርጅት በሰሜን ቨርጂኒያ ለሚገኙ በሁሉም እድሜ ላሉ የእድገትና የአእምሮ እክል ያለባቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦቻቸው ድጋፍ ይሰጣል፡፡

**የቨርጂኒያ ቤተሰብ ተሳትፎ ፕሮጀክት አርክ**
1-888-604-2677, ext. 103
ይህ ድርጅት በቨርጂኒያ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ለሚያገኙ ልጆች ቤተሰቦች ድጋፍና ጥብቅና በስልክና በኢሜል ጥያቄዎችን በመመለስ መረጃን፣ መርጃዎችንና ሊስትሰርቨር ያቀርባል፡፡ ድጋፍ በአንድ-ለአንድ የወላጅ-ለወላጅ የስልክ ማዛመጃ ፕሮግራም በኩልም የሚገኝ ይሆናል፡፡

**ኦቲዝም ስፒክስ**
www.autismspeaks.org
ኦቲዝም ይናገራል በሀገሪቱ ትልቁ የኦቲዝም ሳይንስና ተሚጋች ድርጅት መንስኤዎች፣ መከላከል፣ ህክምናዎችና የኦቲዝም ፈውስ ላይ ምርምር ለማድረግ በቁርጠኛነት በማደግ ላይ ይገናል፡፡ ስለ ኦቲዝም ህመም መታወክ ግንዛቤ መጨመር፤ እንዲሁም ኦቲዝም ላለባቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦቻቸው ፍላጎቶች ይሟገታል፡፡ ድርጅቱ ለቤተሰቦች ብዙ አጋዥ ግብአቶችን (*የ100 ቀን ኪትና አስፐርገር ሲንድሮም እንዲሁም ከፍተኛ ተግባር ያለው ኦቲዝም ኪት* ጨምሮ) እና ከሌሎች ጋር የመደራጀትና የመገናኘት እድሎችን ይሰጣል፡፡

**የጉዲፈቻ ድጋፍና ትምህርት ማዕከል (CASE)**

www.adoptionsupport.org

703-256-3820

CASE በጉዲፈቻ ማህበረሰብ ውስጥ ላለ ማንኛውም ሰው ድጋፍና ትምህርት ለመስጠት ቁርጠኛ የሆነ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡ CASE አውደ ጥናቶችንና በኢንተርኔት የሚደረጉ ስብሰባዎችን ለወላጆች፣ ባለሙያዎችና መምህራን ያቀርባል፡፡

**የወላጅ መረጃና ግብአቶች ማእከል**

http://www.parentcenterhub.org/

የወላጅ መረጃ እና ግብዓቶች ማእከል (CPIR) የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ቤተሰቦች በማገልገል ላይ እንዲያተኩሩ ለወላጅ ማሰልጠኛ መረጃ (PTI) ማእከላትና የማህበረሰብ የወላጅ መገልገያ ማእከላት (CPIR) እንደ ማእከላዊ የመረጃና ውጤቶች ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡ CPIR ብዙ የ NIHCY ግብአቶችን ይይዛል፡፡

**በሰሜን ቨርጂኒያ ውስጥ የትኩረት ጉድለት/ሃይፐርአክቲቭ መታወክ (CHADD) ያለባቸው ልጆችና አዋቂዎች**

https://www.meetup.com/novachadd/

703-641-5451

CHADD፣ AD/HD ላለባቸው ግለሰቦች ትምህርት፣ መሟገትና ድጋፍ የሚሰጥ ብሄራዊ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡ CHADD የምርምር ግስጋሴዎችን፣ መድሀኒቶችና ህክምናዎች AD/HD ያለባቸው ግለሰቦች፣ አባላትና ባለሙያዎች ወቅታዊ መረጃ እንዲኖራቸው ለማድረግ የተለያዩ መርጃዎችን ያሳትማል፡፡ እነዚህ መርጃዎች ትኩረት! መጽሔት፣ የ CHADD የመረጃና ለ AD/HD የመረጃ ምንጭ፣ ከ CHAD የሚገኝ ዜና፣ ነጻ በኤሌክትሮኒክ መልክ የሚላክ ወቅታዊ የዝግጅት ዜና መጽሔና ሌሎች ለመምህራን፣ ለባለሙያዎችና ለወላጆች ልዩ ትኩረት የሚሰቡ ህትመቶች ያካትታሉ፡፡

**ልዩ ለሆኑ ልጆች ምክር ቤት (CEC)**

www.cec.sped.org

1-888-232-7733, TTY: 1-866-915-5000

CEC የአካል ጉዳተኞችን እና/ወይም ስጦታዎችንና ተሰጥኦዎችን (ሁለት ጊዜ ልዩ) ትምህርታዊ ስኬትን ለማሻሻል የተቋቋመ ትልቁ ዓለም አቀፍ የባለሙያ ድርጅት ነው፡፡ CEC ለተገቢ የመንግስት ፖሊሲዎች ይሟገታል፣ የሙያ ደረጃዎችን ያዘጋጃል፣ የሙያ እድገትን ይሰጣል፣ ልዩነት ላላቸው ግለሰቦች ይሟገታል እንዲሁም ባለሙያዎች ውጤታማ ለሙያ ልምምድ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችንና ግብዓቶችን እንዲያገኙ እገዛ ያደርጋል፡፡ CEC የሚያቀርባቸው፡ ሙያዊ ልማት እድሎችና መርጃዎች፤ ልዩ መረጃ፤ በአዳዲስ የምርምር ግኝቶች ላይ ጆርናሎችና ጋዜጦች፣ የክፍል ልምምዶች፣ የፌዴራል ሕግና ፖሊሲዎች፤ ስብሰባዎችና ጉባኤዎች እንዲሁም ልዩ ትምህርታዊ ህትመቶች፡፡

**የሰሜን ቨርጂኒያ ዘላቂነት ማእከል**

www.ecnv.org

የ ENDependence ማእከል እድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ አካል ጉዳተኞች የሚተዳደር ሲሆን በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ የህብትና የጥብቅና ማእከል ነው፡፡ ECNV ራሱን የቻለ የኑሮ ፍልስፍና እና ለሁሉም አካል ጉዳተኞች እኩል ተደራሽነትን እንዲሁም የአካል፣ የአእምሮ፣ የግንዛቤና የስሜት ህዋሳት ችግር ያለባቸውን ሰዎች የራሳቸውን ህይወት እንዲመሩ ያበረታታል፡፡

**ፎርምድ ፋሚሊስ ፎርዋርድ**

www.formedfamiliesforward.org

703-539-2904

ፎርምድ ፋሚሊስ ፎርዋርድ በሰሜን ቨርጂኒያ አካባቢ ውስጥ ቤተሰቦችን፣ መምህራንና የህጻናት ደህንነት ባለሙያዎችን የሚያገለግል አሳዳጊ፣ ዘመድና የህጻናት አሳዳጊ ቤተሰቦችና አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን እንዲሁም ሌሎች ልዩ ፍላጎቶችን ለመደገፍ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡

**የአይሁድ ማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ**

www.jssa.org

JSSA ከፍተኛ ችሎታ ባላቸውና ተንከባካቢ የአእምሮ ጤናና የነርሲንግ ባለሙያዎች የሚሰጥ የተለያዩ የምክር፣ የትምህርትና የሙያ አገልግሎቶች፣ የቤት ውስጥ ድጋፍ፣ የሆስፒስና የነርስ እንክብካቤ እንዲሁም ማህበራዊ አገልግሎቶች ያቀርባል፡፡ JSSA በአመት ከ25,000 ለሚበልጡ በጣም ወጣት ከሆኑ እስከ አዛውንት ድረስ ላሉ ግለሰቦች አገልግሎትና ድጋፍ ይሰጣል፡፡ JSSA የሁሉም ሃይማኖት ተከታይ ቤተሰቦችን ያገለግላል፡፡

**ሜሪና ሜሊሳ ብሎር ራዲዮ ዝግጅት**

www.blogtalkradio.com/themaryandmelissashow, www.facebook.com/mary melissa

ይህ የጥሪ ቅስቀሳ የራዲዮ ንግግር ሾው በሀገር አቀፍ ደረጃ ይተላለፋል፡፡ በሀገሪቱ ዋና ከተማ በሚኖሩ ሁለት እናቶች የሚመራ ሲሆን አካል ጉዳተኛ/ልዩ ፍላጎቶች ያላቸውን ልጆች የማሳደግ መሰናክሎችን የሚጋሩና ልዩ ልዩ ተማሪዎችን ድጋፍ የማድረጊያ መንገዶች ላይ ለመወያየት የተለያዩ ባለሙያዎችንና የማህበረሰብ መሪዎችን ያስተናግዳሉ፡፡

**የሰሜን ቨርጂኒያ ቤተሰብ አገልግሎቶች - የመድብለ ባህላዊ መረጃና ሪፈራል የስልክ መስመር**

www.nvfs.org

703-385-3267, 571-748-2500

NVFS የመድብለ ባህላዊ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን በገቢ፣ በቋንቋ እና/ወይም በባህል እንቅፋት ምክንያት ነባር አገልግሎቶች ሊደርሱባቸው የማይችሉ ግለሰቦችን የአእምሮ ጤና ፍላጎቶች ለማሟላት ያቀርባል፡፡ ተጠቃሚ የሚሆኑት በአሰቃቂ ሁኔታ፣ በድህነት፣ በከባድ ውጥረትና በሌሎች ተግዳሮቶች የተነሳ የአእምሮ ጤንነታቸውና የተረጋጉ መሆናቸው የተጎዳ ከሁሉም የባህልና የዘር ቡድኖች የመጡ ግለሰቦች አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡ አገልግሎቶቹ እንደ ድብርት፣ ጭንቀት፣ ራስን አለማወቅና የስሜት ቀውስ ያሉ ችግሮችን የሚመለከቱና እነዚህም እንደ ግለሰብ፣ ጥንዶች፣ የቡድን እና የቤተሰብ ቴራፒ በተለያዩ መንገዶች ይሰጣሉ፡፡

**የሰሜን ቨርጂኒያ በእይታ የሚታገዝ ንግግር ማህበር**

www.nvcsa.org, info@nvcsa.org

ይህ ድርጅት ለአዋቂዎች እና ለቤተሰብ ተኮር እንቅስቃሴዎችና የመስማት ችግር ላለባቸው ካምፖች በእይታ የሚታገዝ የንግግር ክፍሎችን ያቀርባል፡፡

**የወላጅ ተሟጋች ጥምረት ለትምህርት መብቶች (PACER) ማእከል**

www.pacer.org

የPAER ማእከል ተልእኮ እድሎችን ማስፋትና የአካል ጉዳተኛ ህጻናትን እንዲሁም ጎልማሶችንና ቤተሰቦቻቸውን ጥራት ማሻሻል ወላጆች ወላጆችን በመርዳት ጽንሰ ሃሳብ ላይ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ PACER ማእከል በህጻናትና አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ወላጆች የተቋቋመ ሲሆን ሌሎች ወላጆችንና ተመሳሳይ ችግሮች የሚያጋጥሟቸውን ቤተሰቦች ለመርዳት ነው፡፡ PACER ለግለሰብ ቤተሰቦች፣ ዎርክሾፖች፣ ቁሳቁሶች ለወላጆችና ባለሙያዎች፣ እንዲሁም ለሁሉም ልጆች ነጻና ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት እንዲኖር አመራር ይሰጣል፡፡

**የወላጅ ትምህርት ተሟጋች ማሰልጠኛ ማዕከል(PEATC)**

www.peatc.org

703-923-0010 (Voice/TTY), 1-800-869-6782

የ PEAT ተልእኮ ለቨርጂኒያ ልጆች ከቤተሰቦች፣ ትምህርት ቤቶችና ማህበረሰቦች ጋር ተባብሮ በመስራት በትምህርት የላቀ እንዲሁም በትምህርት ቤትና በማህበረሰብ ህይወት ውስጥ ስኬትን ለማሻሻል አወንታዊ የወደፊት ጊዜአትን መገንባት ነው፡፡ ልዩ ትኩረት የሚደረገው አካል ጉዳተኛ ልጆች ላይ ነው፡፡ ለቤተሰቦችና ለባለሙያዎች አገልግሎት ድጋፍ፤ በጥናት ላይ የተመሰረተ መረጃና ስልጠና እንዲሁም ለስልታዊ ሽርክናና ለስርአታዊ መሻሻል ጥብቅና እድሎች ይሰጣል፡፡

**የልዩ ፍላጎት ልጆች መረጃ**
www.specialneedskidsinfo.com
ይህ ድረገጽ በቨርጂኒያና አካባቢው ላሉ ቤተሰቦች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ቤተሰቦች፣ ከተወለዱ እስከ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድሜ ያላቸው፣ ለልዩ ትምህርት አለም አዲስ ለሆኑ ወይም ልጆቻቸው በቅርብ ጊዜ በምርመራ ለተገኘባቸው ቤተሰቦች ያቀርባል፡፡

**የስልጠና/የቴክኒክ ድጋፍ ማዕከላት (T/TAC)**
www.ttaconline.org
ቨርጂኒያ T/TAC የትምህርት እድሎችን ለማሻሻልና አካል ጉዳተኞች ከተወለዱበት ጊዜ አንስቶ እስከ 22 ዓመት ድረስ የአካል ጉዳተኞችን ስኬት አስተዋጽኦ ለማድረግ ይፈልጋል፡፡ T/TAC ለአካባቢያዊ፣ ክልላዊና ስቴት ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት ጥራት ያለው ስልጠናና ቴክኒካል ድጋፍ እንዲሁም ነጻ የመስመር (ኦንላይን) ላይ የስልጠና ሞጁሎችን ያቀርባል፡፡

**የዩናይትድ ስቴትስ ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ምክር ቤት**
www.usicd.org, info@usicd.org
202-480-2332
USICD የአካል ጉዳተኞችን መብቶችና ሙሉ ተሳትፎ በአለምአቀፍ ተሳትፎና በዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳዮች ያካሂዳል፡፡ የUSICD አባልነት የአካል ጉዳተኞች እኩል መብቶች የሚጠበቁበትና የላቀ ደረጃ ላይ ያሉ የአካል ጉዳተኞች አቅምና ተሰጥኦ የሚከበርበት እንዲሁም ከፍ ያለና አካል ጉዳተኞች እንደ ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ማህበረሰብ ድንበር ተሻግረው የሚሰባሰቡበት ዓለም እንዲኖር ራእይ አለው፡፡

**የቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ ዩኒቨርሲቲ የኦቲዝም የልህቀት ማዕከል (VCU-ACE)**
www.vcuautismcenter.org
የ VCU-ACE ፕሮግራም በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) እና በባህሪ ጤናና ልማት አገልግሎቶች መምሪያ (DBHDS) የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ነው፡፡ VCU-ACE ASD ያለባቸው ሰዎች ሙሉ አቅማቸውን ማሳካት እንዲችሉና በራስ የመመራት፣ አርኪ ህይወት የመምራት መብት እንዳላቸው የሚያምን ሲሆን ይህንንም በስልጠና፣ በቴክኒክ ድጋፍ፣ በአገልግሎቶችና ድጋፎች ላይ ትብብርና ምርምርን በማሟላት ለማሳካት ጥረት ያደርጋል፡፡ ተልእኮው የስፔክትረም ህመም ያለበትን ፍለሰብ የሚደግፉ ቤተሰቦችን፣ መምህራንና ባለሙያዎችን እውቀት፣ ክህሎትና ግንዛቤን በማሻሻል ኦቲዝም ስፔክትረም ህመም ያለባቸውን ግለሰቦች ውጤት ለማሻሻል በስቴቱ በሙላ አቅም መገንባት ነው፡፡ VCU-ACE እና APS በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ASD ላለባቸው ተማሪዎች በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ልምዶችን ግንዛቤን ለመጨመርና በትክክል ትግበራን ለማሳደግና ለክፍል መምህራን፣ ሐኪሞችና ደጋፊ ባለሙያዎች ቀጥተኛ ሞዴሊንግና ስልጠና ለመስጠት በመተባበር ላይ ናቸው፡፡ VCU-ACE የመስመር (ኦንላይን) ላይ የስልጠና ሞጁሎችንና መረጃዎችን ያቀርባል፡፡

**ራይትስሎ**
www.Wrightslaw.com
የራይትስሎው ድረገጽ በብዙ የልዩ ትምህርት ርእሰ ጉዳዮች ላይና ስለስልጠና እድሎች መረጃን በተመለከተ ነጻ ጽሑፎችን ይዟል፡፡

## የአካባቢ በአመት/በየሁለት አመት የሚደረጉ የጉባኤ እድሎች

**የተደራሽነት ስብሰባ**
www.accessibilitysummit.org
በየአመቱ በጸደይ ወቅት በቪየና፣ ቨርጂኒያ በሚገኘው በማክሊን መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን የሚካሄደው ይህ ጉባኤ በተለያዩ የልዩ ትምህርት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ከሀገር ውስጥና ከሀገር አቀፍ እውቅና ካላቸው ተናጋሪዎች ጋር አውደ ጥናቶችን ያቀርባል፡፡ ወርክሾፖች በሶስት መንገዶች ይከፈላሉ፡ ቤተሰብና ተንከባካቢ፣ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ማህበረሰብ፡፡

**CHAD ብሔራዊና ክልላዊ ጉባኤ**
www.chadd.org, www.novachadd.org
CHADD በAD/HD ላይ ለወላጆች፣ AD/HD ላለባቸው አዋቂዎች፣ መምህራንና የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች የትምህርት ጉባኤ ያዘጋጃል፡፡

**የፌርፋክስ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (FCPS) የልዩ ትምህርት ጉባኤ**
https://www.fcps.edu/resources/family-engagement/parent-resource-center
FCPS በተለያዩ የልዩ ትምህርት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ከ FCPS አቅራቢዎችና ከተጋባዥ ንግግር አድራጊዎችች ጋር አውደ ጥናቶችን ያቀርባል፡፡

**ፊውቸርኩዌስት**
http://futurequest.gmu.edu/
FutureQuest የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች፣ ወላጆችና ባለሙያዎች ነፃ፣ ክልላዊ፣ በአመት ሁለቴ የሚኖር የስራ እና የኮሌጅ መድረክ ነው፡፡

**የእድገት እና የመማር እክሎች ላይ ሁለንተናዊ ምክር ቤት (ICDL) ጉባኤ**
www.icdl.com
የICDL አመታዊ ኮንፈረንስ አላማ ወላጆችና ባለሙያዎች ከተለያዩ የትምህርት ዘርፎች የተውጣጡ እውቀትንና ብቃቶችን እንዲያዋህዱ መርዳት ሲሆን ይህም በጨቅላነት እና በልጅነት ጊዜ የስሜት እና የእድገት እክሎችን መከላከልን፣ መገምገምን፣ መመርመርንና ህክምናን ማሻሻል ነው፡፡

**ለኦቲዝም ምርምር ድርጅት**
www.researchautism.org
የኦቲዝም ምርምር ድርጅት በኦቲዝም ላይ ተግባራዊ ምርምር የሚያካሂድ ነው፡፡ በመካሄድ ላይ ያሉ ጥናቶችን በተመለከተ ከመላው አገሪቱ የመጡ ተናጋሪዎች ሪፖርት አድርገዋል፡፡

# ለወታደር ቤተሰቦች ግብአቶች

**የኦቲዝም ትምህርት፣ መረጃና ለወታደር ቤተሰቦች ዝግጅቶች - በየሁለት ወሩ መጽሄድ**
የአካባቢ ነዋሪ እና የሰሜን ቨርጂኒያ የኦቲስቲክ ልጆች ወላጆች መስራች ጠቃሚ ዜናዎችን፣ ጽሁፎች፣ ጥናቶችንና በኦቲዝም ማህበረሰብ ውስጥ ላሉ የወታደር ቤተሰቦች የሚሰቡ ክስተቶችን የሚዘረዝር በወር ሁለት ጊዜ ኢሜል እንዲጠናቀር ያደርጋል፡፡ ሁሉን አቀፍ ጽሁፎች የሚቀርቡት በነጻ ነው፡፡
በ CampbellsServices@gmail.com ያግኙን፡፡

**ልዩ የቤተሰብ አባል ፕሮግራም (EFMP) - ሄንደርሰን አዳራሽ**
www.dcmilitary.com
703–614–7200

ልዩ የቤተሰብ አባል ፕሮግራም ልዩ ፍላጎት ላላቸው የወታደር ቤተሰቦች እርዳታ ይሰጣል፡፡ ልዩ የሆነ የቤተሰብ አባል በአካል፣ አእምሮአዊ ወይም ስሜታዊ ፍላጎት የተነሳ የህክምና ወይም የትምህርት አገልግሎት የሚያስፈልገው ልጅ፣ የትዳር ጓደኛ ወይም ጥገኛ ወላጅ ሊሆን ይችላል፡፡ የልዩ ፍላጎት ምሳሌዎች አለርጂዎች፣ አስም፣ ኦቲዝም፣ የአቴንሽን ጉድለት መታወክ፣ ሴሬብራል ፓልሲ፣ ዲስሌክሲያና ድብርት ያካትታሉ፡፡ በ EFMP ውስጥ መመዝገብ ግዴታና የተዋቀረ ሲሆን ይህም የባህር ኃይል ልዩ የቤተሰብ አባል አስፈላጊውን እንክብካቤ የሚያገኙበት ቦታዎች ላይ ለመመደብ ያስችላል፡፡ የ EFMP ስራ አስኪያጅ በህክምና እንዲሁም ትምህርታዊ ግብአቶች፣ ጥብቅና፣ ወርክሾፖች፣ የእረፍት ጊዜ እንክብካቤና የቤተሰብ ድጋፍ ቡድኖች እርዳታ ይሰጣል፡፡ ለማንኛውም እድሜ ጠበቃ፣ ፕሮግራሙ ስለልጅዎ የግል የትምህርት እቅድ ጥያቄዎችም የሚያግዝዎት ይሆናል፡፡

**ልዩ የቤተሰብ አባል ፕሮግራም (EFMP) - ፎርት ቤልቮር**
www.belvoir.armymwr.com
703-805-4590

**ልዩ የቤተሰብ አባል ፕሮግራም (EFMP) - ፎርት ማየር**
703-696-3510, 703-696-1229

**ልዩ የቤተሰብ አባል ፕሮግራም - የዩናይትድ ስቴትስ የባህር ኃይል**
www.mccshh.com/efmp

**ልዩ የውትድርና ስልጠና ወላጆች (STOMP)**
http://wapave.org/programs/specialized-training-military-parents-stomp, pave@wapave.com
1-800-572-7368 እና 1-253-565-2266 (ለመውሰድ መደወል ይቻላል)
STOMP ልዩ ትምህርት ወይም የጤና ፍላጎት ያላቸው ልጆች ላሏቸው ወታደራዊ ቤተሰቦች ለመርዳት የተቋቋመ በፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ የወላጅ ማሰልጠኛና መረጃ (PTI) ማእከል ነው፡፡ በግዳጅ ላይ ያለ፣ ተጠባባቂና ጡረታ የወጡ ወታደርን ጨምሮ በአለም ዙሪያ ላሉ ወታደራዊ ቤተሰቦች ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የድጋፍ የቡድን ስብሰባዎችን፣ መረጃዎችንና ግብአቶችን፣ ማህበራዊና መዝናኛ ዝግጅቶችን፣ ሊስትሰርቨርን፣ ወርሃዊ ጋዜጣን፣ የድንገተኛ ጊዜአዊ እንክብካቤ፣ ወርክሾፖችንና ጥያቄዎችን በስልክና ኢሜል ይሰጣል፡፡

# የድንገተኛ እንክብካቤ

**ድንገተኛ እንክብካቤ ምንድነው?**

አካል ጉዳተኛ ልጅን በማሳደግ ላይ ካሉት ተግዳሮቶች አንዱ እረፍት ሲፈልጉ፣ ሞግዚት ሲፈልጉ ወይም ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥም ልጅዎን ለመንከባከብ ብቁ የሆነ ሰው ማግኘት ነው፡፡ ድንገተኛ ጊዜአዊ እንክብካቤ በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ልጅዎን በጊዜያዊነት እንዲንከባከቡ የሰለጠኑ አዋቂ ሰዎችን ያቀርባል፡፡ ብዙ ድንገተኛ እንክብካቤ አቅራቢዎች በተለይ የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ልጆች ወንድሞችና እህቶችም እክብካቤን ያደርጋሉ፡፡ ብዙዎች መድህን ዋስትናን፣ ድጋፍን ወይም በገቢ ላይ ተመስርተው ተንሸራታች የክፍያ መጠን ይቀበላሉ

- የማክሊያን መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን አገልግሎት ሚኒስትሪ፣ http://www.mcleanbible.org ፣ 703-639-2000
- የሰሜን ቨርጂኒያ ARC፣ www.thearcofnova.org፣ 703-208-1119
- እንክብካቤ ማህበረሰቦች፣ www.caringcommunities.org፣ 866-CARING-4 (866-227-4644)
- የኤዲ ክለብ፣ www.eddiesclub.org፣ 703-304-2330
- የመጀመሪያው የአሜሪካ የቤት ጤና አጠባበቅ፣ 703-922-9555
- ጂልስ ሃውስ፣ http://jillshouse.org፣ 703-639-5660
- ሜሪ ፋሚሊ፣ 540-364-4757
- የሰሜን ቨርጂኒያ ቤተሰብ አገልግሎቶች (NVFS)፣ www.nvfs.org፣ 571-748-2500

# ድጋፎችና SSI

# የቨርጂኒያ ድጋፎችና ማህበራዊ ዋስትና

## ሜዲኬድ ድጋፎች

ከተቋማት በተቃራኒ አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን በቤታቸው እና በማህበረሰባቸው ውስጥ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማበረታታት የሜዲኬድ ድጋፎችን ተዘጋጅተዋል፡፡ ሜዲኬድ ብቁ ለሆኑ ግለሰቦች የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል፣ እናም፣ ግዛቶች የተወሰኑ መስፈርቶችን "እንዲያቋርጡ" ይፈቅዳል፣ (ግለሰቦች የሜዲኬድ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት በተቋማት ውስጥ የሚኖሩበትን መስፈርት ጨምሮ)፡፡

ከተቋማት በተቃራኒ አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን በቤታቸው እና በማህበረሰባቸው ውስጥ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማበረታታት የሜዲኬድ መልቀቂያዎች እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ ሜዲኬድ ብቁ ለሆኑ ግለሰቦች የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጥ ሲሆን እንዲሁም ስቴቶች የተወሰኑ መስፈርቶችን "እንዲተዉ" (ግለሰቦች የሜዲኬድ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት በተቋማት ውስጥ የሚኖሩበትን መስፈርት ጨምሮ) ይፈቅዳል፡፡

የመማርና ለማቋረጥ የማመልከቱ ሂደት በጣም ውስብስብ ቢሆንም ነገር ግን ልጅዎ ለመልቀቅ ብቁ መሆን አለመቻሉንና በየትኛው እድሜ ላይ ማቋረጡን ማመልከት እንዳለባቸው ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ቤተሰቦች ውስብስብ የአካል ጉዳት አገልግሎት ሥርአትን እንዲሄዱ የሚረዳውን የሰሜን ቨርጂኒያ አርክን እንዲያነጋግሩ ይበረታታሉ፡፡ በድረገጽ http://www.thearcofnova.org ወይም በ 703-532-3214 የሰሜን ቨርጂኒያ አርክ በመደወል ማግኘት ይችላሉ፡፡

የቨርጂኒያ ሜዲኬድ ማቋረጦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- የግለሰብ እና የቤተሰብ የእድገት አካል ጉዳት (IFDDS) መቋረጥ
  *(ብዙውን ጊዜ "DD Waiver" በመባል ይታወቃል)*
- የአእምሯዊ አካል ጉዳት (ID Waiver)
- አረጋውያን ወይም የአካል ጉዳተኞች የተጠቃሚ አቅጣጫ (EDCD) መቋረጥ

ተጨማሪ መረጃ በቨርጂኒያ የህክምና እርዳታ አገልግሎት ክፍል (DMAS) በ http://www.dmas.virginia.gov/ ይገኛል፡፡

## የማህበራዊ ዋስትና ተጨማሪ የዋስትና ገቢ (SSI)

**ከውልደት እስከ 18 ዓመት**
ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 18 ዓመት ድረስ ያሉ ልጆች "እንቅስቃሴን በከባድ ሁኔታ የሚገድብ አካላዊ ወይም አእምሯዊ ችግር(ሮች)" ወይም ቢያንስ አንድ አመት የሚቆይ **እና** የገቢ መስፈርቶችን ያሟላል ተብሎ የሚጠበቅ ከሆነ ለ SSI ጥቅማጥቅሞች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**18 አመት እድሜና ከዚያ በላይ**
እርስዎና ባለቤትዎ በጣም ብዙ ገቢ ወይም ሃብት ስለነበራችሁና በዚህ ምክንያት ልጅዎ 18ኛ አመት ልደቱ ከመድረሱ በፊት ለ SSI ብቁ ካልሆነ/ካልሆነች እሱ ወይም እሷ በ18 አመቱ/ቷ ለ SSI ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ለአካል ጉዳተኞች የማህበራዊ ዋስትና ጥቅማጥቅሞች የበለጠ ለማወቅ፣ www.ssa.gov ይጎብኙ ወይም የቨርጂኒያ የማህበረሰብ ማገገሚያ ፕሮግራሞችን (vaACCSES) በ http://www.vaaccses.org/about_us ያግኙ፡፡